## የአጼው መንግሥት ዕድገት ።

በ1270 በሰሜኑ ደጋማ ኢትዮጵያ በላስታ የአገው ክርስቲያን ስርወ መንግሥት በአዲሱ " የሰለሞናውያን " ባላንጣው ስርወ መንግሥት በተለወጠ ጊዜ በደቡብ ኢትዮጵያ ከላይ የተጠቀሱ የሀርላ ፣ የሀዲያና የጐንጋ እስላማዊና አዋማዊ አገሮችና መንግሥታት በየአካባቢያቸው በዕድገትና በመስፋፋት ሂደት ላይ ነበሩ ።

በሰሜኑ ደጋማ ኢትዮጵያ ከአክሱማውያን ስርወ መንግሥት ውድቀት በኋላ በፈረቃ የተነሱ የአገውና " የሰለሞናውያን " የአጼ ስርወ መንግሥታትና ነገሥታት በመሬት ፣ በግዛትና በንግድ ጉዳዮች የመስፋፋት ዋና አካባቢዎችና አቅጣጫዎች በደቡብ ኢትዮጵያ የጐንጋ — ዳሞት ፣ የሀዲያ — ሲዳማና የሀርላ—ይፋት አገሮችና ሕዝቦች ሆነው ተገኙ ።

በዚህ አኳያ በ1270 በሰሜኑ ደጋ የአገው ስርወ መንግሥት "በሰሎሞናውያን " ስርወ መንግሥት ከተለወጠ አስራ አምስት ዓመታት በኋላ በ1285 በደቡብ ኢትዮጵያ በሀርላ አገር የጥንቱ የሸዋ ስርወ መንግሥት (896—1285) በአዲሱ የይፋት ዋለስማ ስርወ መንግሥት ተለወጠ ። [8]

ሁለቱ የሥልጣን ባላንጣ የገዥ መደቦች በኋላ በየአካባቢያቸው በዘላን ሰፋሪዎች እስኪሸነፉ ድረስ ፣ ከአስራ ሦስተኛው ምዕተ ዓመት እስከ አስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ድረስ መሀልና ደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያን የማያቋርጥ ጦርነት ክልል አደረጉት ። [9] በዚህ ነገር ከ1270 እስከ 1314 ድረስ የመጀመሪያ " ሰለሞናውያን " አጼዎች በአካባቢው የጐንጋ—ዳሞት ፣ የሀዲያ—ሲዳማና የሀርላ—ይፋት አገሮችንና መንግሥታትን ለማስገበር ያልተሳካ ጥረት አደረጉ ።

በመጨረሻ የይፋቱ ሱልጣን ቀዳማዊ ሰብረዲን (132 ? —1332) ከሀዲያው ሱልጣን አመኖ ጋር የጦርነት ግምባር ፈጥሮ በመሀልና በሰሜን ዳሞት ፣ ወረብ ፣ ዋጅ ፣ አላማለል፣ ፈጠጋር ፣ እንዳገብጠን ፣ ሙገር ፣ ግራርያ ፣ ተጉለት ፣ መንዝ ፣ አምሐራ ፣ እንደርታ ፣ ጐጃም ፣ በጌምድር ፣ አንጐት ፣ . . . በተባሉ በአጼ ዓምደጽዮን (1314—1344) ክፍለ ሀገራት ላይ ገዥዎቼን እሾማለሁ ፣ የአገሩም ንጉሥ እኔ ራሴ እሆናለሁ ፣ የአጼውንም ንግሥት በምርኮ ወስጄ እንደገረድ እህል አስፈጫታለሁ ፣ በክርስቲያኖችም ምድር በእስላሞች ዘንድ የተወደደውን ልዩ የጫት ተክል እተክላለሁ በማለት በታላቅ ዛቻና ዘመቻ ተነስቶ ክተት አወጀ ። [10]

---

[8] *Ibid.*, p. 62.
[9] *Ibid.*, pp. 69-90.
[10] Huntingford, *Glorious Victories*, pp. 54-58.



ነገር ግን አጼ ዓምደጽዮን የይፋትና የሀዲያ መሪዎችና ወታደሮች በዘመቻ ቅንጅትና ስምሪት የተግባር እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት ሁለቱንም በቅድሚያ በሥፍራና በጊዜ አለያይቶ በመውጋትና ድል በመቀዳጀት በዘመነ መንግሥቱ በመላ ኢትዮጵያ ማለትም በክርስቲያኑም ፣ በእስላሙም ፣ በአዋሙም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የአጼውን መንግሥት ማዕከላዊ የበላይ ሥልጣን መሠረተ ። በሰሜንና በደቡብ ኩሻዊ ፣ ሴማዊ ፣ ናይሎቲካዊና ኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች አንድነት በአፍሪካ ቀንድ አንድ በሀውርታዊ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕብረተሰብ መሠረተ ። [11]

ተከታዮቹ ጠንካራ አጼዎች ዳዊት (1382—1414) ፣ ይስሐቅ (1414-1429) እና ዘርዓ ያዕቆብ (1434—1468) የዓምደጽዮንን የአገር ግምባታ ፖሊሲና ተግባር የበለጠ በማጠናከር በአፍሪካ ቀንድ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ እስላማዊ የሀርላ—ሀዲያ አገሮችን በደቡብ ምስራቅ ፣ በመሀል ምዕራብ አዋማዊ የጐንጋ ሕዝቦችን ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም አዋማዊ የኦሞ ክልል ነባር አገሮችን በሰሜኑ ደጋ ብዙ ክርስቲያንና አዋማዊ አገሮችንና ክፍለ ሀገራትን በሙሉ በአንድ ማዕከላዊ የአጼው መንግሥት ሥር አደራጁ ። [12]

በ1460ዎቹ እስከ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ድረስ በአፍሪካ ቀንድ በኢትዮጵያ በሀውርታዊ የአጼ መንግሥት ሥር በአገሪቱ መንግሥታዊ ዜና መዋዕሎችና በዘመኑ የአረብ ሰነዶች በስም የታወቁና በተለያዩ ደረጃ የውስጥና የአካባቢ አስተዳደር ሥልጣን የነበራቸው ማህበረሰቦች ፣ የአስተዳደር ክልሎችና ገባር አገሮች ከዚህ በላይ በ1332 በሱልጣን ሰብረዲን የተዘረዘሩት ተጨምሮ በከፊል ፤

የዳሞት ፣ የወረብ ፣ የዋጅ ፣ የአይማለል — ጉራጌ ፣ የፈጠጋር ፣ የእንዳገብጠን ፣ የሙገር ፣ የግራርያ ፣ የጸላልስ ፣ የከተታ ፣ የምድረዜጋ ፣ የወጋዳ ፣ የሰርማት ፣ የተጉለት ፣ የመንዝ ፣ የወለቃ ፣ የሸዋ ፣ የአምሐራ ፣ የአንጐት ፣ የቅዳ ፣ የአገው ፣ የፈላሻ ፣ የጐጃም ፣ የበጌምድር ፣ የሺሜ ፣ የእንደርታ ፣ የሰሜን ፣ የወገራ ፣ የጸለምት ፣ የዋግ ፣ የሰሐርት ፣ የዶባ ፣ የትግራይ ፣ የአክሱም ፣ የሐማሴን ፣ የባህረ ነጋሽ ፣ የሰምሀር ፣ የናራ ፣ የዋዲባ

---

[11] *Ibid.*, the entire chronicle.

[12] Peruchon, *Les Chroniques*; *Omari, Masalik*; Maqrizi, *Moslem kings*; Doresse, *Histoire Sommaire*,pp. 189-202.

ርካ ፣ የጋንጅ ፣ የደፋት ፣ የድዋሮ ፣ የአዳል ፣ የአራባቢኒ ፣ የሀዲያ ፣ የሻርካ ፣ የባሊ ፣ የዳራ ፣ የከምባታ ፣ የሶማሌ ፣ የጋፋት ፣ የወላሞ ፣ አገሮችና ሕዝቦች እንደ ነበሩ ይታወቃል ። [13]

## ኢትዮጵያና የአረቡ ዓለም ።

የአገሮች የውጭ ግንኙነትና ግንዛቤ ሁልጊዜ ቁልፍ ነገር ነው ። በመሆኑም ጥንት በዘመነ አክሱም ፍጻሜና በመካከለኛው ዘመን በአገውና " በሰለሞናውያን " ስርወ መንግሥታት ወቅት አጐራባች የአረብ መንግሥታትና ታዋቂ ጸሐፊዎች ስለኢትዮጵያ በሀውርታዊ የአጼ መንግሥት የነበራቸውን ግምትና ግንዛቤ በዚህ ጥናት በአሁኑ ደረጃ ማገናዘብ የዘመኑን ታሪክ የበለጠ ለመረዳት ያስችላል ።

በዚህ አኳያ፣ታዋቂው የአረብ የታሪክ ባለሙያ ኢብን ያቁቢ በ872[14] እንደ መዘገበው ፣ በዘመኑ በቀይ ባህር የዳህላክ ደሴት ገና የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ውስጣዊ አካል ነበር ። ሌላ የዘመኑ ታዋቂ የአረብ ምሁር ማሱዲ በ935 [15] እንደ ጻፈው ፣ በአሥረኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ የዳህላክ ደሴትና በኤደን ባህረሰላጤ የዚላ ወደብ ጨምሮ የአፍሪካ ቀንድ የሰሜንና የምስራቅ ጠረፍ ግዛቶች በሙሉ የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ይዞታዎች ነበሩ ። በ970ዎቹ [16] የአረብ ጸሐፊ ኢብን ሀውቃል እንደ ጻፈው ፣ በአሥረኛው ምዕተ ዓመት ፍጻሜ አሁንም የዚላ ወደብ የኢትዮጵያ መንግሥት አካል ነበር ። የዘመኑ የአረብ ታዋቂ የጅኦግራፊያ ምሁር ኢድሪስ (1100—1136) እንዳረጋገጠው ደግሞ በአስራ ሁለተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በአፍሪካ ቀንድ በኤደን ባህረሰላጤ ጠረፍና በሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ የበርበሮች ምድር የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት የግዛት ክልል ውስጥ ነበር ። [17]

እንዲሁም እነዚህና ሌላም የመካከለኛው ዘመን ታዋቂ የአረብ ጸሐፊዎች በአፍሪካ ቀንድ በኢትዮጵያ የአጼ መንግሥትና በሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ከጉአርዳፋይ ጫፍ እስከ ዛንዚባር ደሴት በሚደርስ ረጅም ቀበሌ ከነበረው ከባንቱ የአዛኒያ መንግሥት መካከል በሥፍራና በፖለቲካ ይዞታ የነበረውን ልዩነት በግልጽ አስታውቋል ። [18]

[13] Huntingford, *Glorious Victories*, Omari, *Masalik*, Maqrizi, *Moslem* Kings perruchon, *Les chroniques*.
[14] Trimingham, *Islam*, pp. 50-51.
[15] Doresse, *Histoire Sommaire*, p. 191.
[16] *Ibid*.
[17] *Ibid*.,p. 192.
[18] *Ibid*., figs. 5. 6. pp 49, 145,



ይህ ጥንታዊ የባንቱ የአዛኒያው መንግሥት በአፍሪካ ቀንድ በተጠቀሰው የሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ በዓመተ ዓለም ከመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ገደማ ጀምሮ በዘመነ ክርስትናእስከ አስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ለ1500 ዓመታት ጊዜ እንደ ነበር ጥንታዊ የግሪክ ፣ የሮማውያንና የአረብ ጸሐፊዎች በየዘመናቸው ከሰጡት መረጃዎች ይታወሳል ። በመጨረሻ ግን ከአካባቢው የኦሮሞና የሶማሌ ማኅበረሰቦች የአዛኒያን ሕዝብ እንዳስለቀቁት የትውፊት መረጃ ይጠቁማል ።

በአፍሪካ ቀንድ ጥንታዊ የኢትዮ—አዛኒያን የወሰን ክልል በሚመለከት ፣ የአረብ ጸሐፊ ማሱዲ እንዳስቀመጠው ፣ በአስረኛው ምዕተ ዓመት የዋቤ ወንዝ በሁለቱ አገሮች መካከል የተፈጥሮ የወሰን መስመር ነበር።[19] የአረብ የጅኦግራፊያ ባለሙያ የነበረው ኢብን ሴይድ (1214—1274) በዘመኑ ጨምሮ እንደመዘገበው ደግሞ ፣ በአስራ ሦስተኛው ምዕተ ዓመት፣ በሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ የሞቃዲሾ ከተማ ሕዝብ በሃይማኖት እስላሞች ከፖለቲካ ሥልጣን አኳያ ግን ከፊሉ በኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ስር ከፊሉ እንዲሁም በአዛኒያ መንግሥት ስር ነበር ። [20]

በተጨማሪም ፣ በመካከለኛው ዘመን ሁለቱም አረቦችና ኢትዮጵያውያን በአፍሪካ ቀንድ የኢትዮጵያ እስላሞችን መሬት ክልል " ባር ሰአዳዲን " ፣ የአዛናውያንን ክልል ደግሞ " ባርአይጃን " ማለትም በቅደም ተከተል " የሰአዳዴን መሬት " ፣ " የአዛኒያ መሬት " እያሉ በኢትዮጵያና በአዛኒያ የአገር ክልሎች መካከል ልዩነት ይገልጹ እንደ ነበር አይዘነጋም ። [21]

ከአረብ ታዋቂ ጸሐፊዎች በተለይ በ1348 ለሞተው ኢብን ፋድል አላህ አማሪ ፣ ለማክሪዚ (1366—1442) እና ለሽሃባዲን አብዱልቃድር) (1506—1543) በሕግ ሙያው አረብፋቂህ ተብሎ ለሚታወቀውና በ1530ዎቹ የኢማም አህመድ ግራኝን ጦርነት ዜና መዋዕል ለጻሐፈው በኢትዮጵያ ታሪክ የአገርና የትውልድ ምስጋና የሚገባቸው ባለውለታዎች ናቸው ።

ከሦስቱ ባለወለታዎች አማሪ በግብጽ በ1332 በኢትዮጵያ እስላም አገሮች ላይ አጼ ዓምደጽዮን ባካሄደው ጦርነት ጉዳይ በ1330ዎቹ የዚላው

[19] *Ibid*. 127.
[20] *Ibid*., p. 133.
[21] *Ibid*., figs 5, 6, pp. 49. 145; W. Conzelman, tr. and ed; *Histoire de Galawedwos Roi'd Ethiopie* (1895), pp. 121-122; Arab Faqih, *Conquete*. p. 7.
" የባርሰአዳዲን " ሌላ ተለዋጭ ስያሜ " የተባበሩ የዚላ አገሮች " ነበር ።

ሼክ ጀማልዲን አብደላህ ከኢትዮጵያ የይፋትን ልዑካን ቡድን መርቶ ለፖ ለቲካ ድጋፍ ወደ ግብጽ ቤተ መንግሥት በሄደ ጊዜ ከቡድኑ መሪ በተሰ ጠው ዝርዝር መረጃ መሠረት የኢትዮጵያን የሰባቱ የይፋት ፥ የደዋሮ ፥ የአራባቢኒ ፥ የሀዲያ ፥ የሻርካ ፥ የባሌና የደራ ሱልጣኔቶች ታሪክ ጽፎ ለዓ ለም አቆየ ። [22] ማክሪዚ ደግሞ ከአንድ መቶ አመታት በኋላ በአስራ አራ ተኛው ምዕተ ዓመት የአማሪን ታሪክ በአዲስ መረጃ አጠናክሮ በአገሪቱ ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ በቀረቡ በዋለስማ ሱልጣኖችና " በሰለሞናው ያን " አጼ ነገሥታት መካከል ለረጅም ዘመን የተካሄደውን የግዛትና የሥልጣን ጦርነት በዝርዝር መዝግቦ ለትውልድ ያስተላለፈው ባለውለታ ነው ። [23]

ከዜላው ሼክ ጀማልዲን አብደላህ በተሰጠው መረጃ መሠረት ፥ በ1330ዎቹ አማሪ እንደ ጻፈው ፥በአፍሪካ ቀንድ በመካከለኛው ዘመን የኢ ትዮጵያ የአጼ መንግሥት ብሔራዊ የጠረፍ ክልል [24] በደቡብ ምስራቅ ከሕንድ ውቅያኖስ አንስቶ በሰሜን ምዕራብ ከባርካ ቆላ ፥ ባሻገር እስከ የዛሬው ከሰላ አካባቢ የሚያርስ ሰፊ ግዛት ሲሆን ፥ በዚህ ታላቅ በሀውር ዊ መንግሥትና ሕብረተሰብ፥በአንድ ማዕከላዊ የአጼ ሥልጣን ስር ዘጠና ዘጠኝ ታላላቅና ትንንሽ የአካባቢ ነገሥታትና አገረ ገዥዎች ነበሩ ። [25]

በአስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ከተባሉት ዘጠና ዘጠኝ የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት የአስተዳደር ክልሎች መካከል በአማሪ መጽ ሐፍ ሰምሃር ፥ሳሆ ፥ ሃማሴን ፥ ናሬ፥ ባርያ ፥ ትግራይ ፥ ሰሐርት ፥ አምሐራ ፥ ሸዋ ፥ ዳሞት ፥ ገንዘ ፥ አዳል ፥ ሞራ ፥ ይፋት ፥ ደዋሮ ፥ አራባቢኒ ፥ ሀዲያ ፥ ሻርካ ፥ ባሊና ደራ በተለይ በስማቸው ተለይተው ተጽፈዋል ። [26]

ጸሐፊ አማሪ ጨምሮ እንደመዘገበው ፥ በዘመኑ በኢትዮጵያ በሀው ርታዊ የአጼ መንግሥት ሥር አዋማዊ ፥ የክርስትና የጁዳይዝምና የእስል ምና ሃይማኖቶችን የሚከተሉና በቁጥር አምሳ የሚሆኑ የቋንቋ ማህበረሰ ቦች ነበሩ ። [27] እንዲሁም በአረቡ ምሁር ቃል ፥ በዘመኑ ኢትዮጵያ እያ ንዳንዳቸው ሰባት ሰባት የድምጽና የንባብ እንዚሮች ከአላቸው ከሃያ ስድ ስት የፊደል ዘሮች ማለትም በድምር ከ182 የፊደል ምልክቶች የተፈጠ ረና የራስዋ የሆነ ብሔራዊ የጽሕፈት ሥርዓት ነበራት ። [28]

[22] Trimingham, *Islam in Ethiopia*, p. 72.
[23] Maqrizi, *Moslem kings*.
[24] Omari, *Masalik*, p. 22.
[25] *Ibid.*, p. 25
[26] *Ibid.*, pp. 22-26.
[27] *Ibid.*, p. 21.
[28] *Ibid*



በመጨረሻም በ1430ዎቹ ማክሪዚ ከአጉራባቹ ከየመን አገር ሆኖ የእስላም ነገሥታት በኢትዮጵያ በሚል አርዕስት በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ መጽሐፍ በጻፈ ጊዜ ፥ የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ብሔራዊ የጠረፍ ክ ልል በደቡብ ምስራቅ ከባቢልማንደብ ሰርጥ ጀምሮ በሰሜን ምዕራብ በከ ሰላ አካባቢ ወደ ተከሩር ደርሶ በአባይ ሸለቆ በኩል ወደ ደቡብ ምዕራብ ወደ አባይ ወንዝ መነሻ ድረስ መዘርጋቱን መዝግቦአል ። [29]

## የሱልጣኖችና የአጼዎች የሥልጣን ጦርነት ።

በ1332 የሱልጣን ሰብረዲንን የአመጽ ጦር አጼ ዓምደጽዮን በአጸፋ ዘመቻ ድል ከአደረገው በኋላ ፥ ቃዲ ሰለሂ የተባለ የይፋት የሃይማኖት መሪ አስራ ሰባቱን የአዳል ፥ የሞራ ፥ የለበከላ ፥ የሀገራ ፥ የፈድሴ ፥ የግዳድ፥ የነገብ ፥ የዙባ ፥ የሀርላ ፥ የሁባት ፥ የተርባ ፥ የዕዶም ፥ የአልብሮ ፥ የዜላ ፥ የእስቴ ፥ የደዋሮና . . . የአካባቢ ነገሥታት ጨምሮ በ2722 የጦር አዛዦች የሚመራ ታላቅ የይፋት ጦር እንደገና አደራጅቶ የዓምደጽዮንን ሠራዊት በአዲስ ኃይል ገጠመው ። [30]

የዓምደጽዮን ዜና መዋዕል ጸሐፊ በእግረ መንገዱ ጨምሮ እንደገለ ጸው የቃዲ ሰለሂን ዘመቻ የመሩ የይፋት 2722 የአካባቢ ነገሥታት ቃዲ ዎች ፥ ባላባቶችና የጦር አዛዦች በአገራቸው በድምር 12,048 መስጊዶች ነበሩአቸው [31] ። ይህ መረጃ በደቡብ ምስራቅ ከ890 እስከ 1332 ድረስ በአራት ምዕተ ዓመት ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያ እስላሞች በኢኮኖሚ ፥በከ ተማ ፥ በንግድ በሃይማኖትና በባህል የደረሱበትን ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ያሳያል ። ቢሆንም በጦር ድርጅትና ስምሪት ጉድለት የሰብረዲንና የሰለሂ ዘመቻዎች በኃይል በተደራጀ የአጼ ዓምደጽዮን ጦር ተሸነፈ ። በጦርነቱ ወቅት የይፋት ከተሞች ፥ መስጊዶች ፥ መንደሮችና እርሻዎች በዓምደጽ ዮን ወታደሮች በወል ተቃጠሉ ። በመደዳ ተዘረፉ ።

በዚህ ረገድ ለምሳሌ በጦርነቱ መጀመሪያ እርሱና ወታደሮቹ በይ ፋት ከተሞችና አገር ላይ ያደረሱትን ታላቅ የሕይወትና የንብረት ጥፋት ለባላንጣው ሱልጣን ሰብረዲን አጼ ዓምደጽዮን ራሱ በታላቅ የድል ስሜት እንደሚከተለው ይገልጸል ። በአጼው ቃል ፤

" ከአገሬ በተነሳሁ በሙሉተኛው ቀን ከሰባት ፈረሰኞች ጋር ወደ እንተ ከተማ ገባሁ ። . . . ከዚያ በኋላ የተቀሩ ወታደሮቼ ደርሰው የይፋ

[29] Maqrizi, *Moslem Kings*, p. 1.
[30] *Huntingford, Glorious Victories*, pp. 74-80.
[31] *Ibid.*, p. 80.

ትን ምድር ፈጽመው አጠፉት ። እኔም ከዚያ አገር እንደ አሸዋ የበዛ ወርቅ ብርና ነሐስ ከብዙ አልባሳት ጋር ወሰድኩ ። ቀጥሎም ወታደሮቼን ኩል ጐራ ፣ ገዳያ ፣ ኩባት ፣ ፈድሲ ፣ ሃርጋያ ፣ በቁልዛርና ሸዋ ወደሚባሉ የእስላም አገሮች በሙሉ ሰደድኩ ። እነርሱም በእነዚህ አገሮች ሁሉ ጦርነት አካሄዱ ። ሰዎቹን በሰይፍ ገደሉ ። ታላላቅና ጽኑ ከተሞቻቸውን አቃጠሉ ። በተጨማሪም ቁጥር ሥፍር የሌለ የእንስሳትና የሰዎች ምርኮ ወሰዱ ። ”[32]

በ1332 የዋለስማ ሱልጣኖችና መሳፍንቶች በይፋትና በአዋሽ ሸለቆ በአጼ ዓምደጽዮን ሠራዊት እንደዚህ በብርቱ ከተደበደቡ በኋላ ብዙ ጊዜ ሳይቆዩ በዛሬው ሰሜን ምስራቅ ሸዋ ይፋትን ለአጼው ክርስቲያኖች በመተው ከአስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ጀምረው በቀዳማዊ ሱልጣን ሀቀዲንና በሱልጣን ሰአዳዲን መሪነት በደቡብ ምስራቅ “አዳል” የሚባል አንድ ሌላ አገርና መንግሥታዊ ማዕከል መሠረቱ ።[33]

አሁን የይፋት—አዳል ሱልጣኖች በምስራቅ ከዘይላ ጠረፍ በምዕራብ እስከ ታችኛው ሃዋሽ ሸለቆና የሐረርጌ ደጋ ክልል ያለውን እስትራቴጂያዊ ምድር በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው በደቡብና በመሀል ኢትዮጵያ ለአጼዎች በሚገብሩ አገሮችና ሕዝቦች ሁሉ ላይ በወል የጥቃትና የጥፋት ጦርነት ጀመሩ ።[34]

ይህን አዲስ የዋለስማ ሱልጣኖችን የአመጽ ፖሊሲ ለማጥፋት አጼ ዳዊት (1382—1413)፣ አጼ ይስሐቅ (1414—1429) እና አጼ ዘርዓ ያዕቆብ (1434—1468) በመላው ደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ አዲስ ወታደራዊ ዘመቻ ጀመሩ ። በዚህ አኳኋን አጼ ዳዊት ሱልጣን ሀቃዲንን ገደለ ። በአስራ አምስተኛው ምዕተ ዓመት መባቻ አመጸኛው የዋለስማ ሱልጣን ሰዳዲን ደግሞ በአጼ ይስሐቅ ወታደሮች በዘይላ ወደብ ሸሽቶ በመሸገበት ተገደለ ። በመሆኑም የዘይላ ወደብ ለመጀመሪያ ጊዜ በአጼው ጦር በቀጥታ ተያዘ ።[35]

በ1415 ሱልጣን ሰአዳዲን በአጼው ጦር በዘይላ ወደብ ከተገደለ በኋላ የሟቹ የሱልጣን አሥር ልጆች አምልጠው በስደት ወደ የመን ሄዱ ። ነገር ግን ከሃያ ዓመታት በኋላ ከየመን ስደታቸው ተመልሰው የሰአዳዲን ልጆች ሱልጣን ዳግማዊ ሰብረዲን ፣ ሱልጣን ማንሱር ፣ ሱልጣን ዳግማዊ ጀማልዲንና ሱልጣን በድላይ በአካባቢው ከሀዲያ አመጸኛ መሪዎች ጋር የአ

[32] *Ibid.*, p. 56.

[33] Maqrizi, *Moslem Kings*, pp. 14-18; *Trimingham*, *Islam*, p. 74.

[34] *Ibid.*

[35] *Ibid.*



መጽ ግምባር ፈጥረው በመላው ደቡብ ምስራቅ ለአጼው በሚገብሩ አገሮችና ሕዝቦች ላይ ለረጅም ጊዜ የጥቃት ጦርነት ከፈቱ ።

ነገር ግን አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በብርቱ ወታደራዊ እርምጃ የዋለስማ ሱልጣን በድላይንና የሀዲያ ሱልጣን ማሂኮን በጦር ሜዳ በመግደል በተለይ የይፋት—አዳል ሱልጣኖችን አመጽ በዘመኑ ደመሰሰ ።[36] በተጨማሪም አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በአጼው መንግሥት የአስተዳደር ክልሎችንና የገባር አገሮችን ሰላምና ጸጥታ የሚጠብቁ “ ጩዋ ” የሚባሉ ንጉሣዊ ወታደሮችን በነዋሪነት የማስፈር ፖሊሲና ፕሮግራም ጀመረ ።[37]

አጼ ዘርዓ ያዕቆብ የአዳልና የሀዲያ አመጸኛ ሱልጣኖችን አሰያይቶና አከታትሎ በተለያዩ ሥፍራዎች ከገደላቸው በኋላ እስከ 1520ዎቹ ድረስ ለረጅም ጊዜ የአዳል ጥንታዊ የዋለስማ ሱልጣኖችና መሳፍንቶች የአመጽና የጦርነት ፖሊሲያቸውን በመተው ለአገሪቱ ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት ዓመታዊና ወቅታዊ ግብር እየገበሩ በሰላም ለመኖር አዲስ የፖሊሲ ምርጫና እርምጃ ወሰዱ ።[38]

ነገር ግን በሌላ በኩል ከ1470 ገደማ ጀምሮ በአዳል አገር የዘይላ ፣ የሐረር ፣ የዳካር ፣ የሁባት ፣ የገዳያ ወዘተ ታላላቅ ከተሞችና ክፍለ ሀገራት መሪዎችና ገዥዎች በነበሩት በእነኤሚር ለዳይ ኡትማን ፣ በእነኤሚር ማህፉዝ ፣ በእነኤሚር አቡባከር መሪነትና አዝማችነት የአጼዎችንና የሱልጣኖችን ኃይል ፣ ፖሊሲ ፣ ሥራና ስምምነት በትጥቅ የሚቃወሙ በሕብረተሰቡ ዘንድ ገረዶች ፣ ኤሚሮች ፣ ዋዚሮች ፣ ኢማሞች፣ አውራዮች፣ ቃዲዎች ፣ ሼኮች ተብለው የሚታወቁ አመጸኛ ባላባቶች ነጋዴዎችና የሃይማኖት ወገኖች ለአገሪቱ ሱልጣኖችና አጼዎች ባላንጣዎች ሆነው ተከሰቱ።

በመጨረሻ በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በትውፊታዊ ስያሜ “ አህመድ ግራኝ ” ማለትም “ አህመድ ግራ እጁ ” ተብሎ የሚታወቀው ኢማም አህመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዛዚ (1506—1543) የዚህ የአዳል ባላባታዊ የዋዚሮች ፣ የኤሚሮች ፣ የነጋዴዎች ፣ የቃዲዎች የሕግ ባለሙያዎችና የሃይማኖት ምሁራን የአመጽ እንቅስቃሴ መሪና አዝማች በመሆን በሁለቱም በኢትዮጵያ በአካባቢው የዋለስማ ሱልጣኖችና በማዕአከላዊ ጼዎች ሥልጣንና ሥርዓት ላይ አገር አቀፍ የጥፋት ጦርነት በ1524 ከፈተ ።

[36] Perruchon, *Chroniques*, pp. 20-23, 58-65.

[37] *Ibid.*, pp. 31,45

[38] *Ibid.*, p. 3; Trimingham, *Islam*, pp. 81-82.

## 3. የአህመድ ግራኝ አመጽ ከ1524 እስከ 1543

### የታሪክ መረጃ

የኢማም አህመድ ግራኝ አመጽ ከ1524 እስከ 1543 ድረስ የአዳል አመጸኛ ኤሚሮች ማለትም የክፍለ ሀገር ገዥዎች ከኩተማ ነጋዴዎችና ከሃይማኖት ምሁራን ጋር በሕብረት በሁለቱም ማለትም በዋለስማ መሳፍንት በሚመራው በአዳሉ አካባቢያዊ የገዥ መደብና በአገር አቀፍ ደረጃ ደግሞ በአገሪቱ ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት ላይ በድምሩ ለአሥራ ዘጠኝ ዓመታት ያካሄዱት በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ በማህበራዊ ዕድገት በሕይወት ፣ በኀብረትና በባህል ከፍተኛ ጥፋት ያስከተለ የእርስ በርስ ጦርነት ነው ። የጦርነቱ ታሪክ ቁልፍ የመረጃ ምንጮች የሚከተሉ ሰነዶች ናቸው።

የጦርነቱ ዋናው የመረጃ ምንጭ በማዕረግ ስሙ አረብ ፋቂህ ተብሎ የሚታወቀው ታዋቂ የየመኑ የሕግ ባለሙያ ሽሃብዲን ቤን አብደል ቃዴር የተባለው የኢማም አህመድ ግራኝ ዜና መዋዕል ጸሐፊ በ1535 በጦርነቱ መካከል በአረብኛ ቋንቋ የጻፈው ታላቅ መጽሐፍ ነው ። የአረብፋቂህ መጽሐፍ በተለይ የሚገልጸው የጦርነቱን ከ1524 እስከ 1535 ድረስ የተፈጸመውን የዘጠኝ ዓመታት ታሪክ ብቻ ነው ። የመጽሐፉ ደራሲ አረብ ፋቂህ አሊቃው ኢማም አህመድ ግራኝ በአዳሉ የዋለስማ መሳፍንታዊ የገዥ መደብና በአገሪቱ ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት አመራር ላይ በአካባቢና በአገር አቀፍ ደረጃ ታላቅ ጦርነት አካሂዶ በሰሜን ምዕራብ በጣና ሐይቅ አጠገብ በደምብያ ማለትም በፈላሻ ምድር የመንግሥቱን ማዕከል ከመሠረተው በኋላ የጦርነቱን ታሪክ በድንገት ያቆማል ።

ይህ በኢማም አህመድ ግራኝ አመጽ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ አጠቃላይ የመካከለኛው ክፍለ ዘመን ታሪክ አንድ ቁልፍ የመረጃ ምንጭ የሆነው ታላቅ መጽሐፍ ለትውልድና ለታሪክ የተላለፈው በአዳል መንግሥት ተወላጆችና ወራሾች እጅ በታላቁ የሐረር ከተማ ሲጠበቅ ኖሮ በመጨረሻ በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ፍጻሜ በአውሮፓ ምሁራን ግኝትና ትርጉም ነው ። [1] ለዚህ ጥናታችን እንደ ዋና ምንጭ የተወሰደው መጽሐፍ ታዋቂው የፈረንሳይ ምሁር ረኔ ባሴት ከረጅም ትምህርታዊ የግርጌ ማብራሪያ ጋር ከአረብ ፋቂህ የአረብኛው ሰነድ ወደ ፈረንሳይኛ የተረጎመው ነው ። [2]

[1] Antoine D,'Abbadie et philippe paulitshke, trs. and eds; *Furuh el Habacha Des Conquetes Faites En Abyssinie Au XVI Sicle* (Paris, 1899) pp. V-VI.

ግራኝ=ግራ እጁ በዘልማድ ግራኝ የሚለው ነው ።

[2] Arab—Faqih, *Histoire de La Conquete de Abyssinie XVI Sicle*, tr and ed. by F. Basset (1987).



በኢማም አህመድ ግራኝ አመጽ ታሪክ ተጨማሪ የመረጃ ምንጮች የአጼ ልብነ ድንግል (1508—1540) አጭር ዜና መዋዕል ፣ [3] የአጼ ገላውዴዎስ (1540—1559) ዜና መዋዕል ፣ [4] በ1780—1783 በጉንደሩ ደጃዝማች ኃይሉ እሸቴ የተዘጋጀ አጭር የዜና መዋዕሎች ማስታወሻ ፣ [5] እና በኢማሙ ላይ በክርስቲያን አጼ የሚመራውን ማዕከላዊ መንግሥት ለመርዳት ተብሎ በ1541—1543 ከሕንድ ወደ ኢትዮጵያ የተላከውን የፖርቱጋል ወታደራዊ ግብረ ኃይል ጉዞና ተግባር የሚገልጹ በሁለት የግብረ ኃይሉ አባሎች የተጻፉ ሁለት መጻሕፍት ናቸው ። [6]

ከእነዚህ የታሪክ መረጃዎች ፣ የልብነ ድንግል አጭር ዜና መዋዕልና የኃይሉ እሸቴ የዜና መዋዕሎች ዘገባ በጦርነቱ ታሪክ ቁንጽል ማስታወሻዎች ናቸው ። የገላውዴዎስ ዜና መዋዕልና የፖርቱጋል መጻሕፍት የሚገልጹት ዋናው ነገር እንዴት የዘመኑ ሁለት የዓለም ኃያላን የፖርቱጋልና የቱርክ መንግሥታት በሃይማኖት ስምና ሽፋን የመጀመሪያው በ[illegible]ው ወገን የሁለተኛው ደግሞ በኢማሙ ወገን ጣልቃ ገብተው በ1541—1543 በኢትዮጵያ የኢማም አህመድ ግራኝን ዘመንና መንግሥት ወደ መጨረሻ ውድቀት እንደ አደረሱት ነው ።

የአረብ ፋቂህ ታላቅ መጽሐፍም ሆነ የገላውዴዎስ ዜና መዋዕል ወይም የፖርቱጋል መጻሕፍት በታላቁ የኢትዮጵያ የ1524—1543 የእርስ በርስ ጦርነት ከ1541 በፊት በሁለቱም ተፋላሚዎች ወገን በቀጥታ የውጭ ኃይሎች ማለትም የቱርክና የፖርቱጋል መንግሥታት እጅ እንደነበር አያሳዩም ። በመሆኑም እስከ ዛሬ በአጼው ማዕከላዊ መንግሥት ላይ የኢማም አህመድ ግራኝ አመጽና ድል በአገሪቱ የክርስቲያን መንግሥት ላይ በቱርኮች ተጽዕኖ የተፈጠረና በውክልና የተካሄደው የእስላም የወረራ ጦርነት ነው የሚለው ሃይማኖታዊ የአጼው ደጋፊዎች ቲሲስ የጦርነቱ ወገናዊ ትርጉም ነው ።

[3] R.K. Pankhurst, ed., *The Ethiopian Royal Chronicles* (1967). pp. 49-59.

[4] W.E. Conzelman, tr. and ed., *Chronique de Galawedos, Roi de Ethiopie* (1895).

[5] R.Basset, tr. and ed., *Etudes Sur L,'Histoire D'Eth'iopie* (1881).

[6] M.de Castanhoso, *The Portuguese Expedition to Abyssinia* 1541-1543, tr. and ed. by R.S. Whiteway (1892); J. Bermudes, *A Short Account of the Embassy which the Patriarch D. Ioab Bermudes brought from the Emperor of Ethiopia*, tr. and ed. by R.S, Whiteway and Annexed to Castanhoso's, The Portuguese expedition to Abyssinia (*Ibid*)

ለካስታንሆሶ የፖርቱጋሎች ጀግንነት ተርጓሚዎቹ ሙራድ ካሚልና ዮና ቦጋለ (አዲስ አበባ (1952)

## የአዳል እርስ በርስ ሎርነትና የአህመድ ግራኝ አነሳስ ።

ባጭሩ የኢማም አህመድ ግራኝ አመጽ የኢትዮጵያ እስላሞች ረጅምና ውስብስብ ታሪክ አንድ አጭር መግለጫ ነው ። በመሆኑም በአገሪቱ ታሪክ አንድ ከፍተኛ ጉዳይ ነው ። በዚህ አኳያ ፣ ከ896 እስከ 1577 ድረስ ለሰባት ምዕተ ዓመታት የሸዋ (896—1285) ፣ የይፋት (1285—1415) እና የአዳል (1515—1577) ተከታታይ ሱልጣኔቶች በፈረቃ በተነሱ የሸዋ ማክሪዙማና የይፋት ዋለስማ ስርወ መንግሥታትና ሱልጣኖች አመራር ከሸዋ ፣ ከይፋት ከዜላ ፣ ከዳካር ፣ ከአውሳና ከሐረር አካባቢያዊና ወቅታዊ የፖለቲካ ማዕከላት ፣ በኋላ ከአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ፍጻሜ ጀምሮ ቀበሌው በአፋር ፣ በሶማሌና በኦሮሞ ማህበረሰቦች ቁጥጥር ስር እስ ኪሆን ድረስ ፣ በምስራቅ ከዜላ ጠረፍ አንስቶ በምዕራብ ወደ አባይ—ጊቤ ወንዞች ክልል በሚደርሰው ሰፊ ምድር ከንግድ ሥራ ጋር የእስልምና ሃይማኖት ፣ ባህልና ሥልጣኔ እንዳስፋፉ አሁን ከታሪክ መረጃና ምርምር በት ክክል ታውቋል ። [1]

በዚህ ረጅም የታሪክ ዘመን ፣ በተለይ ከ1285 እስከ 1577 ድረስ የይፋት — አዳል ሱልጣኖች በየጊዜው በአመጽ መነሳታቸው ባይቀርም ለኢትዮጵያ ማዕከላዊ የአጼ መንግሥትና ነገሥታት ወቅታዊ ግብርና አገልግሎት የሚሰጡ የአካባቢ ባላባቶች ነበሩ ።

በዚህ ነገር ፀዘመኑ ዓምደጽዮን የዋለስማን የመጀመሪያ ሱልጣኖች በኃይል ሚዛን እንዳስገበራቸው ፣ በኋላም አንገብርም ብለው በየጊዜው በአመጽ የተነሱ ኃይለኛ የይፋት—አዳል ሱልጣኖችን ማለትም ዳግማዊ ሀቀዲንን ፣ ሰአዳዲንንና በዲላይን የአገሪቱ ማዕከላዊ አጼዎች ቀዳማዊ ዳዊት ፣ ይስሐቅና ዘርዓ ያዕቆብ በየዘመናቸው በቅጣት እርምጃ እንደገደ ሉአቸው ተመልክቷል ።

በ1445 አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በአመጽ ሴራ የተነሱ አጐራባች የአዳልና የሀዲያ የአካባቢ ሱልጣኖችን በዘመቻ ገድሎአቸው እስከ ሞቃዲሾ ጠረፍ[2] ድረስ በመላው ምስራቅ ፣ ደቡብና መሀል ኢትዮጵያ ማዕከላዊ የአጼ መንግሥትን የበላይ ሥልጣን የበለጠ ካጠናከረው በኋላ የአዳሉ የዋለስማ ሱልጣኖች ወቅታዊ የአመጽ ፖሊሲያቸውን በመለወጥ ለማዕከላዊ የአጼ ነገሥታት የተለመደውን መንግሥታዊ ግብር ፣ አገልግሎትና ክብር እየ ሰጡ የአካባቢ ሥልጣናቸውን ይዘው በሰላም የመኖር አዲስ ዝንባሌና የተግባር እርምጃ ማሳየት ጀመሩ ። [3]

---

[1] UNESCO, *African History*, III, pp. 575-585; Irimingham, *Islam in Ethiopia*, pp. 58-76.

[2] Perruchon, *Chroniques* pp. 20-21; Doresse, *Histoire Sommaire* pp. 199, 201-202

[3] *Trimingham, Islam in Ethiopia*, p. 81; Perruchon, *Chroniques*, p.3.



በዚህ አኳያ ለምሳሌ የአዳሉ ሱልጣን መሐመድ በዲላይ (1445—1471) ለአጼ በዕደማርያም (1468—1478) ቤተ መንግሥት የደንቡን ዓመታዊ ግብርና አገልግሎት እየሰጠ በማዕከላዊው የአጼ መንግሥት ሥር በሰላም ለመኖር የነበረውን አዲስ የሰላምና የግብር ውሳኔ ተግባራዊ እንዳደረገው ይታወሳል ። [4]

በአንጻሩ ግን ከ1470ዎቹ እስከ 1520ዎቹ ድረስ በአዳል የአካባቢ ሱልጣኖችና በአገሪቱ ማዕከላዊ አጼዎች መካከል የተከሰተውን አዲስ የፖለቲካና የግብር ስምምነት የሚቃወም የአዳል ፊውዳላዊ የኤሚሮች ፣ የገረዶች ፣ የዋዚሮች የኢማሞች ፣ የሕግ ምሁራን ፣ የአውራዎች ፣ የበታዎች ፣ የቃዲዎች ፣ የሀጂዎች ፣ የሼኮችና የሸሪፎች ማለትም የክፍለ ሀገር ባላባቶች ፣ የከተማ ነጋዴዎችና የሃይማኖት መሪዎች አዲስ መደባዊ እንቅስቃሴ በዜላ ፣ በዳካር ፣ በአውሳ ፣ በሁባት ፣ በገዳያና በሐረር ታላላቅ ክፍለ ሀገራትና ከተሞች በእነ ኤሚር ለደይ ኡትማን ፣ በእነ ኤሚር ማህፉዝ ፣ በእነ ኤሚር አቡባከር መሪነትና አዝማችነት ተፈጥሮ በመጨረሻ ለ1524—1543 አገር አቀፍ የኢማም አህመድ ግራኝ አመጽ የፖለቲካ የድርጅትና የርዕዮተ ዓለም ቅድመ ሁኔታዎችን መንገዶችንና ማግሪያዎችን አዘጋጀ ። [5]

በዚህ የሽግግር ዘመን ፣ በኋላ በአስራ ስምንተኛው ምዕተ ዓመት በሰሜኑ ደጋ የኦሮሞ ራሶች የጐንደር አጼ ነገሥታትን እንደሚያደርጉት የአዳል አመጸኛ የዜላ ፣ የሁባትና የሐረር ክፍለ ሀገር ኤሚሮች የአገራቸውን የመስተዳደር ሥልጣን ከጦር ኃይል ጋር ከያዙ በኋላ የዋለስማን ደካማ ሱልጣኖች ለአመጽ ፖሊሲያቸውና ተግባራቸው በኃይል የፖለቲካ ሽፋን አድርገው መጠቀም ጀመሩ ።

ከአዳል አመጸኛ ኤሚሮች የመጀመሪያው የዜላ ክፍለ ሀገር ገዥ ለደይ ኡትማን በሱልጣን ሻምሱዲን መሐመድ (1472—1487) ዘመን በአጼ በዕደማርያም ላይ በአመጽ ተነሳ ። [6] በአመጹ ጅምር በአጼው የቅጣት እርምጃ የአዳል አገር በጦር ኃይል በከፋኛ ሲደበደብ ብዙ ኤሚሮችም በምርኮ ተወሰዱ ። ቢሆንም በ1475 ገደማ አዳሎች በኤሚር ለደይ ኡትማን መሪነት የአጼ በዕደ ማርያምን ሁለት ተከታታይ ዘመቻዎች ድል አድርገው መለሱ ። [7] ከዚያ በኋላ የበዕደ ማርያም ልጅና ወራሹ አጼ እስ

---

[4] *Ibid.*

[5] *Ibid.*, pp. 81-86; Arab-Faqih, *Conquete*, pp. 6-33.

[6] *Trimingham, Islam in Ethiopia*, p. 82.

[7] *Ibid.*

ክንድር (1478—1494) በኤሚር ለደይ ኢትማን ላይ ባካሄደው የቅጣት ዘመቻ ከሐረር በስተደቡብ የአዳልን የዳካር መዲና ደበደበ ፡፡[8] ነገር ግን በመጨረሻ በ1494 አጼው ራሱም በአዳሎች ተገደለ ፡፡[9]

በሱልጣን መሐመድ አዝሀረዲን (1488—1518) ዘመን የሐረርና የዜላ ገዥ ኃይለኛው ኤሚር ማህፉዝ በኋላ የኢማም አህመድ ግራኙ ሚስት የዝነኛ ባታህ ድል ወንበረ[10] አባት ለሃያ አምስት (1492—1517) ዓመታት በሦስት ማዕከላዊ አጼዎች እስክንድር ፣ ናኦድ (1494—1508) እና ልብነ ድንግል (1508—1540) ዘመን በደዋሮ ፣ በፈጠጋርና በይፋት ታላላቅ መሀል ክፍለ ሀገራት ላይ በየወራቱ የዘረፋ ጦርነቶችን ሲያካሂድ ኖሮ በመጨረሻ በ1517[11] በፈጠጋር በአጼ ልብነ ድንግል የጦር አበጋዝ ገብረ እንድርያስ ሲገደል ፣ አብሮት የነበረው ሱልጣን መሐመድ በደዋሮ አጐራባች እስላሞች እርዳታ በፈረስ አምልጦ ወደ አገሩ ወደ አዳል ከተመለሰ በኋላ ፣ በ1518[12] በሟቹ ኤሚር ልጅ መሐመድ እጅ ተገደለ ፡፡

የአዳል የመስተዳደርና የጦር ኃይለኛ መሪ ማህፉዝና ሱልጣን መሐመድ እንደዚህ በአንድ ጊዜ ከተገደሉ በኋላ ከ1518 እስከ 1527 ድረስ በአዳል መሪዎችና በጦር ሹማምንቶች መካከል ታላቅ የሥልጣን ጦርነት ተፈጠረ ፡፡ በዚህ የሽግግር ወቅት በ1520 የሟቹ ሱልጣን ልጅና ወራሽ ሱልጣን አቡበከር መሐመድ (1518—1527) የአዳልን የፖለቲካ ማዕከል ከዳካር ወደ አዲሱ የሐረር መዲና አዛወረ ፡፡[13] ከ1520 እስከ 1527 ድረስ የአዳል አገር በተለይም የሐረር ፣ የሁባትና የዜላ ታላላቅ ከተሞችና ክፍለ ሀገራት በአገሩ መሪዎችና ባለሥልጣኖች መካከል የሥልጣን ጦርነት መድረኮችና መስኮች ሆኑ ፡፡[14]

በዚህ ወቅትና አኳያ ሱልጣን መሐመድ አዝሀረዲንን የገደለው መሐመድ ማህፉዝ በ1519 ገደማ ለአንድ ዓመት የአዳል ኤሚር ሆኖ ከገዛ በኋላ እሱም ራሱ በሁባቱ ገዥ በኢብራሂም አህመድ ተገደለ ፡፡ የሁባቱ ኢብራ

---

[8] *Ibid.*

[9] UNESCO, *African History*, p. 585.

[10] Arab-Faqih, *Conquete*, p. 51.


[11] *Ibid.*, p. 61

[12] *Ibid.*, p. 9; Trimingham, *Islam in Ethiopia*, pp. 82-83; Arab-Faqih, *Conquete* p. 61, note 1.

[13] *Ibid.*, *Conquete*, p. 25.

[14] *Ibid.*, pp. 9-33.






ጥንታዊው የሐረር መስጊድ

ሂም[15] አህመድ በአዳል ኤሚርነት ሦስት ወራት ከገዛ በኋላ ራሱም በቀድሞ ኤሚር ማህፉዝ ባርያ በነበረው በወሰኒ ተገደለ ፡፡ ወሰኒ ራሱ በአዳል ኤሚርነት ሦስት ወራት ከገዛ በኋላ በማንሱር ማህፉዝ ተሸንፎ በዜላ ተገደለ ፡፡

ኤሚር ማንሱር ደግሞ ለአምስት ወራት የአዳል የመስተዳደርና የጦር መሪ ከሆነ በኋላ የወደፊቱ ኢማም አህመድ ግራኙ ሞግዚት—አስተማሪ በነበረው ገራድ አቡን ተገደለ ፡፡ ገራድ አቡን የአዳል የመስተዳድርና የጦር መሪ ሆኖ ፣ በአረብፋቂህ ቃል ፣ በፍትህና በሰላም አገሩን ለሶስት ዓመታት ያህል ከአስተዳደረ በኋላ በ1520ዎቹ መጀመሪያ አጋማሽ በሱልጣን አቡበከር መሐመድ ሴራ በዜላ ሲገደል ፣ ኢማም አህመድ ግራኙ በሱልጣን ላይ በአመጽ ተነሳ ፡፡

---

[15] *Ibid.*, p. 10. ይህ የሁባቱ ኢብራሂም አህመድ ፤ አረብፋቂህ መጽሐፍ ውስጣዊ ይዘትና ሂደት መሠረት የወደፊት አመጸኛ ኢማም አህመድ ግራኙ ወላጅ አባት ይመስላል ፡፡



ጥንታዊው የሐረር መስጊድ

በገራድ አቡን ጦር ውስጥ አንድ ፈረሰኛ ወታደር የነበረው ኢማም አህመድ ግራኝ ጌታው በሱልጣን አቡበከር ከተገደለ በኋላ ከጥቂት ተከታዮቹ ጋር በሱልጣኑ ላይ ሸፍቶ ወደ አባቱ አገር ወደ ሁባት ገባ ። ከ1524 እስከ 1527 ድረስ ሱልጣን አቡበከር የሶማሌ ወንበዴዎችን [16] ሰብስቦ የአስራ ሰባት ዓመት ወጣት የነበረውን አመጸኛ ኢማም አህመድ ግራኙን ለመግደል በሐረርና በሁባት መካከል በተለያዩ ሥፍራዎችና ወቅቶች ብዙ ያልተሳኩ ሙከራዎችን አድርጐ በመጨረሻ በ1527 ራሱ በአመጸኛው ኢማም እጅ ወደቀ ። [17]

በአዳል ሱልጣኖችና ኤሚሮች መካከል የተካሄደው ይህ ረጅም የሥልጣን ጦርነትና ሽብር በ1527 በኢማም አህመድ ግራኙ አመጽና ድል ወደ አንድ ከፍተኛ ምዕራፍ ደረሰ ። ቀጥሎም ከ1527 እስከ 1543 ድረስ ከምስራቅ አካባቢ አልፎ በአገር አቀፍ ደረጃ ተስፋፋ ። በ1527 የሃያ አንድ ዓመት ወጣት ኢማም አህመድ ግራኙ ሱልጣን አቡበከርን ገድሎ በምትኩ የሟቹን ወንድም ኦማርዲንን (1527—1553) ዙፋን ላይ አስቀመጠ ። [18]

በ1529 ኢማም አህመድ ግራኙ ከደዋሮ ዘመቻ በድል ከተመለሰ በኋላ ሱልጣን ኦማርዲን በግብርና በምርኮ ጥያቄ የዋለስግን ጥንታዊ የመሳፍንት መደብ አስተባብሮ ኢማሙን ከነተከታይ ኤሚሮቹ ከሥልጣን በኩዴታ ለማባረር ያልተሳካ የአመጽ እርምጃ በወሰደ [19] ጊዜ የአዳል ሕብረተሰብ መደባዊ ጥንቅርና ጥቅም ብሎም የኢማም አህመድ ግራኙ አመጽ ኢኮኖሚያዊ ፡ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መሠረትና መነሻ በጉልህ ታየ ።

በ1529 ክረምት ወራት ኢማም አህመድ ግራኙ ከደዋሮ ዘመቻ በታላቅ ድልና የሀብት ምርኮ ወደ ሐረር ከተማ ከተመለሰ በኋላ የአዳል ታላላቅ ኤሚሮችና የሃይማኖት መሪዎች ከሱልጣን ኦማርዲን ጋር በተሰበሰቡበት ጉባኤ ጥንታዊ የሱልጣኖችን ከባድ የግብር ሥርዓትና አገልግሎት በብርቱ ሂስ ነቅፎ ለወደፊቱ ለመንግሥትና ለጦር መሣሪያ የሚያስፈልገው ወጭ ከዘመቻ በሚገኘው ምርኮ እንዲሸፍን ከአገሬው ሕዝብ የሚሰበሰበው የግብር ሀብት ደግሞ ለሕብረተሰቡ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ አገልግሎቶች እንዲውል በሥልጣኑ መወሰኑን ባስታወቃቸው ጊዜ ፊውዳ

[16] *Ibid.*, pp. 14-15.
[17] *Ibid.*, p. 33
[18] *Ibid.*
[19] *Ibid.*, p. 149.



ላዊ የአዳል የገዥ መደብ መሪዎችና አባሎች በፍርሃት መንፈስ የኢማሙን ውሳኔ እንደሚቀበሉ በጉባኤው አረጋገጡ ።[20]

ነገር ግን ኢማም አህመድ ግራኙ በሐረር ከተማ ለአዳሉ የዋለስማ ጥንታዊ የገዥ መደብ አዲሱን የምርኮና የግብር ፖሊሲ በይፋ አስታውቆ ዘርባህ በሚባል በሀርላ አገር በሀርላና በሶማሌ ማህበረሰቦች መካከል ለነበረው ግጭት የሰላም መፍትሔ ለማስገኘትና በአጼ ልብነ ድንግል ማዕከላዊ መንግሥት ላይ ለሚያካሂደው አዲስ ዘመቻ የወታደሮች ምልመላ ለማድረግ ከጥቂት ፈረሰኛ ተከታዮች ጋር ወደ ገጠር ከሄደ በኋላ ዋዚር ኑር ፡ ገራድ አህሙሽ ፡ አውራይ አቡን ፡ የሁባቱ ቃዲ አቡበከር ፡ የሕግ ምሁር አህመድ ጨምሮ ብዙ የዋለስማ ፊውዳል መሳፍንቶች ፡ መኳንንቶች ፡ ኤሚሮችና የሃይማኖት መሪዎች በሱልጣን ኦማርዲን መሪነት ተሰብስበው በአዳል አገር ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ጥንታዊ የግብር ሥርዓት በሥልጣኑ ሽሮአል በማለት በሐረር ከተማ ለዘመቻ የሰበሰበውን ሀብትና የጦር መሣሪያ ዘርፈው ኢማሙን ከሥልጣኑ አውርደነዋል የሚል የአመጽ ውሳኔአቸውን በነበረበት አገር በቀጥታ ለራሱ በደብዳቤ ገለጹለት ። [21]

ኢማም አህመድ ግራኙም የኩዴታውን ዜና ለአመጸኛ ደጋፊዎቹና ተከታዮቹ በዘርባህ ቀበሌ በአሳወቃቸው ጊዜ ፡ ኤሚር ሁሴን ፡ ኤሚር ዓሊ ፡ አውራይ አህመዲን ፡ ገራድ ዘሀርቡይ ፡ ገራድ አብድናስር ፡ ገራድ አብድ ፡ አውራይ ግቡይ ፡ ቴዎድሮስ አደም ጨምሮ ብዙ የአዳል አመጽ መሪዎችና አዝማቾች በኢማሙ ጉን ተሰልፈው በመደባዊ የኃይል ሚዛን የሱልጣን ኦማርዲንን የቅልበሳ ሴራ በቁጥጥር ሥር አደረጉ ። ከዚያ በኋላ በኢትዮጵያ የአካባቢው ሱልጣንና የማዕከላዊ አጼ ሥርዓት ላይ አገር አቀፍ የአመጽ ዘመቻቸውን የበለጠ አጠናክረው ቀጠሉ ።

[20] *Ibid.*, p. 148.
[21] *Ibid.*, p. 149.

## የአህመድ ግራኙ ጉሳና የጦር ድርጅት ፤

የአህመድ ግራኙን ጉሳና አመጣጥ በሚመለከት ፣ ድርሳነ ራጉኤል [1] በጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የተጻፈው የምኒልክ ዜና መዋዕል [2] ፣ በቅርቡ የግራኝ አህመድ ወረራ [3] በሚል ርዕስ የተጻፈው የአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ መጽሐፍና በአረብ ፋቂህ የተጻፈው የራሱ የኢማሙ ዜና መዋዕል [4] እስከ ዛሬ ድረስ የታወቁ አራት የታሪክ ምንጮች ናቸው ።

በድርሳነ ራጉኤል መሠረት ፣ የግራኙ እናት አዳላዊት ሴት ስትሆን አባቱ ከአዳላዊት እስላም ሴት ጋር ግብረ ሥጋ በመፈጸሙ ገና ግራኙ ከመወለዱ በፊት በደብረ ሊባኖስ ካህናት የተገደለ አንድ የገዳሙ መነኩሴ ነበር ። በተጨማሪም በድርሳነ ራጉኤል ቃል ፣ እግዚአብሔር አህመድ ግራኙን በአጼ ልብነ ድንግል ላይ ለቅጣት ያስነሳበት ምክንያት ፣ አጼው የክርስትና እምነትና ትምህርት ተላልፎ " የጋላ " አዋግዊ ባህልና ሥርዓት በመከተሉ ነበር ይላል ። [5]

በዘመነ ልብነ ድንግል " የጋላ " ወይም የኦሮሞ ሕዝብና የተባለው አዋግዊ ባህል በኢትዮጵያ የአጼው መንግሥት ግዛት ክልል ገና አልታወቀም ነበር ። በመሆኑም የድርሳነ ራጉኤል አባባል በሥፍራና ጊዜ ያልተያያዘና የማይያያዝ በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት በአገሪቱ በቅደም ተከተል የተፈጸመውን የአህመድ ግራኙንና የኦሮሞ ፍለሳን ታሪክ አስመስለው ለመግለጽ የቤት ክርስቲያን ጸሐፊዎች ከጊዜ በኋላ የፈጠሩት ሲሆን ፣ በኋላም አጼ ምኒልክ ዜና መዋዕል በጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በአዲስ ቅርጽና ትርጉም የሰፈረውም ያው የድርሳነ ራጉኤል አሳብ ነው ።

አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በኢትዮጵያ የስርወ መንግሥታትና ነገሥታት ታሪክ ትንተናቸው ፣

" አጼ ይኩኖ አምላክ በአግራ ዘር እየተረዳ በአቡነ ተክለ ሃይማኖትና በአባ ኢየሱስሞዓ እየተደገፈ ከዛጉዬዎች ተረክቦ የመሠረተውን ፣ እነአጼ ሠይፈ አርእድ እነ አጼ ዓምደ ጽዮን የገነቡትን ፣ እነ አጼ ዳዊት እነ አጼ ያዕቆብ የጣራውን ውቅር አሳምረው የከደኑትን ፣ ብዙ የአግራ የትግሬ የአገው የጸለምት - የዳሞት የባሌ የደዋሮ የፈጠጋር የይፋት የእንጎት መኳንንትና ሕዝብ ሊታወጉትና መነኮሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት የማዕዘን ድንጊያም አሸዋና ሲሚንቶም ሆነው ሁሉም በየበኩሉ ድርሻውን በማበርከት ያጸኑትን ያጼ ልብነ ድንግልን መንግሥት ለማፈራረስ የቻለው የግራኝ አህመድ አገሩ ወረዳው ጉሳውና ትውልድ ከወዴት ነው ? " [6] የሚለውን ጥያቄ አቅርበው የሚከተለውን የራሳቸውን የመልስ ፣ አሳብ ሰንዝረዋል ።

ለጥያቄያቸው መልስ አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በሐረር ከተማ ከአቶ አህመድ ዓሊ ሻሚ በደብዳቤ በተሰጣቸው ትውፊታዊ አስተያየት ላይ የራሳቸውን ትርጉም ጨምረውበት " ግራኝ አህመድ ባባቱ በኢብራሂም የሐዊያ ሱማሌ ተወላጅ በሌላው ወገን (ምናልባት በናቱ) ሐረርጌን ካቀኑት ከሐርላህ የሱማሌ ነገዶች በተለይ በአርበኝነት ከታወቁት ከመለሳዮች ወገን ነው ብለን አሳባችንን በዚህ ላይ እናቆማለን " [7] ብሎአል ።

ነገር ግን በሰነድ የታወቀው የዘመኑ የአዳል ታሪክ ይዘትና ሂደት አመጸኛው ኢማም አህመድ ግራኙ በጉሳውና በትውልዱ የሐዊያና "የመለሳይ " ሶማሌዎች ወገን ነበር የሚለውን የአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያን የመደምደሚያ ትችቶች አይደግፍም ።

ምክንያቱም አንደኛ ፣ በዘመኑ በታላቁ የአዳል አካባቢ መንግሥት ሥር የሶማሌ ዘላን ጉሳዎች በአመዛኙ ገና ወደ እስልምና ሃይማኖትና ባህል ያልገቡ ወይም በመግባት ሂደት ላይ የነበሩ አዋግውያን ብቻ ሳይሆኑ በመጀመሪያ ከ1524 ገደማ እስከ 1527 ድረስ በግድ ምልመላ በአዳሉ ሱልጣን አቡበከር ወገን ተሰልፈው አመጸኛ ኢማም አህመድ ግራኙን ለመግደል ብዙ ያልተሳኩ ሙከራዎችን ያደረጉ ፣ [8] በመጨረሻ ደግሞ ኢማሙ ሱልጣኑን ከገደለው በኋላ እንደሌላው የአካባቢው ሕዝቦች ሁሉ በመሣሪያ ተገደው በአገሪቱ ማዕከላዊ የአጼ ንጉሥና ሠራዊት ላይ በኢማሙ ወገን በግድ የተሰለፉ አረብ ፋቂህ " ወምበዴና ቀማኛ " የሚላቸው እንደነበሩ ይታወሳል ። [9] ባጭሩ በዘመኑ ዘወትር ከሀርላ ጉረቤቶችና እርስ በርሳቸው ይዋጉ የነበሩ የሶማሌ ዘላን ጉሳዎች በማህበራዊ የዕድገት ደረጃና በድርጅታዊ ሃይማኖት ልምድ ኢማም አህመድ ግራኙን

---

1 እንድሬ ካኮ ፤ " ድርሳነ ራጉኤል " ፤ *AE*, Vol. 2 (11957), pp. 91-122; እንድሬ ካኮ ፤ " የግራኝና የጋሎች ታሪክ በአማርኛ ጽንጽ " *AE*, Vol. 2 (1957), pp. 123-143.

2 ገብረ ሥላሴ ፤ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ (1959) [illegible]

3 ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ ፤ የግራኝ አህመድ ወረራ (1966) ፤ ገጽ 166-176.

4 Arab-Faqih, *Conquete*, pp. 10.255.

5 እንድሬ ካኮ ፤ " የግራኝና የጋሎች ታሪክ " ፤ ገጽ 129-132.

6 ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ ፤ የግራኝ አህመድ ወረራ ገጽ 174 ።

7 *Ibid.*, p. 177. 208. 219.

8 Arab-Faqih, *Conquets*, pp. 14-15, 20-25.

9 *Ibid.*, pp. 14-15,44-46,149.

የሚያከል ታላቅ የሃይማኖት ፤ የጦርና የሕዝብ መሪና አስተማሪ የሚፈ ጥር የኢኮኖሚ ፤ የድርጅትና የባህል መሠረትና መግሪያ ገና አልነበራቸ ውም ።

ሁለተኛ ፤ በአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በግራኝ አህመድ ወረራ እንደ ተገመተው በአዳል አገርም ሆነ በሶማሌ ማህበረሰብ ዘንድ በተለይ በዘ መኑም ሆነ ከዚያም በኋላ " መለሳይ " የሚባል በራሱ ቋንቋና ሥፍራ የታ ወቀ ልዩ ጐሳ አልነበረም ። በዘመኑ በኢማም አህመድ ግራኙና በአጼ ሠርጸ ድንግል ዜና መዋዕሎች " መለሳይ " በሚል ስም በብዙ ሥፍራዎ ችና ወቅቶች የተገለጹ የጦር ሙያ ሰዎች በአዳል አገር ለግን በገንዘብ ተቀጥረው የሚዋጉ በጦርነት ሙያ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠኑና ልዩ የጦር መግሪያ ማለትም የብረት ጥሩር የነበራቸው በሃይማኖት እስላሞች የነ በሩ የአዳል ምንደኛ ወታደሮች እንደነበሩ በትክክል የታወቀ ነገር ነው ።

በዚህ ረገድ ፤ ለምሳሌ በ1527—1543 የኢማም አህመድ ግራኝ አመጽ የመለሳይ ወታደሮች የኢማሙ ምርጥ የግል ጦር ፤ የክብር ዘበኛ በመሆን ለኢማሙ አገር አቀፍ ድል ወሳኝ አስተዋጽኦ አደረጉ ።[10] እን ዲሁም በ1563—1564 የመለሳይ ምንደኛ ወታደሮች የዙፋን ባላንጣዎ ቹን ደምስሰው ለአጼ ሠርጸ ድንግል (1563—1597) ሥልጣኑን አስያ ዙ ።[11] በ1568 ደግሞ 500 ጥሩር የለበሱ የአዳል ምንደኛ መለሳዮች በሀ ዲያ አመጸኛ ሱልጣን አዜ ወገን ሆነው ከጥቂት ዓመታት በፊት በዙፋኑ ላይ እንዲወጣ የረዱትን አጼ ሠርጸ ድንግልን ወጉት ።[12] በመጋቢት 1577 የአዳል መለሳይ የተባሉ ቅጥር ወታደሮች በአጼ ሠርጸ ድንግል ተገዝተው በዋቢ ጦርነት የራሳቸውን ሱልጣን መሐመድ አራተኛን አሳልፈው ሰጡ ። በታህሳስ 1 ቀን 1578 በሰራዩ ጦርነት[13] በኢትዮጵያ ሠራዊትና በቱርክ ወራሪዎች መካከል በተካሄደው ታላቅ የጨበጣ ጦርነት አሁንም የአዳሉ የመለሳይ ወታደሮችና የጦር አለቆች ከወገን ጦር ጋር ተሰልፈው ከሀጂው ባህረ ነጋሽ ይስሐቅና በቱርክ አዛዥ የተመራውን ወራሪ ጠላት በመደም ሰስ ተግባር ታላቅ ሚና ተጫወቱ ።[14] የአጼ ሠርጸ ድንግል ዜና መዋዕለ ጸሐፊ ወልደ ሃይማኖት ይህን አስመልክቶ እንዳለው ፤

" በዚህ ቀን ጌሉ የተባለው የመለሳዮች አለቃ በመካከላቸው ገብቶ ብዙ ቱርኮችን ከበታተናቸው በኋላ ራሱ ሞተ ። እርሱም በመለሳዮች

[10] *Ibid.*, pp. 84, 111, 130, 185, 207.

[11] Conti Rossini *Sarsa Dengel, part.2*

[12] *Ibid.*

[13] *Ibid.*, part 6.

[14] *Ibid.*, part 7.



ዘንድ በኃይሉና በብርታቱ የታወቀ ሰው ነበር ። ይህ ሰውዬ መጀመሪያ መሐመድን ከድተው ወደ ንጉሡ የገቡ መለሳዮች አለቃ ነበር ። በኋላ ሌሎች የእነርሱን ምሳሌ በመከተል መሐመድ ብቻውን እስኪቀር ትተ ውት ወደ ንጉሡ መጡ ።[15]

ስለዚህ ባጭሩ ፤ በ1527-1543 ለኢማም አህመድ ግራኝ የተዋጉለት ፤ በ1563—64 አጼ ሠርጸ ድንግልን በዙፋን ላይ እንዲወጣ የረዱት፣በሚያ ዝያ 1568 በሀዲያው ሱልጣን ተቀጥረው አጼ ሠርጸ ድንግልን የወጉት ፤ በመጋቢት 1577 በዋቢ ጦርነት የአዳሉን ሱልጣን አሳልፈው ለአጼ ሠር ጸ ድንግል የሰጡት ፤ በመጨረሻም በታህሳስ 1 ቀን 1578 በሰራዩ ታላቅ ጦርነት በአጼ ሠርጸ ድንግል የተመራውን የኢትዮጵያ ሠራዊት ፊታው ራሪ ሆነው በከሀጂው ባህረ ነጋሽ ይስሐቅና በቱርኩ አዛዥ የተመራውን የቱርክ ወራሪ ጠላት በጨበጣ ውጊያ አተራምሰው የሞቱ የምስራቅ ኢትዮጵያ የመለሳይ ወታደሮችና የጦር አለቆች አቶ ተክለ ጻድቅ መኩ ሪያ የግራኝ አህመድ ወረራ በተሰኘው መጽሐፋቸው እንደገመቱት እንድ " መለሳይ " የሚባል የሶማሌ ወይም የሀረሳ ጐሳ አልነበሩም ።

ሦስተኛ በሌላ በኩል የኢማም አህመድ ግራኝ ዜና መዋዕል ጸሐፊ አረብ ፋቂህ እንደጻፈውና የዘመኑን ታሪክ በጥልቀት የመረመሩ ታዋቂ ምሁራንም እንደሚስማሙበት ፤ ኢማም አህመድ ግራኝን ጨምሮ ለረ ጅም ጊዜ በኢትዮጵያ አጼ ነገሥታት ላይ ጦርነት ከአካሄዱ ከአዳሉ ፊው ዳል ኤሚሮች ፤ ገራዶች ፤ አውራዮችና ኢማሞች ብዙዎቹ በታላቁ የሁ ባት ክፍለ ሀገር ከትግሬ—አዳል ጋብቻ ከ1387 እስከ 1527 ድረስ ከአንድ ምዕተ ዓመት በሚበልጥ ዘመን ውስጥ የተፈጠሩት " የበለው " ጦረኛ ጐሳ መሪዎችና አባሎች ነበሩ ።[16]

በአረብ ፋቂህ በተጻፈው የኢማም አህመድ ግራኝ ዜና መዋዕል ቃል ፤ በአዳሉ ሱልጣን በአዳዲን (1387—1415) ዘመን ከሰሜኑ ደጋ " በለው አብደላህ " የሚባል አንድ የትግሬ መስፍን ወደ አዳል ቤተ መንግሥት ገባ ። ሱልጣን ሰአዳዲን ለዚህ ለትግሬ ስደተኛ ልጁን በጋብቻ ሰጠው ። ከዚህ ከትግሬ—አዳል የቤተ መንግሥት ጋብቻ የተፈጠረው አንድ አዲስ የአዳል ጐሳ " በለው " የሚባል ሆነ ። አገሩም በዛሬ ሐረ

[51] *Ibid.* በዚህ ነገር አንድ የአደሬ የሕግ ባለሙያና የቀድሞ ከፍተኛ የመንግሥት ባለ ሥልጣን በግል ውይይት እንዳጫወቱኝ በአደርኛ ቋንቋ "መለሳይ ማለት ጨዋና ታማኝነቱ በዝ ጀግና ሰው እንደማለት ነው ። ኢማም አህመድ ግራኝና ምርጥ የአዳል ወታደሮቹ በእርግጥ እንደ አደሬዎቹ አባባል ጉበዝ ጀግና ፤ ጨዋና ታማኝ ሰዎች ማለትም መለሳዮች ነበሩ ።

[16] Arab-Faqih, *Conquete*, pp. 10, 255, 420-421; Doresse, *Histoire Sommaire* p. 209.

ርና ጅጅጋ ከተሞች መካከል በባቢሌ አካባቢ የሁባት ክፍለ ሀገር ነበር ።
የጉሳውም የወንዱ የግዕረግ ስም " አውራይ " የቤቱ ደግሞ " ቢታህ "
ነበር ።[17]

በዚህ አኳያ በኢትዮጵያ ታሪክ በኋላ እንደ እቴጌ ጣይቱ የጦር ሜዳ
ጀግና የነበረችው የታላቁ ኤሚር ማህፉዝ ልጅና የኢማም አህመድ ግራኝ
ባለቤትና የጦር ሜዳ ጓደኛ የድል ወንበራ ግዕረግ " ባታህ " እንደነበር
ይታወሳል ።[18] በተጨማሪም ወንድ ይሁን ሴት የዚህ የአዳሉ የበለው
ጉሳ አባሎች አንድ የጋራ ጠባያቸውና ሥራቸው በአገሪቱ በመሀል አገር
የቤተ ክርስቲያንና የቄስ ጥላቻ ነበር ። አሁን በሚጠናው ታሪክ ታላቁን
የደብረ ሊባኖስ ገዳም ጨምሮ የዘመኑ ታላላቅ የሸዋና የሰሜን ኢትዮጵያ
ገዳማትን በግምባር እየሄዱ ከዘረፉና ካቃጠሉ ከኢማም አህመድ ግራኝ
ከፍተኛ የጦር መሪዎች አንዳንዶቹ አውራይ አቡበከርን የመሰሉ የጦረ
ኛው የበለው ጉሳ መሪዎችና አባሎች ነበሩ ።[19]

ከትውፊት እንደሚታወቀው ፣ በቀድሞው የኢትዮጵያ ፊውዳላዊ
ዘመንና ሥርዓት በ1524—1543 በኢማም አህመድ ግራኝ መሪነት የተ
ካሄደው የአዳል ኤሚሮች ፣ ነጋዴዎችና ምሁራን የአመጽ ታሪክ በተረት
ሕብረ ቀለም አንድ የፈረሱ ቁመት አርባ ክንድ የሆነ " ግራኝ " የሚባል
" ጭራቅ " ሥራ እንደሆነ ተደርጎ ቀርቧል ። ለዘመኑ ጸሐፊዎችና ሊቃ
ውንት አንድ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ባገር አመጸኛ ተሸነፈ ብሎ
የታሪክ እውነታ መቀበልና ማመን የማይታሰብ ነገር ሆነ ።

በመሆኑም ፣ ኢማም አህመድ ግራኝ የውጭ አገር ዜጋ ነው ፣ የቱ
ርክ ምንደኛ ነው ፣ ሃይማኖታዊ ሥነ ምግባር ያነሰው የአንድ መነኩሴ ልጅ
ነው ፣ "መለሳይ " የሚባል የአንድ ጦረኛ የሶማሌ ጉሳ ተወላጅ ነው
ወዘተ . . . የሚል ተረት በታሪክ ስም ተፈጠረ ። ለሥርዓቱና ለዘመኑ ጸሐ
ፊዎችና ሊቃውንት የአጼው ወታደሮችና የጦር አለቆች የተሸነፉት በቱ
ርክ መሣሪያና ወታደሮች ነበር ብሎ ማመንና ማስተማር ለሕሊናቸው
ሸክም አልሆነም ።

በአንጻሩ ግን በታዋቂው የሕግ ባለሙያ አረብ ፋቂህ የተጻፈው ታላቁ
የኢማም አህመድ ግራኝ ዜና መዋዕል በግልጽ እንደሚያስተምረን ፣የአ
ጼው ጦርና ተከታዮች በመጋቢት 1529 በታላቁ የሹምቡራ ኩሬ ጦር
ሜዳ በሰባት የውጊያ ረድፎች ተመድበው የቀረቡ 216,000 ወታደሮችን

[17] *Ibid., Conquete*, p. 255.

[18] *Ibid.*, pp. 51, 74-75.

[19] *Ibid.*, pp. 181 255, 256



ጨምሮ ፣ በታላላቅ የደዋሮ ፣ የፈጠጋር ፣ የደፋት ፣ የባሌ ፣ የሻርካ ፣ የገ
ንዘ ፣ የከምባታ ፣ የጉራጌ ፣ የዳሞት ፣ የሸዋ ፣ የአግራ ፣ የአንጎት ፣ የትግ
ራይ ፣ የሰራዌ ፣ የበጌምድር ፣ የሰሜን ፣ የደምቢያ ጦር ሜዳዎች የተሸነፉት
ታላላቅ ገዳማትና መቅደሶች የተዘረፉት፣በግሺ አምባም ታላቁ የልዑላንና
የመሳፍንት የግዞት መንደር የፈረሰው በአመዛኙ በኢማሙ አዝማችነት
በአዳሉ ታላላቅ የጦር መሪዎች በከፍተኛ የውጊያ ታክቲክ በተደራጁና
በተመሩ የመለሳይ ፣ የሀርላ ፣ የሶማሌ ወታደሮችና ጥቂት የውጭ አገር
ምንደኞች እጅ ነበር ።[20]

በአጼ ልብነ ድንግል ሠራዊትና የጦር አለቆች ላይ የኢማም አህ
መድ ግራኝ ወታደራዊ ድል ከሁሉ በላይ የኢማሙ ዋዚር አዶሌን፣ ዋዚር
ሞጃሂድን ፣ ገራድ አብድናስርን ፣ ዋዚር አባስ አቡንን ፣ ባታህ ወንበራ
ማህፉዝን . . . ወዘተ የመሳሰሉ ፣ ምናልባትም በአስራ ዘጠነኛውም ምዕተ
ዓመት እነ ራስ ጉበና ዳጨውና እንደ እነራስ አሉላ አባነጋ ያሉ ስመጥር
የጦር መሪዎች እስኪነሱ ድረስ በሰነድ በታወቀው የኢትዮጵያ ታሪክ
ወደር የሌላቸው የአዳል የጦርና የአስተዳደር መሪዎች ሥራ ነው ።

በዚህ አኳያ ፣ በጦርነቱ መጀመሪያ ኢማም አህመድ ግራኝ ራሱ
የቤቱን የሚንቀሳቀስ ዕቃ በሙሉ ከሚስቶቹ ጌጣጌጥ ጋር እየሸጠ ከየአ
ካባቢው በውድም በግድም ለመለመላቸው ወታደሮችና የጦር አለቆች
የጦር መሳሪያ በመግዛትና በማስታጠቅ በራሱ የሚመራ አንድ ጠንካራ
የጦር ሠራዊት አደራጀ ።[21] የኢማሙ ሚስት ባታህ ወንበራ ማህፉዝ በ
ጦር ሠፈር ልጆች እስከትገላገል ድረስ በሴትነት ጾታና ሥራ ተወስና
ከጦር ሠራዊት ሳትለይ ከባልዋ ጋር ልጦሩ በድርጅትና በቅስቀሳ ተግባር
ከፍተኛ የሆነ የአመራር ሚና ተጫውታለች ።[22] የአዳል የሕግና የሃይ
ማኖት ምሁራን ከወታደሮች ጋር በጦር ሜዳዎች ተሰልፈው ታላቅ የቅስ
ቀሳና የፕሮፖጋንዳ ሥራ ሰርተዋል ።

በአረብ ፋቂህ ዘገባ መሠረት ፣ ዋዚር አዶሌ የኢማም አህመድ ግራኝ
አባት ባርያ ነበር ። የኢማሙ አባት ኢብራሂም ከሞተ በኋላ ወጣት ኢማ
ሙን በልጅነቱ ያሳደገው እርሱ ነበር ። ኢማም አህመድ ግራኝ የአገሩን
ሱልጣን ገድሎ የመንግሥት ሥልጣን እንደያዘው እንደ ወላጅ አባቱ ለሚ
ወደውና ለሚታዘዘው አዶሌ በኢትዮጵያ አጼዎች ሹመት እንደ ራስ ግዕ
ረግ የሆነውን የዋዚርነት ሹመትና ግዕረግ ሰጠ ።

[20] *Ibid.*, pp. 67-131.

[21] *Ibid.*, p. 73.

[22] *Ibid.*, pp. 51.

ከ1527 እስከ 1534 ድረስ ዋዚር አዶሌ ለኢማም አህመድ ግራኝ በባዳቂ ፣ በሽምብራ ኩሬ ፣ በአንጾኪያ በአይፈርስና በዛሪ ታላላቅ የጦር ሜዳዎች አከታትሎ የጀብድ ሥራዎችን ሰርቷል ። ታላላቅ የደዋር ፣ የይፋት ፣ የፈጠጋር ፣ የባሌ ፣ የዳሞት የጋፋትና የእናርያ አገሮችንና ሕዝቦችን በኢማም አህመድ ግራኝ ሥልጣን ሥር አውሉአቸዋል ። ከነሐሴ 1531 እስከ የካቲት 1532 ድረስ ለሰባት ወራት ኢማሙ አጼ ልብነ ድንግልን እያባረረ በሰሜኑ ዶጋ በዛሬው ወሎ ዘመቻ ባካሄደበት ጊዜ ዋዚር አዶሌ በደቡብ ኢትዮጵያ የኢማሙ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆኖ አስተዳድሮአል ። በየካቲት 1532 በደብረብርሃን ከተማ በ50 የጦር አለቆች የሚታዘዙ 31,000 ወታደሮችን በታላቅ የድል ሰልፍ አሰልፎ ኢማሙ ከሰሜን ዘመቻ በድል አድራጊነት ሲመለስ የክብር አቀባበል አድርጎለታል ።[23] በሰኔ 1534 ከመሞቱ በፊት ዋዚር አዶሌ በሰሜን በትግራይና በሰራዌ ዘመቻ ካአሂዶአል ።[24]

እንዲሁም የኢማም አህመድ ግራኝ አማች የነበረው ሞጃሂድ ዓሊ ከ1527 እስከ 1540 በባዳቂ ፣ በሽምብራ ኩሬ ፣ በደዋር ፣ በባሌ ፣ በዋጅ ፣ ቢጋሞ ፣ በወላሞ ፣ በበጌምድርና በግሼ እምባ ታላላቅ ዘመቻዎች በአዝማችነትና በፊታውራሪነት ለአዳል ኤሚሮች ፣ ነጋዴዎችና የሃይማኖት መሪዎች አመጽ ድል ወሳኝ አስተዋጽኦ ካደረጉ ሰዎች አንዱ ነበር ።[25]

ከመንግሥትና ከነገሥታት ሀብት ጋር ለአጼ ዙፋን የሥልጣን ባላንጣዎች ለመሆን የሚችሉ ልዑላን ከአገልጋዮቻቸው ጋር በግዞት የሚኖሩበትን የግሼን አምባ መንደር በልዩ ልዩ መንገዶችና መሣሪያዎች ለመስበር ለኢማም አህመድ ከ1531 እስከ 1540 ድረስ ወደ ዘጠኝ ዓመታት ጊዜ ወሰደ ።[26] በመጨረሻ ግን በየካቲት 1540 በዋዚር ሞጃሂድ ዓሊና በገራድ አምዱሽ ማህፉዝ ጥምር አመራር በአምባው የግዞት መንደር የሚኖሩ ከ2000 በላይ ልዑላንና አገልጋዮቻቸው በከፊል ወይም በሙሉ ተገደሉ ። በዘመኑ ዜና መዋዕል እንደተመለከተው በሞጃሂድ—አምዱሽ በተዘረፈው የአምባ መንደር ላይ ፣

“ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ድረስ የተደሙት ነገሥታት ያከማቹት ብዙ ወርቅና የሐር ልብስ ተገኘ ። ሌላውን ሀብት ከእግዚአብሔር ከራሱ በቀር የሚያውቀው የለም ። በዚያን ጊዜ ወርቅ እንደ ደንጊያ የሐር ልብስም እንደቅጠል ረከሰ ። ያንድ ወቄት ወርቅ ዋጋ 30 አሞሌ

[23] *Ibid.*, pp. 278-279, 352-353

[24] *Ibid.*, pp. 442-44.

[25] *Ibid.*, p. 49.

[26] *Ibid.*, pp. 49, 319, 406-409.



ጨው ፣ የአንድ በሬም ዋጋ አንድ ወቄት ወርቅ ሆነ ። በተራራው የሚገኙት እስራኤሎች (ልዑላን ማለቱ ነው) በሰይፍ እየተመቱ ተገደሉ ። የቀሩትም ስለሃይማኖታቸው ወደ ባህር እየተወረወሩ ሞቱ ።[27]

## የአመጹ አገር አቀፍ ሂደትና ስፋት

የኢትዮጵያ የአጼዎችንና የሱልጣኖችን ጦርነት እንዲሁም በአዳል ሱልጣኖችና ኤሚሮች መካከል ለረጅም ዘመን የተካሄደውን የእርስ በርስ የሥልጣን ትግል በሚመለከት ከዚህ በላይ በዝርዝር የተባለው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ በኢትዮጵያ በሁለቱም ማለትም በአካባቢ የአዳል ሱልጣኖችና በአገሪቱ ማዕከላዊ አጼዎች ላይ የ1524—1543 የአዳሉ ኢማም አህመድ ግራኝ የአመጽ ጦርነት ዋናው የወቅቱ ዓለም አቀፍ መነሻ በዘመኑ ከ1498 እስከ 1520ዎቹ ድረስ በአካባቢው በሕንድ ውቅያኖስ ፣ በፋርስ ባህረሰላጤ ፣ በአረቢያና በቀይ ባህር አገሮችና ሕዝቦች ላይ ሁለቱ የፖርቱጋልና የቱርክ ባላንጣ ወራሪዎች የፈጠሩት ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካ ፣ የሃይማኖትና ማህበራዊ ቀውስ ነበር ።

በ1520ዎቹ ፣ በ1530ዎቹና በ1540ዎቹ በአካባቢው በፖርቱጋሎችና በቱርኮች መካከል የተፈጠረው ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጣዊ ጉዳይ ላይ ምን እንዳስከተለ ለማወቅ በቅድሚያ ሁለቱ ኃይሎች በአካባቢ ዓለም ላይ በአጠቃላይ ምን ሁኔታ አስከተሉ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነገር ይሆናል ።

በዚህ አኳያና ወቅት ከ1498 እስከ 1520 ድረስ የፖርቱጋል የባህር ዘራፊ የጦር መርከበኞች በሕንድ ውቅያኖስ ፣ በፋርስ ባህረ ሰላጤ ፣ በአረብ ባህረሰላጤ ፣ በኤደን ባህረሰላጤና በቀይ ባህር ጠረፎችና ወደቦች በኩል ግብጽንና መካከለኛውን ምስራቅ አልፎ ወደ ሜድትራኒያን ባህርና ደቡብ አውሮፓ ይደርስ የነበረውን የምስራቅ ማለትም የእስያ ዓለም አቀፍ የቅመማቅመም ንግድ ምንጭና መስመር በደቡብ ሕንድ ውቅያኖስ ፣ በደቡብ አፍሪካ ጫፍና በምስራቅ አትላንቲክ ውቅያኖስ በኩል አልፎ በምዕራብ አውሮፓ ወደ ፖርቱጋል እንዲደርስ ለማድረግ ባካሄዱት የንግድ ጦርነት በአካባቢው ዓለም አቀፍ የጸጥታ ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቀውስ እንደፈጠሩ አይዘነጋም ።[1] ለምሳሌ በ1507 ብቻ የፖርቱጋል የባህር ዘራፊ የጦር መርከበኞች በፋርስና በአረብ ባህረ ሰላጤ

[27] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ የግራኝ አህመድ ወረራ 1 ገጽ 571

[1] W. Birch, tr. and ed., *The Commentaries of the Great Alfonso Dalvaquerque* 4 vols, (1875-84), I. pp. 43, 71; F.C. Danvers, *The portuguese in India*, 2 vols. (1966), I pp. 65, 74, 78, 114, 118, 122, 133, 178-79; 274-76, 334-46; C.F. Beckingham and G. W. B. Huntingford, trs and eds., *The Prester John of the Indies*, 2 vols. (1961), II, p. 414.

ወደቦች በድምሩ ከ330 በላይ በዓይነትና በመጠን የተለያዩ የንግድ መር ከቦችን በዘረፋና በእሳት ከጥቅም ውጭ አደረጉ ።[2]

ባጭሩ ከ1498 እስከ 1520 ድረስ ሁለቱ ተፋላሚ የፖርቱጋልና የቱ ርክ ወራሪዎች የቀይ ባህር ፣ የአፍሪካ ቀንድ ፣ የአረብ ባህረ ሰላጤ ፣ የፋ ርስ ባህረ ሰላጤና የሕንድ ውቅያኖስ የንግድ ወደቦችንና መርከቦችን ከጥ ቅም ውጭ አደረጉ ።[3] ከዚያ በኋላ በተለይም በአፍሪካ ቀንድ በቀይ ባህር ወደቦችና ደሴቶች ዓለም አቀፍ ንግድ የነበራቸው የኢትዮጵያ ታላላቅ የአዳል ነጋዴዎች በአካባቢው ዓለም እንደዚሁ በፖርቱጋሎችና በቱር ኮች በተፈጠረው ተመሳሳይ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ ከወ ደቁ የአረብ ፣ የቱርክና የፋርስ ምንደኞች ጋር በኢትዮጵያ የኢማም አህ መድ ግራኙን የ1524—1543 የአመጽ ጦርነት በመደገፍ በዘረፋ ዘመቻ ላይ ተሰማሩ ።

በዚህ ረገድ በ1527 ኢማም አህመድ ግራኙ በአጼ ልብነ ድንግል ማዕከላዊ መንግሥትና ሠራዊት ላይ የአመጽ ጦርነት ከመከፈቱ በፊት ከ1524 እስከ 1527 ድረስ በሐረርና በሁባት ክፍለ ሀገራት ከሱልጣን አቡበ ከርና ከሶማሌ ተከታዮች ጋር ሲዋጋ ሳለ[4] በ1524 ገደማ የአጼው የደዋሮ አጐራባች ክፍለ ሀገር ገዥ ፋኑኤል ታላቅ ጦር ይዞ ኢማም አህመድ ግራኙ በነበረበት ሁባት በተባለ አገር ላይ የተለመደውን ወቅታዊ የግብርና የዘ ረፋ ዘመቻ አካሄደ ።[5]

በወቅቱ የአስራ ሰባት ዓመት ወጣት የነበረው ኢማም አህመድ ግራኙ የፋኑኤልን ጦር በውጊያ አሸንፎ ከመለሰ በኋላ በደዋሮ ማለትም በራሱ በፋኑኤል ግዛት ላይ የራሱን የዘረፋ ዘመቻ አካሂዶ ከታላቅ ምርኮ ጋር በድል ወደ አገሩ ተመለሰ ።[6]

ከደዋሮ ዘመቻ በኋላ በ1527 ኢማም አህመድ ግራኙ በተጨማሪም በሐረር ከተማ በግምባር ውጊያ ሱልጣን አቡበክርን ከሶማሌ ተከታዮቹ ጋር ድል አድርጐ በሃያ አንድ ዓመቱ የአዳል አካባቢ መንግሥት ሥል ጣን በኃይሉ ያዘ ።[7]

---

[2] *Ibid.*, Commentaries.

[3] Danverse, *The portuguese in India, J*; Doresse, *Histoire Sommaire*, pp. 215 - 223.

[4] Arab-Faqih, *Conquete*, pp. 14-25.

[5] *Ibid.*, pp. 15-17.

[6] *Ibid.*, pp. 30-32.

[7] *Ibid.*, p. 33.



በዘመኑ በግምት በምስራቅ ከኤደን ባህረ ሰላጤ አንስቶ በምዕራብ እስከ ጨርጨር ደጋና ታችኛው የአዋሽ ሸለቆ ድረስ የአገሪቱ ታላቁ ክፍለ ሀገር ወይም በትክክለኛው አባባል ራስ ገዝ ክልል የነበረውን እስ ትራቴጂያዊ የአዳል አካባቢ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ በኋላ ፣ ኢማም አህመድ ግራኙ ከ1527 እስከ 1535 ድረስ ከሐረር ፣[8] ከደብረ ብርሃን ፣[9] ከዋጅ[10] ከደዋሮና[11] ከአክሱም[12] ተከታታይ ማዕከላት አገር አቀፍ የአመጹን ሂደትና ስፋት በደቡብ ምስራቅ ከዜላ ወደብ ጀምሮ በሰሜን ምዕራብ እስከ ከሰላና[13] ኑቢያ[14] ድረስ በደቡብ ምዕራብ ከጋሞ[15] ደጋ አንስቶ በሰሜን እስከ አማራ ፣ አንጐት ፣ ትግራይ ፣ ሰራዩ ፣[16] ሐማሴን ፣[17] አርኪኮና[18] ዳህላክ[19] ደሴት ድረስ አስፋፋ ።

ከ1535 እስከ 1543[20] ድረስ ኢማም አህመድ ግራኙ በሰሜን ምዕ ራብ በታላቁ ጣና ሐይቅ አጠገብ በፈላሻ አገር ከደምቢያ ጸሚ ማዕከሉ የዛሬ ሦስቱ አጐራባች የኢትዮጵያ ፣ የሶማሊያና የጁቡቲ አገሮች የሚገ ኙበትን የሰሜን ምስራቅ አፍሪካን መለስተኛ አህጉር በአንድ ማዕከላዊ ሱልጣኔት መንግሥትና ሕግ ሥር አድርጐ በየካቲት 1543 በዛሬ ጐንደር ክፍለ ሀገር በደንቀዝ ቀበሌ በተካሄደው ጦርነት ከአጼ ገላውዲዎስና ከፖ ርቱጋል ወታደሮች ጋር የመጨረሻ ጦርነቱን ሲዋጋ ከአንድ የፖርቱጋል ነፍጠኛ ጥይት ተመቶ እስከሞተበት ቀን ድረስ ለስምንት ዓመታት ገዛ ።

ይህ በጥቅሉ የሰፈረው ታሪክ በዝርዝር ሲቀርብ የሚከተለውን ይመ ስላል ። በ1523—1524 አካባቢ ኢማም አህመድ ግራኙ በሁባት የፋኑ ኤልን ጦር አሸንፎ መለሰ።በ1524 በሐረር አካባቢ በሱልጣን አቡበከርና በሶማሌ ተከታዮቹ ላይ የአመጽ ጦርነት ከፈተ ። በ1526—1527 ገደማ ኢማም አህመድ ግራኙ ከሐረር በአጐራባቹ የደዋሮ አገር ባካሄደው ዘመቻ

---

[8] *Ibid.*, pp. 15-353 ( in 1524-1532).

[9] *Ibid.*, pp. 354-360, 401( in 1532, 1533).

[10] *Ibid.*, pp. 366-373, 395 ( in 1532).

[11] *Ibid.*, 373-395 (in 1532).

[12] *Ibid.*, pp. 420-449 ( in 1533-1535).

[13] *Ibid.*, pp. 428-431.

[14] *Ibid.*, pp. 430-440.

[15] *Ibid.*, pp. 396-398.

[16] *Ibid.*, pp. 442-448.

[17] *Ibid.*, pp. 449-450.

[18] *Ibid.*, p. 450.

[19] *Ibid.*, p. 450.

[20] *Ibid.*, pp. 449-468; C. S. Whiteway tr. and ed., *The Portuguese Expedition to Abyssinia in 1541-1543*( (1902).

ተሸንፎ ሲመጣ ከተከታዮቹ ብዙዎች ሞቱበት ። በ1527 ከደዋሮ ዘመቻ መልስ ኢማሙ በሐረር ሱልጣን አቡበክርን በውጊያ ገድሎ የአካባቢ መንግሥት ሥልጣን ያዘ ። በተጨማሪም የአጼ ልብነ ድንግል የጦር አበጋዝ ራስ ደግልሃን በሐረር አካባቢ ያዘመተው ታላቅ ሠራዊት ምርኮ ይዞ ሲመለስ ኢማም አህመድ ግራኙ በክትትል ዘመቻ አሸንፎት በምርኮ የተወሰዱ ወገኖቹን ከእንስሳት ጋር መለሰ ። ከጠላት ወገንም ታላቅ ምርኮ ይዞ በድል ተመለሰ ።

በ1527 ኢማም አህመድ ግራኙ የደገልሃንን ጦር አሸንፎ ከመለሰው በኋላ ከሐረር በምስራቅ እስከ ጠረፍ አካባቢ ድረስ ሂዶ በሶማሌ ወንበዴዎች ላይ የቅጣት እርምጃ ከወሰደባቸው [21] በኋላ በአጼ ልብነ ድንግል ላይ ለሚከፍተው ጦርነት የሶማሌ ወታደሮችንና የጎሳ መሪዎችን በግድ ምልመላ ከሥሩ አሰለፋቸው ። ከዚያ በኋላ በ1527 መጨረሻ ገደማ ኢማም አህመድ ግራኙ በከፍተኛ የጦር መሪዎቹና አዛዦቹ ሥር ተከፍለው የተደራጁ ወታደሮቹን አስከትሎ ከሐረር በደዋሮ ፣ በይፋትና በፈጠጋር አጎራባች የአጼው ታላላቅ ክፍለ ሀገራት ላይ አጭር የወሰን ዘረፋ በማካሄድ ከታላቅ ምርኮ ጋር በድል ወደ ሐረር ተመለሰ ።

በሌላ በኩል አጼ ልብነ ድንግል የኢማሙን የአመጽ ዝግጅት ፣ እንቅስቃሴና ተግባር በፈጠጋር በዛሬው ደብረዘይት—ዱከም አካባቢ በሚኖርበት ሰምቶ ከትግሬ ፣ ከአገው ፣ ከጎጃም ፣ ከበጌምድር ፣ ከአንጎት ፣ ከቂዳ ፣ ከጋን ፣ ከደዋሮ ፣ ከባሌ ፣ ከገንዘ ፣ ከፈጠጋር ፣ ከገደብ ፣ ከአራን ፣ ከማያ ፣ ከዳሞት አገሮችና ሕዝቦች የመከላከያ ሠራዊት ለመመልመልና ለማደራጀት በዛሬው ወሎ ወደ አማራ ክፍለ ሀገር ሄደ ። [22]

ከ1528 እስከ 1529 የኢማሙና የአጼው ሠራዊቶች በፈጠጋር ክፍለ ሀገር በባዳቄና በሽምብራ ኩሬ የጦር ሜዳዎች በጦር ፣ በጋሻ ፣ በጎራዴ በቀስትና በፈረስ ውጊያ በግምባር የተፋለሙበት ኢማሙ በአጼው ላይ ወሰኑን የሽምብራ ኩሬ ድል ያገኘበት ዓመት ነበር ። በዚህ ወቅት በ1528 መጀመሪያ ኢማም አህመድ ግራኙ በ12,500 የሚቆጠሩ የመለሳይ ፣ የሀርላና የሶማሌ ወታደሮችን ከጥቂት የባህር ማዶ ምንደኞች ጋር በአንድ ብርቱ የዘመቻ ሠራዊት አደራጅቶ ለፈጠጋር ጦርነት ከሐረር በክተት ተነሳ ።

በክተቱ ስምሪት ነፍስጡር የነበረችውን ጦረኛ ሚስቱን ባህታ ድል ወንበራ ማህፉዝን ፣ <u>ዋዚሮ</u> አዶሌን ፣ <u>ዋዚር</u> ኑር ኢብራሂምን ፣ <u>ኤሚር</u> ሞጃሂድ ዓሊን ፣ <u>ኤሚር</u> ሁሴን ጋቱርን ፣ <u>ኤማር</u> ዘሀርቡይ መሐ

[21] Arab-Faqih, *Conquete*, pp. 44-46.
[22] *Ibid.*, pp. 77-88.



መድን ፣ <u>ገራድ</u> አብድናስርን ፣ <u>ኤሚር</u> አቡበከር ቀጭኑን ፣ የሀርላ ጎሳ መሪ <u>ሱልጣን</u> መሐመድን ፣ ማታን ኡስማን ፣ ሄራቡ ጎይታና አህመድ ጉራይ የተባሉ የሶማሌ የጎሳ መሪዎችን ፣ ሼክ ደዋድን ፣ የጦር ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ሰባኪ የሕግ ምሁር ሲድ አቡበከርን ጨምሮ ከሀያ በላይ የሚቆጠሩ ከፍተኛ የጦር መሪዎች ፣ አዛዦችና ሰባኪዎች ከኢማሙ ጋር ነበሩ ።

በዘመቻው ጉዞ በሐረርና በአዋሽ መካከል <u>ዚፋህ</u> [23] በሚባል በአንድ የእስላሞች መንደር ጦረኛዋ ባታህ ድል ወንበራ በኢማሙ አህት ሙኒሳህ ዘንድ መሐመድ የሚል ስም የተሰጠውን ሕጻን ተገላገላ ከኋላ ስትቀር ባሏ ግን ከስድስት ቀናት ቆይታ በኋላ ከነሠራዊቱ በዘመቻው ስምሪት ወደፊት በመቀጠል የአዋሽ ወንዝን ተሻግሮ ከከሰም ወንዝ አካባቢ በውስጡ ክርስቲያኖችንና እስላሞች በአንድነት ወደሚኖሩበት አንድ <u>አግ ጃህ</u> [24] ወደሚባል መንደር ደረሰ ።

የአግጃህ እስላሞች ለኤማም አህመድ ግራኙ አማችህ ኤሚር ማህፉዝ ጨምሮ የቀድሞ የአዳል ሱልጣኖችና ኤሚሮች በደንበር ቀበሌዎች ላይ ወቅታዊ የዘረፋ ዘመቻ ከማድረግ አልፈው በአጼው መሀል አገር ጦርነት አካሄደውበት አያውቁም ። አሁን ግን አንተ እስከ አጼው መሀል አገር ገብተህ ጦርነት ከፍተሃልና በእስላሞች ላይ ጥፋት እንዳይደርስ ተጠንቀቅበት በማለት ቢመክሩትም እርሱ ግን ከአመጽ ጦርነቱ ወደ ኋላ መመለስ የማይፈልግ ሆነ ። [25]

የኢማም አህመድ ግራኙ ከነሠራዊቱ ከአግጃህ ወደፊት ፣ በመቀጠል በዱካም አካባቢ ባዶቄ በሚባል መንደር ወደ አጼው ሠፈር በደረሰ ጊዜ፣ ሠፈሩን ቢትወደድ ሰርፃ ፣ ራስ ማህፀንተ ፣ አውራይ ኡትማን (የቀድሞ የአዳል እስላም መስፍን) ፣ የትግሬ ሹም ተክለ ኢየሱስና ጻሕፈላም ሮቤል የሚባሉ አምስት ከፍተኛ መኳንንቶች አሴር ፣ አሮንና ፣ ፍቅረ ኢየሱስ ከሚባሉ ከትግሬ የበታች ሹማምንቶች [26] ጋር ይጠብቁ ነበር ። የባዶቄን መንደርና ቤተ ክርስቲያን በሚጠብቁ የአጼ ሹማምንቶችና በኢማም አህመድ ግራኙ ሠራዊት መካከል ሰመርማ የሚባል በፈረስ የማያሻገር አንድ ጠባብ ወንዝ ነበር ። በተጨማሪም ከአጼው ጦር ጋር በመርዛማ ቀስት ውጊያ ታዋቂ የሆኑ የማያ ወታደሮች ነበሩ ።

[23] *Ibid.*,p.75.
[24] *Ibid.*, p. 96
[25] *Ibid.*
[26] *Ibid.*, pp. 102-104 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፤ ግራኝ ገጽ 212,229

በመስከረም 1528 በአጼውና በኢማሙ ወታደሮች መካከል በሰመርግ[27] ጠባብ ወንዝ ላይ በተካሄደው በባደቄ ጦርነት የኢማሙ ሠራዊት በውጊያው ቦታ ተጽዕኖ ፣ በአጼው ሮቤል ፣ አሴር ፣ አርን ፣ ፍቅረ ኢየሱስና አውራይ ኡትማን በተባሉ ጀግኖች የጀብዱ ሥራና በግያ መርዛግ ቀስት ተሸንፎ ወደ ኋላ ሸሸ ። በዚህ ጊዜ የአጼው ድል አድራጊው ጦር በሚሸሸው የአዳል ሠራዊት ላይ በክትትል የጥቃት እርምጃ ቢወስድበት ኖሮ ምናልባትም ዕለቱ የኢማም አህመድ ግራኝ አመጽ ፍጻሜ ይሆን ነበር ።

የኢማም አህመድ ግራኝ ሠራዊት ከባዶቄ ጦር ሜዳ በሽሽት አምልጦ ወደ አገሩ ሳይመለስ በአካባቢው እየተንቀሳቀሰ ለብዙ ወራት ከተደራጀ በኋላ አፄው ልብነ ድንግል ከመላ ሰሜንና መሀል ክፍለ ሀገራት የተሰበሰቡ 16,000 የፈረስና 200,000 የእግር ወታደሮችን ከ200 በላይ በሚቆጠሩ የጦር መሪዎችና አዛዦች ሥር በሰባት የውጊያ ረድፎች አደራጅቶ የኢማሙን ከጥቂት ምንደኞች ጋር በድምር 12,500 በቀኝ ፣ በግራና በመሀል ማለትም በሦስት የውጊያ ረድፎች የተደራጁ የመለሳይ ፣ የሀርላና የሶማሌ ወታደሮችንና የጦር አዛዦችን በመጋቢት 13 ቀን 1529 በሞጀና በዝቋላ መካከል በሽምብራ ኩሬ ሜዳ ከጥዋት እስከ ቀትር በፈጀ ጦርነት ገጠሟቸው ።[28]

በድምር 228,500 ኢትዮጵያውያን ታላቁን የእርስ በርስ ጦርነት በተዋጉበት በሽምብራ ኩሬ ጦር ሜዳ የአጼው ታላቅ ሠራዊት በድርጅትና በአመራር ጉድለት በኢማሙ ከፍተኛ የውጊያ ስልትና ልምድ በተደራጀ አነስተኛ ሠራዊት ተሸንፎ ተፈታ ። ከዚያ በኋላ አጼው ራሱ በ1540 በትግራይ በደብረ ዳሞ ገዳም እስኪሞት ድረስ ለአሥር ዓመታት ከኢማሙ አዳኝ ወታደሮች እጅ ከቦታ ወደ ቦታ እየሸሸ በስደት የመከራ ሕይወት ኖረ ።

በጦርነቱ ከኢማሙ 12.500 ወታደሮች መሀል 5000 ሲሞቱ ከእነዚህም 3000 የተሰለፉበትን የውጊያ ረድፍ ለቀው በወል የሸሹ የሶማሌ ወታደሮች ነበሩ ።[29] ከአጼው የጦር መሪዎችና አዛዦች 211 ሲሞቱ ከእነዚህም 86 ትግሬዎች ነበሩ ። በጦር ሜዳው የወደቁ የትግሬ ወታደሮች ቁጥር ደግሞ 10,000 እንደነበር ተመልክቷል ።[30]

---

[27] *Ibid.*, *Conquete*, pp. 101-112.

[28] *Ibid.*, pp. 113-131; Dabbatie et Paulitschke, *Futuh*, p. XIX

[29] *Ibid.*,pp.124, 130.

[30] *Ibid.*, p. 130.



ኢማም አህመድ ግራኝ ከሽምብራ ኩሬ በድል ወደ ሐረር ተመልሶ የሦስት ወራት እረፍት አደረገ ። ቀጥሎም በሰኔ—ሐምሌ ወራት በደዋሮ ክፍለ ሀገር እስከ ዋቢ ወንዝ መነሻ ድረስ ዘምቶ የክፍለ ሀገሩን ገዥ ራስ ነቢያትን በግምባር ጦርነት አሸንፎ አባረረው ።[31] ጦረኛው ኢማም ከደዋሮ በድል ወደ ሐረር ከተመለሰ በኋላ በከተማው የአዳል መሳፍንቶች በሱልጣን አማርዲን መሪነት የግብርና የምርኮ ሕጉን በመቃወም የሞከሩበትን የኩዴታ ሴራ አከሸፈ ። በተጨማሪም ከሐረር በደቡብ ምስራቅ በሶማሌ ጐሳዎች ዘንድ ለተፈጠረው የጸጥታ ችግር የመፍትሔ እርምጃ ወሰደ ። ቀጥሎም በዓመቱ መጨረሻ ከደቡብ ምስራቅ በኩል ወደ ባሌ ክፍለሀገር በዘመቻ ገብቶ እንዲሁም የክፍለ ሀገሩን ገዥ ሻንኩርን በውጊያ አሸንፎ አባረረው ። ተክለ ሃይማኖት የሚባለውንም ሌላ ሹም ከነሚስቱ በምርኮ ይዞ ወደ ሐረር ተመለሰ ።[32]

ከባሌ ዘመቻ ወደ ሐረር ከተመለሰ በኋላ ኢማም አህመድ ግራኝ የሁለት ወራት እረፍት አደረገ ። በዚህ ጊዜ ለረጅም ዘመቻ ጦሩን በድርጅትና በመሣሪያ የበለጠ አጠናከረ ። በዚህ ረገድ ሰባት መድፎችን በዜላ በር ከውጭ አስገባ ። በተጨማሪም ሰባ የአረብ ምንደኞችን ቀጠረ ። በዚህ ሁኔታ ሠራዊቱን በመሣሪያና በድርጅት ከአጠናከረው በኋላ ፣ ከ1530 እስከ 1532 ድረስ ኢማም አህመድ ግራኝ በስደት ከቦታ ወደ ቦታ በፈረስ በእግር የሚሸሸውን አጼ ልብነ ድንግልን ለመግደል በእርጐባ ፣ በደዋሮ ፣ በሻርካ ፣ በዋጅ ፣ በገበር ፣ በወርባ ፣ በግያ ፣ በዝቋላ ፣ በፈጠጋር ፣ በዱከም ፣ በዳሞት ፣ በሸዋና በአማራ በሰሜን ምዕራብ እስከ በሽሎ ወንዝ ድረስ ያልተሳካ አገር አቀፍ የዘመቻ እርምጃ ወስዶ በሄደበት አካባቢ ሁሉ በአጼው ጦር ፣ መሳፍንቶች ፣ ሹማምንቶችና የሃይማኖት ድርጅቶች ላይ በተለይ ታላቅ ጥቃትና ጥፋት አደረሰ ።[33]

በዚህ አኳያ በየካቲት 1531[34] በደዋሮ አይፈርስና አንጾኪያ በተባሉ ሁለት የጦር ሜዳዎች በራስ እስላም ሰገድ በአጼው የጦር አበጋዝ በተመሩ 106,000 ወታደሮችና በኢማሙ 10,500 ወታደሮች መካከል በተካሄደው ውጊያ የአጼው ሠራዊት አሁንም በድርጅትና በአመራር ጉድለት ተሸንፎ ተፈታ ።

---

[31] *Ibid.*, pp. 131-147.

[32] *Ibid.*, pp. 155, 159-62.

[33] *Ibid.*, pp. 170-353.

[34] *Ibid.*, p. 185.

በሚያዝያ 1531 አሁንም በደዋር በእንጾኪያ አጠገብ በዛሪ ጦርነት በትግሬ መኳንንት ተክለ ኢየሱስና በራስ እስላም ሰገድ በጋራ የተመራ የአጼው ሌላ ሠራዊት በኢማሙና በዋዚር አዶሉ በተመራ የአዳል ሠራዊት እጅ እንደገና ተሸነፈ ። [35] በዚህ በዛሪ ጦርነት ከሁለቱ የጦር መሪዎች ሌላ ከአጼው ከፍተኛ የጦር አዛዦች 130 እንደሞቱ አረብፋ ቂህ ጨምሮ አስቀምጧል ። [36]

ከዛሪ ጦርነት በኋላ ባለድሉ ኢማም አህመድ ግራኝ እንደቀድሞ ወደ ሐረር መመለስን ትቶ ስደተኛውን አጼ እያባረረ ከነሠራዊቱ በመሀል አገር በግምት በጭላሉ ተራራና በአባይ ወንዝ መካከል በአዋሽ ወንዝ ክልል ዋጅ ገበርጌ ፣ በራራ ፣ ላሊበላ ፈጠጋር ፣ ዱከም ፣ ባዶቄ ፣ እንጦጦ ፣ ሸዋ ፣ ዳሞት ፣ ወዘተ በተባሉ አገሮችና ሥፍራዎች በአጼ ወታደሮች ፣ ሹማምንቶችና የሃይማኖት ድርጅቶች ላይ ታላቅ የጥቃትና የጥፋት እርምጃ መውሰድ ጀመረ ። [37]

አጼ ልብነ ድንግል ኢማሙ ከአንጾኪያ—ዛሩ ጦርነቶች በኋላ እንደበፊቱ ወደ ሐረር ሳይመለስ በተጠቀሱ የአዋሽ አካባቢ አገሮች ላይ የጥቃት ዘመቻ መቀጠሉን ሰምቶ በዋጅ አጠገብ ገበርጌ በተባለው አገር በድብቅ ወደሚኖርበት ቦታ ታዋቂውን የጦር መሪ ራስ ወሰን ሰገድን ከዳሞት ፣ አውራይ ኡትማን ሌላ የጦር አዛዥ ደግሞ ከይፋት ጠራቸው ። [38]

ከፍተኛ መኳንንቶችና ሹማምንቶቹ በተገኙበት ጉባኤ አጼ ልብነ ድንግል ለራስ ወሰን ሰገድ እስላሞች በዘረፋ ጦርነት በአገር ፣ በሕዝብና በሃይማኖት ድርጅቶች ላይ በተለይም በዋጅና በገበርጌ አጠገብ ወረባ በተባለው በአንድ ለምና ሀብታም አገር ላይ ያደረሱትን ታላቅ ጥቃትና ጥፋት ዘርዝሮ አስረዳ ። ራስ ወሰን ሰገድም ለአጼው ፣ ለመኳንንቶችና ለሹማምንቶች በሰጠው ብርቱ ሃይማኖታዊ ሂስ ይህ ዓይነት መከራ በአባቶቻችሁና በቅድመ አያቶቻችሁ ዘመን አልደረሰም ፤ እናንተ በሕዝቡ ላይ በአደረሳችሁት የአስተዳደር በደል ምክንያት እምላክ ያመጣባችሁ ቅጣት ነው ብሎ በቁጣ ሲናገር የተሰበሰቡ መኳንንቶችና ሹማምንቶች አንተ መሪያችን ነህ እንከተልሃለን ከዚህ ታላቅ መከራ አገራችንን ንጉሣችንንና ሃይማኖታችንን አድን በማለት [39] በስሜት ጠየቁት ።

---

[35] *Ibid.*, pp. 195-206.

[36] *Ibid.*, p. 203.

[37] *Ibidi*, pp. 211-220.

[38] *Ibid.*, pp. 213, 221.

[39] *Ibid.*



በተጨማሪም ራስ ወሰን ሰገድ አገሩን በጦር ኃይል ይዞ የመንግሥት ፣ የኢኮኖሚና የሃይማኖት ድርጅቶችን እያቃጠለ ንጉሡን እንደ እውሬ ከቦታ ወደ ቦታ ያባርረው ለነበረው ለኢማም አህመድ ግራኝ ወደ አገርህ ተመለስ ብሎ እንደሚከተለው ደብዳቤ ጻፈለት ።

“ እናንተ እስላሞች ናችሁ ። እኛ ክርስቲያኖች ነን ። ከአሁን በፊት እኛ በአገራችሁ ላይ ዘምተናል ። አገራችሁ ዘርፈናል አቃጥለናል ። አሁን ደግሞ እምላክ ለእናንተ በእኛ ላይ ድል ሰጥቶአችኋል ። ቢሆንም ድል ተለዋዋጭ ነገር ነው ። እስከ ዛሬ የሰራኸው ይበቃሃል ። ወደ አገርህ ተመለስ ። ንጉሡን በሽምብራ ኩሬ ፣ በአንጾኪያና በዛሪ አሸነፍኩ ፣ ሠራዊቱንም ደመሰስኩ በማለት ትመካ ይሆናል ። አትሳሳት ። የንጉሡ ጦር አሁንም ጠንካራ ነው ። አሁንም ንጉሡ ታላቅ ሠራዊት አለው እስከ ዛሬ አንተ ያላየኸውና የማታውቀው የጉራጌ ፣ የጋፋት ፣ የዳሞት ፣ የእናርያ ፣ የኤዝዘይት ፣ የጅማና የመሳሰሉ ብዙ ሕዝቦችና ወታደሮች የንጉሡ አገልጋዮች ናቸው ። በመሆኑም አሁን ከያዝኸው ምርኮና ወርቅ ጋር ወደ አገርህ ተመለስ ። እምቢ ብትል ግን ትዳሚ ቀን እንጋጠማለን ። ታላቅ ወንድምህን ገራድ አቡን ኢብራሂምን የገደልሁ ጦሩንም የደመሰስሁ እኔ ነኝ ። እኔ ወሰን ሰገድ እስከ ዛሬ እንደአሸነፍካቸው ሹማምንቶች አይደለሁም ። [40] በማለት ብርቱ ማስጠንቀቂያ ሰጠው ።

በግንቦት 1531 ኢማም አህመድ ግራኝ በዝቋላ—አዋሽ አጠገብ ተከታዮቹ የአቡኑን ሀብታም ቤተ ክርስቲያን ዘርፈው ባቃጠሉት በረራ ተብሎ በሚጠራ ሥፍራ ታሞ ሳለ የራስ ወሰን ሰገድ መልእክተኛ በዋዚር አዶሌ አቅራቢነት ሕመሙ እንዳይታወቅበት ለታክቲክ የደንብ ልብሱን ለብሶ ከሹማምንቶቹ ጋር በተቀመጠበት ጉባኤ ላይ ደብዳቤውን ለኢማሙ ሰጠ ። በመልክተኛው ፊት የደብዳቤውን ይዘት በጉባኤው ለተቀመጡ ሹማምንቶቹ በይፋ ካስታወቀው በኋላ ፣ ለመልእክተኛው ተመልሰህ ለጌታህ ለራስ ወሰን ሰገድ አድርስለት በማለት በለው አብዱ ፣ ኤሚር ሁሴንና ኢማም አህመድ ግራኝ ራሱ በቅደም ተከተል የሚከተለውን መልስ ሰጡ ። በለው አብዱ የተባለው ጦረኛ ለመልክተኛው ፤ “ ለጌታህ እንዲህ ብለህ ንገረው ። አንተ ራስህ እንደምትገምተው ጀግና ሰው ከሆንክ እኛ በአንተ ምድር በአንተ አገር ነን ፣ ናና እንዋጋ ” በማለት ለግምባር ውጊያ ጋበዘው ።

ቀጥሎም ኤሚር ሁሴን ለራስ ወሰን ሰገድ መልእክተኛው ሲናገር ፣ “ ሂድና ለጌታህ ይህን ንገረው ። የቅዳሜን ውጊያ በሚመለከት ፣ በእም

---

[40] *Ibid.*, pp. 222-227.

ላክ ፈቃድ አንተ ራስህ በዚያን ቀን እንደምትገደል ሼኮቻችን አስታውቀውናል ” አለ ። በመጨረሻ ኢማም አህመድ ግራኝ ራሱ ለመልእክተኛው በሰጠው ቃል ፡

“በሚገኝበት ሥፍራ ሁሉ እሱን እየተከታተልን እስከ መጨረሻው እንደምናባርረው ለጌታህ ንገረው ። ወደ አገራችሁ ተመለሱ ያለንን ነገር አንቀበልም ። ጦርነት ምኞታችንም ፍላጐታችንም ነው ። በሌላ በኩል ግን ከእኛ ጋር ቁሞ የሚዋጋ ሰው እስከ ዛሬ አላገኘንም ። አንተም ወንድ ከሆንክ የንጉሡን ሀብት ከእኛ እጅ አድን ። የያዝ ንባችሁን አገር እንለቅም ። . . . ይህንን ሁሉ ሂድና ለጌታህ ንገረው ” [41] በማለት መላ ኢትዮጵያን አንድ የእስላም አገርና መንግሥት አድርጐ መግዛት የጦርነቱ ዓላማ እንደነበር በይፋ ገለጸ ።

ከዚያ በኋላ በግንቦት 9 ቀን 1531 [42] ሕመሙ ተሽሎት ኢማም አህመድ ግራኝ ከበራራ በወረባ በኩል አድርጐ በወቅቱ ከራስ ወሰን ሰገድ ጋር በዳሞት አካባቢ (በዛሬው ጅባትና ሜጫ) በነበረው አጼ ልብነ ድንግል ላይ የማሳደድ ዘመቻውን ሊቀጥል ተነሳ ። ይህን የኢማሙን የክትትል ዘመቻ እንቅስቃሴ ሰምቶ ራስ ወሰን ሰገድ አጼው ወደ ዳሞት ሲሸሽ እርሱ ግን ጦሩን ይዞ ወደ አዳል አገር የሚዘምት አስመስሎ ( ኢማሙ ከዳሞት ወደ እርሱ ግንባር በመመለስ በራሱና በአጼው መካከል ገብቶ እንዲከበብ ለማድረግ) ወደ ደዋሮ በኩል ከነጦሩ ተንቀሳቀሰ ። [43]

ነገር ግን የታክቲክ ሰው ኢማም ከሰላዮቹ አስቀድሞ በአገኘው መረጃ መሠረት የራስ ወሰን ሰገድ የደዋሮ—አዳል እንቅስቃሴ የእርሱን የዳሞት — አቅጣጫ ዘመቻ ወደ ኋላ ለመመለስ የታሰበ ነገር መሆኑን ደረሰበት ። በመሆኑም ወደፊት በመቀጠል በሰኔ1531 መጨረሻ ገደማ በዳሞት ዙሪያው በግንድና በእሾህ በታጠረና “ የዝሆን ዱር ” ተብሎ በሚታወቀው ባለሶስት በር ምሽግ ውስጥ በተደበቀው አጼ ላይ ያልተሳካ ጦርነት ከፍቶ ብዙ የጦር ሹማምንቱን ሲገድል አጼው ራሱ ግን በአንድ ጠባብ መውጫ በር አምልጦ ከጦር አዛዡ አውራይ ኡትማን የይፋት ገዥ ጋር በሽሽት ወደ ገበርጌ ሄደ ። [44]

ከዝሆንዱር ጦርነት በኋላ በሐምሌ ወር ኢማሙ የጦር ከፍተኛ ሹማምንቶቹን ቡድን በቡድን እየላከ በበራራ ፡ በግራርያ ፡ በእንደገብጠን ፡

[41] *Ibid.*, pp. 228-229.

[42] *Ibid.*, p. 231.

[43] *Ibid.*, p. 234.

[44] *Ibid.*, pp. 237-240.



በሸዋና በፈጠጋር የደብረ ሊባኖስ ገዳምና የባዳቂ “ ቤተ መንግሥት ” ሀብት ጨምሮ የቤተ ክርስቲያንና የቤተ መንግሥት ሀብትና ንብረት ዘረፋ አካሄደ ።

በዚህ አኳያ ፡ በታሪክና በመንፈሳዊ አገልግሎት በአገሪቱ ከአክሱምና ከላሊበላ ታላላቅ ገዳማት ጋር የሚቆጠረውን የደብረ ሊባኖስን ገዳም ለማስዘረፍ ኢማም አህመድ ግራኝ በሐምሌ 1531 በኤሚር አቡበከር ቀጭኑ መሪነት ኤሚርሞጃሂድ ፡ አብሳግኑርንና ድልሰገድን የመሳሰሉ ታዋቂ የጦር አበጋዞችን ጨምሮ 300 ፈረሰኛ ወታደሮች የሚገኙበትን አንድ የዘረፋ ግብረ ኃይል ከበራራ በስድስት ቀናት ጉዞ ወደ ግራርያ (የዛሬ ሰላሌ) አዘመተ ። [45] የገዳሙ መነኩሴዎች ብዙ ሀብት ሰጥተው ገዳሙ እንዳይቃጠልባቸው ከኤሚር አቡበከር ቀጭኑ ጋር ሲደረድሩ ሳለ አውራይ አቡበከር የሚባል አንድ የአዳሉ ጦረኛው የበለው ጕሳ አባል የተጀመረውን የሰላም ድርድሩን በመቃወም በታላቁ ገዳም ላይ በድንገት እሳት በለኮሰበት ጊዜ ብዙ መነኩሴዎች በፈቃዳቸው እየሮጡ ከገዳሙ እሳት ውስጥ ገብተው ተቃጠሉ ። [46]

በሌላ በኩል አጼ ልብነ ድንግል ከዝሆንዱር ጦርነት አምልጦ ከጦር አዛዡ አውራይ ኡትማን ጋር መጀመሪያ ወደ ገበርጌ ቀጥሎም ወደ ዋጅ ሸሽቶ ከራስ ወሰን ሰገድ ጋር ተገናኘ ። በዚህ ወቅት በሐምሌ 1531 ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ጊዜና ሁኔታ በትክክል ያልተገለጸ አርባ ፈረንጆች በዋጅ አገር ከአጼው ጋር ነበሩ ። [47]

በሐምሌ 1531 የኢማሙ ሠራዊት በእንደገበጠን ፡ በግራርያ ፡ በበራራ ፡ በፈጠጋርና በሸዋ ቀበሌዎች በቤት ክርስቲያን ፡ በመንግሥትና በኢኮኖሚ ድርጅቶች ላይ የከፈተውን የጥፋት ዘመቻ አጼው ከራስ ወሰን ሰገድና ከአውራይ ኡትማን ጋር በዋጅ አገር ሰምቶ በራስ ወሰን ሰገድ መሪነት የደዋሮ ፡ የጉጃም ፡ የፈጠጋርና የይፋት ወታደሮችንና የጦር አዛዦችን በኢማሙ ላይ ለማዝመት ወሰነ ።

በመሆኑም የራስ ወሰን ሰገድ ሠራዊት ከአጼው ጋር የነበሩ አውሮፓውያን በሰሩት ጀልባዎችና በባህላዊ 500 የዋና ስልቻዎች ከዋጅ የአዋሽ ወንዝ ተሻግሮ በወረባ በኩል ወደ ፈጠጋር ገባ ። [48] ነገር ግን በነሐሴ 1531 በፈጠጋር በቦሳት (በዛሬው ቦሳት ወረዳ) በራስ ወሰን ሰገድና በኢ

[45] *Ibid.*, pp. 246-250.

[46] *Ibid.*, pp. 250-256.

[47] *Ibid.*, p. 251.

[48] *Ibid.*, p. 252.

ግሙ ሠራዊቶች መካከል በተካሄደው ጦርነት ራስ ወሰን ሰገድ በጨበጣ ውጊያ በአንድ ገራድ አብድ በተባለ የአዳል ጦረኛ ሰይፍ ተገደለ ። [49]

ራስ ወሰን ሰገድ በገራድ አብድ ከተገደለ በኋላ በአዋሽ ወንዝና በደብረብርሃን መካከል የሚገኙ የይፋት ፣ የፈጠጋር ፣ የሸዋ የበራራ የወረባ ነባር ሕዝቦች በመደዳ ሰለሙ ። ድል አድራጊው ኢማም አህመድ ግራኝ በእነዚህ አገሮች ሹማምንቶችና የጦር አለቆቹን ሾመ ። [50] በሹማምንቶቹም ላይ ዋዚር አዶሴን እንደራሴው አድርጐ ሾመው ። [51] ከአገሩ በምርኮ ተወስዶ ክርስትና ከመነሳቱ በፊት የአዳል መሳፍንት ወገን የነበረው አውራይ ኡትማን የአጼው የይፋት ገዥና የጦር አዛዥ ከራስ ወሰን ሰገድ ሞት በኋላ ከነጦሩ በድምር በ20,000 የሚቆጠሩ ተከታዮቹን ይዞ ወደ ኢማሙ ገባ ። [52]

በሌላ በኩል በነሐሴ 1531 ራስ ወሰን ሰገድ በቦሳት በተገደለ ጊዜ በዙፋን ስሙ ወናግ ሰገድ የተባለው አጼ ልብነ ድንግል ከቤተ መንግሥት ሹማምንቶቹ ጋር በዋጅ ነበር ። [53] የራስ ወሰን ሰገድን ሞት ፣ የጦር ሠራዊቱን በአዳሎች እጅ መፈታት ፣ የሕዝቦቹን መስለምና የአውራይ ኡትማንንም ከነጦሩ ወደ ኢማሙ መግባት ከሰማ በኋላ መላ ደቡብ ኢትዮጵያን ለኢማሙ ትቶ በሰሜኑ ደጋ ወደ ቤተ አማራ ማለትም ወደ ዛሬው ወሎ በሽሽት ለመሄድ ተነሳ ።

አረብፋቂህ እንዳስቀመጠው ፣ በነሐሴ 1531 መጨረሻ ገደማ ፣"ንጉሥ ወናግ ሰገድ የክረምቱን ወራት በዋጅ ያሳልፍ ነበር ። በዋጅ እንደ ነበር የወሰን ሰገድን ሞትና የጦሩንም መፈታት ሰምቶ እጅግ በጣም አዘነ ። የጦር አዛዦቹን ፣ ቤተሰቦቹንና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖቹንም ሰብስቦ " አሁን ምን እናድርግ ? ምን ምክር ትሰጡኛላችሁ ? አሁን የትኛው አገር ይቀበለናል " ብሎ ጠየቃቸው ።

" እነርሱም እርስ በርሳቸው ገና ሲነጋገሩ ሳሉ ምክራቸውን ሳይጠብቅ ንጉሡ ራሱ የውሳኔ አሳብ በመስጠት ፤

" ወደ አባቶቻችንና ወደ አያቶቻችን አገር ማለትም የዘውድ ሥርዓት ወደ ተፈጠረበት ወደ ቤተ አምሐራ ሄደን እንቀመጥ ። እዚያ የመግ

[49] *Ibid.*, pp. 262-266.

[50] *Ibid.*, pp. 267-273.

[51] *Ibid.*, pp. 278-279

[52] *Ibid.*, pp. 273-281.

[53] *Ibid.*, p. 281.



ቢያ በሮቹን ዘግተን እስላሞቹን እንከለክላቸዋለን ። አሁን በእስላሞቹ የተያዘውን አገር ትተንላቸው እየተከላከልን በቤተ አምሐራ ለመሞት እንሂድ " [54] ብሎ ንጉሣዊ ውሳኔ አደረገ ።

የአጼ ልብነ ድንግል ሠራዊት በአመጸኛው ኢማም አህመድ ግራኝ ተሸንፎ መፈታትና በነሐሴ 1531 የአጼው ከደቡብ ኢትዮጵያ ወደ ሰሜኑ ደጋ ሸሽቶ መግባት በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ማዕከላዊ የአጼው መንግሥት ሥልጣን መዳከምና የአካባቢ የጦር አበጋዞች ዘመን መጀመሪያ ነበር ። ይህ በአጼ ልብነ ድንግልና በኢማም አህመድ ግራኝ መካከል የተከሰተው የደከመ ማዕከላዊው አጼና ጠንካራ የአካባቢው ጦር አበጋዝ ግንኙነት በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት እስከ አጼ ነገሥታት ቴዎድሮስ ዮሐንስና ምኒልክ ዘመን ድረስ በመቀጠል የኢትዮጵያን የማህበራዊ ሥርዓት ዕድገት ለምዕተ ዓመታት ወደ ኋላ እንደሚያስቀረው በዚህ ጥናት ከዚህ በታች አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ይገለጻል ።

በ1531 ወደ አጼ ልብነ ድንግል ሽሽትና የኢማም አህመድ ግራኝ የክትትል ዘመቻ ሁኔታ እንደገና ስንመለስ ፣ አጼው ከነ ንጉሣዊ ቤተሰቡና ተከታዮቹ ጋር ከደቡብ ሸሽቶ በቤተ አምሐራ ወደ እስትራቴጂያዊው ዋስል አምባ ከገባ በኋላ የአዳሉ የክትትል ጦር በኢማሙ መሪነት በድንገት ደርሶበት በጥቅምት መጨረሻ በአምባው ላይ በአጼውና በኢማሙ ተከታዮች መካከል በተካሄደው ጦርነት አሁንም የኢማሙ ወገን አሸነፈ ። [55] አጼው አሁንም እጫካ ውስጥ ገብቶ ከጠላቱ እጅ ለትንሽ አመለጠ ። [56] በማታው ጨለማ በውጊያ ወቅት ከተደበቀበት ጫካ ወጥቶ ሄደ ።

በዘመኑ በቤተ አምሐራ የታወቁ የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ድርጅቶች የመካነ ሥላሴ ፣ የአትሮንስ ማርያም ፣ የደብረ ነጐድጓድ ፣ የቤተ ሰማያት ፣ የገነተ ጊዮርጊስ ፣ የደብረ እግዚአብሔርና የደብረ እስጢፋኖስ ታላላቅ ቤተ ክርስቲያኖችና ልዑላን በግዞት [57] የሚኖሩበት የግሼን አምባ [58] መንደር ነበሩ ። በ1531 በዚህ የግዞት መንደር ከ100 በሚበልጡ ቤቶች 2,300 ልዑላንና አገልጋዮች ነበሩ ። [59] አጼው ከዋ

[54] *Ibid.*

[55] Dabbadie et paulitske, *Tutuh*, p. XX.

[56] Arab-Faqih, *Conquete*, pp. 303-305.

[57] *Ibid.*, pp. 303-326, 331-337.

[58] *Ibid.*, pp. 319-325.

[59] *Ibid.*, p. 314.

ስል ጦር ሜዳ ካመለጠ በኋላ በህዳርና በታህሳስ 1531 የኢማሙ ወታደሮች በእነዚህ ታላላቅ ገዳማት ለምዕተ ዓመታት በነገሥታትና በካህናት ከተሰበሰቡ ውድ የወርቅ ፣ የብርና የሀር ዕቃዎች የቻሉትን ያህል ዘርፈው ከደብረ እስጢፋኖስ ገዳም በስተቀር ሁሉንም ገዳማት ከነሀብታቸው ጋር አቃጠሉ ።

ከተጠቀሱ የቤተ ክርስቲያን ድርጅቶች መሀል የመካነ ሥላሴ ገዳም ስፋት ቁመት 150 ክንድ ጐን 100 ክንድ የመዝጊያው ቁመት 10 ክንድ ጐኑ 4 ክንድ ሲሆን ውስጡ ደግሞ በወርቅ ያጌጠ ነበር ። በራሱ በኢማም አህመድ ግራኙ ቁጥጥር 1000 የሚሆኑ ወታደሮች የገዳሙን የወርቅ ጌጣጌጥ ከግድግዳና ከጣሪያው በመጥረቢያ እያነሱ ለግማሽ ቀን ከዘረፉ በኋላ የቀረውን ከነገዳሙ አቃጠሉ ።[60] ከደብረ እግዚአብሔር ጥንታዊ ገዳም በተዘረፉ ዕቃዎች ውስጥ ደግሞ 909,999[61] ወቄት የሚመዝን አንድ ከወርቅ የተሠራ ጥፍጥፍ ዕቃ ተገኘ ።

ነገር ግን በተፈጥሮ አቀማመጡ ሁኔታና በታዋቂ የትግሬ ቀስተኞች ብርታት የአዳልና የአረብ ዘራፊዎች በህዳር 1531 ታላቁን የግሼን አምባ መንደር ለመያዝ ያደረጉት ከባድ ጥረት ከሸፈ ።[62] ወደ አምባው መንደር ከሄደው ቡድን መሪዎች አንዱ ገራድ አህሙሽ በምርኮ ተወስዶ በኰብላዩ አጼ ትእዛዝ በአካባቢው ተገደለ ። እንዲሁም በነሐሴ ወር አጼውን ከዶ ከነሠራዊቱ ወደ ኢማሙ የገባው አውራይ ኡትማን ከሶማሌ የጐሳ መሪ ገራድ ማታን ጋር በአምባው ጦርነት ተገደለ ።

ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ኢማም አህመድ ግራኙ ከቤተ አምሐራ ገዳማት የዘረፈውን ታላቅ ሀብት ይዞ ወደ ደቡብ በመመለስ በጥር 1532 በደብርሃን ከተማ ከእንደራሴው ከዋዚር አዶሊ ጋር በታላቅ ሰልፍ ተገናኘ ።

ከጥር 1532 እስከ ሚያዝያ 1533 ድረስ ድል አድራጊው ኢማም አህመድ ግራኙ ከደብረብርሃን ከዋጅና ከደዋሮ ጊዜያዊ የዘመቻ ማዕከላት በታላላቅ የጦር መሪዎች በእነዋዚር አዶሌ ፣ በእነ ዋዚር ሞጃሂድ ፣ በእነ ኤሚር ሁሴን በእነ ገራድ አብድ ናስር መሪነትና አዝማችነት በመላው ደቡብ ኢትዮጵያ የሸዋ ፣ የይፋት ፣ የፈጠጋር ፣ የአርጐባ ፣ የማያ ፣ የዋጅ ፣ የደዋሮ ፣ የሻርካ ፣ የባሌ ፣ የሀዲያ ፣ የገንዘ ፣ የከምባታ ፣ የጉራጌ

[60] *Ibid.*, pp. 310-314.

[61] *Ibid.*, p. 330.

[62] *Ibid.*, pp. 319-325.



የወረባ ፣ የገበርጌ ፣ የበራራ ፣ የዳሞት ፣ የጋፋት ፣ የጂማና የእናራ (የእናርያ) ሕዝቦችንና አገሮችን ሙሉ በሙሉ ከሥልጣኑ ስር አደረጋቸው ። ነገር ግን በ1532 በዋዚር ሞጃሂድ መሪነት ወደ ወላሞ—ጋሞ ያዘመተው ጦር ብቻ ተሸንፎ ተመለሰ ።

እነዚህ ነባር የአካባቢ አገሮችና ሕዝቦች ማዕከላዊ የአጼ ወታደሮችን ሹማምንቶችንና ቄሶችን ከመካከላቸው ከአስወገደ በኋላ የኢማም አህመድ ግራኙን የእስላምና ሃይማኖትና ሥልጣን የተቀበሉት ብዙ ተቃውሞ ሳያደርጉ ነበር ። እንዲያውም አንዳንዶቹ ለምሳሌ የሀዲያ ፣ የዳሞት ፣ የጋፋትና የእናርያ መሪዎችና ሰዎች በአጼው ማዕከላዊ ወታደሮችና ሹማምንቶች ላይ ከአዳሎች ጋር የአመጽ ግምባር ፈጠሩ ።

በዚህ ረገድ በ1532 ኢማም አህመድ ግራኙ ሠራዊቱን አስከትሎ በታላላቅ ሐይቆች አካባቢ ወደ ሀዲያ አገር በደረሰ ጊዜ የአገሩ መሪዎች በአጼው ላይ የሚከተለውን መሠረታዊ የሥርዓትና የሃይማኖት ምክንያቶች ደርድረው በትጥቅ ከአዳሎቹ ጋር ተባበሩ ። በአረብፋ ቂህ ቃል ፣ ኢማሙ ከነጦሩ ወደ ሀዲያ አገር ሲገባ ፤

“ የአገሩ መሪ ሊቀበለው መጣ ። እርሱም ለንጉሡ የሚገብር ሆኖ በየዓመቱ ለንጉሡ በክርስትና ሃይማኖት ተጠምቃ ሚስት የምትሆንለት ወጣት ልጅ ይገብር ነበር ። ይኸውም የቆየ ልማዳዊ ግብር መሆኑ ታውቋል ። ይህ የሀዲያ መሪ ከነወታደሮቹ ወደ ኢማም ቀርቦ “ እኔም እስላም ነኝ ፣ ትእዛዛችሁን እፈጽማለሁ ” በማለት ተናገረ ። አህመድም በደህና ተቀበለው ። የሀዲያውም መሪ ለእስላሞቹ የእንግድነት አቀባበል አደረገላቸው ኢማሙም ለሀዲያ መሪና ለተከታዩ ሹማምንቶቹ የክብር ሽልማት ሰጣቸው ። የአገሩም ሕዝብ ብዙ ነው ።

“ ቀጥሎም ኢማሙ ’ እናንተ . . . ለምን በየዓመቱ ለንጉሡ ከልጃገረዶቻችሁ ሁሉ በውበቷና በጠባይዋ የተመረጠችውን ትገብሩለታላችሁ ? ’ በማለት ላቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተለውን መለሱለት ።

“ በጥንት ዘመን ንጉሡ በኃይል ከእነርሱ ስለበለጠ ይህንን ግብር እንዲገብሩ አባቶቻችንን አስገደዳቸው ። እኛም የጦር መሣሪያ ታጥቀን በተጫኑ ፈረስ ላይ እንዳንቀመጥ ተከልክለን እንኖራለን ። በተጨማሪም በየዓመቱ አንዲት ወጣት ልጅ እንድንገብርለት አስገድዶናል ። እኛም እንዳይገለንና መስጊዶቻችንንም እንዳያፈርስብን ፈርተን ወጣት ሴት ልጅ እየገበርን ለመኖር ተገደናል ።

“ ንጉሡ ከግብር ገንዘብ ጋር ልጅቷን የሚረከባት ሰው ሲልክብን እንደሞተች በመቁጠር አካላቷን አጥበን በጨርቅ ከተገነዘችና የሙታን

ቅዳሴ ከተፈጸመላት በኋላ በቃሬዛ ላይ አድርገናት እናስረክባታለን ። አባቶቻችንና አያቶቻችንም ሁሉ እንደዚሁ ያደርጉ ነበር ።

“ አሁን ግን ኃያሉ አምላካችን እናንተን . . አመጣልን ። አስገባሪያችን የነበረውን ንጉሥ አባረራችሁት ። ወታደሮቹንም አጠፋችሁ ። ስለዚህ አሁን ከእናንተ ጋር ተሰልፈን የአምላካችንን ጦርነት እንዋጋለን ። ኃይላቸውን ስለሰበራችሁ ንጉሡና ወታደሮቹ ከዚህ በኋላ ሊያስቃዩን አይችሉም ። ” [63]

በማለት ሀዲያዎች በኢትዮጵያ ማዕከላዊው የአጼ ሥልጣንና ጦር ላይ ከአዳሎች ጋር የአመጽ ግምባር ፈጠሩ ።

ደቡብ ኢትዮጵያን በረጅም ጊዜ ጦርነት በቁጥጥሩ ሥር ካደረገ በኋላ ከሚያዝያ 1533 እስከ ሚያዝያ 1535 ኢማም አህመድ ግራኝ ከደብረ ብርሃን ፣ ከቄዳና ከአክሱም የዘመቻ ማዕከላት በሰሜን የቄዳ ፣ የትግራይ ፣ የሰሐርት ፣ የአበርገሌ ፣ የእንደርታ ፣ የተምቤን ፣ የሽሬ ፣ የአጋሜ ፣ የሰራዬ ፣ የሐማሴንና የድሆኖ ማለትም የአርኪኮ ሕዝቦችንና አገሮችን በሙሉ አስገበረ ። [64] በተጨማሪም በቀይ ባህር የዘመኑ የዳህላክ ደሴት ገዥ የነበረው ሱልጣን አህመድ ኢስማኤልና እንዲሁም በከሰላ አካባቢ በወቅቱ መዘጋ ተብሎ የሚጠራው የቤጃ እስላማዊ አገር መሪ ንጉሥ ሙክታር በየበኩላቸው ለኢማሙ ገበሩ ። [65] ሌላም ኢማም አህመድ ግራኝ ከነሠራዊቱ ወደ ትግራይ በገባ ጊዜ በአክሱም ከተማ የትግሬ እስላሞች በደቡብ ሀዲያዎች እንደአደረጉት ከኢማሙ ጋር ተባበሩ ። [66]

ነገር ግን በሰሜን ማለትም በትግራይ—ሰራዬ ታላቅ የ1534—1535 የአካባቢ ረሀብና ከእሱም ጋር የተያያዘው የሰውና የእንስሳት ወረርሽኝ በሽታ ኢማሙን በትግራይ ፣ በሰራዬ ፣ በሐማሴንና በድሆኖ (አርኪኮ) የአካባቢ እንደራሴዎችን ከሰሩ ሹም የግዛቱን ማዕከል ከአክሱም—ትግራይ በሰሜን ምዕራብ በታላቁ ጣና ሐይቅ አጠገብ በፈላሻ አገር ደምቢያ እንዲያደርግ አስገደደው ። [67]

---

[63] *Ibid.*, pp. 372-373.

[64] *Ibid.*, pp. 409-420, 442-449.

[65] *Ibid.*, pp. 426, 431, 450.

[66] *Ibid.*, pp. 420-421, 424, 456.

[67] *Ibid.*, pp. 449-450.

[68] *Ibid.*, pp. 451-461.



በመሆኑም ከሚያዝያ 1535 ጀምሮ የኢማሙ የጦር አለቆችና አገረ ገዥዎች ከትግራይ ፣ ከሐማሴንና ከሰራዬ በመዘጋ—ወገራ በኩል ወደ ሰሜን ምዕራብ በመሄድ የወገራ ፣ የጸለምት ፣ የሰሜን ፣ የላስታ ፣ የበጌምድርና የደምብያ አገሮችንና ሕዝቦች በጦር ኃይል አስገብረው ያዙ ። [68] በደቡብ የሀዲያ ሰዎች በትግራይ ደግሞ የአክሱም እስላሞች እንዳደረጉት ከአገሪቱ ማዕከላዊ አጼዎች ጋር ለረጅም ዘመን በነበራቸው የሥልጣንና የሃይማኖት ቅራኔ ምክንያት በሰሜን እንዲሁም የፈላሻ ሰዎች ከኢማም አህመድ ግራኝ ጋር ተባበሩ ። [69]

ከ1535 እስከ 1543 ድረስ ለስምንት ዓመታት ደምብያ የኢማም አህመድ ግራኝ የሱልጣኔት መንግሥት የፖለቲካና የሃይማኖት ማዕከል ሆነ ። [70] በዚህ ዘመን በአገሪቱ የአዳል መሪዎችና ወታደራዊ አስተዳዳሪዎች በየአካባቢው ከተሞችና መስጊዶች እያሰሩ የየአካባቢውን ነባር ሕዝብ በእስላም ሃይማኖት ሥር በገባር ሕግና ሥርዓት መግዛት ጀመሩ ።[71]

የገባር ግብርና ሥርዓትን በተመለከተ ለምሳሌ ገና በ1532 በአዋሽ ወንዝ አካባቢ በልማትና በሀብት ታዋቂ የነበረው የወረባ አገር ከገበረለት በኋላ ኢማም አህመድ ግራኝ በአገሩ ገባር ሕዝብ ላይ የወሰነበት የዓመት ግብር ዓይነትና መጠን 15,000 ጭነት ስንዴ ፣ 1000 ወቄት ወርቅና 1000 ጉንዶ ማርና ቅቤ እንደነበር ይታወሳል ። [72]

## የአህመድ ግራኝ ውድቀት ፤

በአረብፋ ቂህ ዘገባ መሠረት ፣ በ1531 በልብነ ድንግል ሠፈር አርባ ፈረንጆች እንደነበሩ ይታወሳል ። ከእነዚህ ፈረንጆች አንዱ በ1526 የፖርቱጋል የልዑካን ቡድን ከስድስት ዓመታት ቆይታ በኋላ ከኢትዮጵያ ወደ አገሩ ሲመለስ በአጼው ቤተ መንግሥት የቀረው የቡድኑ ጠጉር አስተካካይ ቤርሙዲዝ የተባለው ግለሰብ እንደ ነበር ይገመታል ። በመሆኑም በ1535 አጼ ልብነድንግል ቤርሙዴዝን በኢማም አህመድ ግራኝ ላይ ለወታደራዊ እርዳታ ወደ ሮማ ፓፓና ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ ልኮ የአገሪቱን ውስጣዊ የእርስ በርስ ጦርነት ዓለም አቀፍ ጉዳይ በማድረግ ለፖርቱጋሎችና ለቱርኮች ጣልቃ መግባት አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ከፈተ ።

---

[69] *Ibid.*, pp. 456-459.

[70] *Ibid.*, p. 461.

[71] *Ibid.*, pp. 459-461.

[72] *Ibid.*, p. 393.

ቤርሙዴዝ ከኢትዮጵያ በግብፅና በየሩሳሌም በኩል አቋርጦ በየአካባቢው የቱርክ ኬላዎችን በዘዴ በማለፍ መጀመሪያ ወደ ሮም ኢጣሊያ ከዚያም ወደ ሊዝቦን ፖርቱጋል ከፖርቱጋል ደግሞ ወደ ሕንድ አገር ደርሶ በሕንድ ጐአ ከተባለው የፖርቱጋል ኮሎኒ በ1498 ለመጀመሪያ ጊዜ በውቅያኖስ በር ወደ ሕንድ መለስተኛ አህጉር የደረሰው የቨስኮ ዳጋማ ልጅ በክርስቶፍ ዳጋማ (1511—1542) አዝማችነት 400 የፖርቱጋል ነፍጠኞችን አስከትሎ በሐምሌ 1541 ወደ ኢትዮጵያ እስኪመለስ ድረስ ውስብስብ ዓለም አቀፍ ጉዞና ጉዳይ የስድስት ዓመታት ጊዜ ወሰደበት ።[1]

በ1541 ቤርሙዲዝ የፖርቱጋል ነፍጠኞችን አስከትሎ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ኢማም አህመድ ግራኝ ከደምቢያ ማዕከሉ አገሪቱን ሲገዛ፣ በሌላ በኩል ኮብላዩ አጼ ልብነድንግል በነሐሴ 1540 በትግራይ በደብረዳሞ ገዳም ሞቶ በደቡብ ልጁና የዘውድ ወራሹ ጀግናው ገላውዴዎስ (1540—1559) በኢማሙ መንግሥትና ጦር ላይ ጠንካራ የሆነ የደፈጣ ጦርነት እያካሄደ ነበር ።

የፖርቱጋል ጦር ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ፣ በ1541 አጼ ገላውዴዎስ በሰሐርት ትግራይ ከኢማም አህመድ ግራኝ የአካባቢ ጦር ጋር ተጋጥሞ በመሸነፍ መጀመሪያ ወደ ሰሜን አምባ[2] ሸሽቶ ከሰሜን አምባ ደግሞ በዋድላ—በጌምድር—ጐጃም ግንደበረት በኩል የአባይ ወንዝ ሁለት ጊዜ አንዴ ከበጌምድር ወደ ጐጃም አንዴ ከጐጃም ወደ ሸዋ በመሻገር በሸዋ ፣ በይፋት፣በፈጠጋርና በደዋሮ በደፈጣ ታክቲክ እየተንቀሳቀሰ ከኢማሙ የአካባቢ ገዥዎች ጋር በመዋጋት ላይ ነበር ።

በሐምሌ 1541 የፖርቱጋል ነፍጠኞች ከምጽዋ ገብተው በአርኪኮ የኢማም አህመድ ግራኝን ገዥ ገድለው[3] የወደብ ከተማውን ያዙ ። ከዚያ በኋላ ከአጼ ገላውዴዎስ ወኪል ባህረነጋሽ ይስሐቅ ጋር ተገናኝተው በሰራዬ ወደ ደባርዋ ከተማ በመሄድ ከሐምሌ እስከ ታህሳስ 1541 ድረስ ቆዩ[4] በደባርዋ የአጼው እናት እቴጌ ሰብለወንጌል በስደት ከምትኖርበት ከደብረ ዳሞ ገዳም መጥታ ከፖርቱጋል ጦር ጋር ተገናኘች ።[5]

---

[1] ከስታንሆፕ ፣ የፖርቱጋሎች ጀግንነት ፣ ገጽ 11-14፤ ተ.ጸ. መኩሪያ ፣ የግራኝ ወረራ ፣ ገጽ 520 -523 ፣ 603 ።

[2] C.F. Beckingham, "A note on the Topography of Ahmed Gragn's Campaigns in 1542, *Journal of Semitic Stusdies,*" vol. 4 (1955), pp. 362-373.

[3] ተ.ጸ. መኩሪያ ፣ የግራኝ ወረራ ፣ ገጽ 608-610 ።

[4] ከስታንሆፕ ፣ ፖርቱጋሎች ፣ ገጽ 19-21 ፣ 69

[5] *Ibid.*, p. 23.



ፖርቱጋሎችና እቴጌ ሰብለወንጌል ከኢማም አህመድ ግራኝ ጋር በውጊያ ከመጋጠማቸው በፊት በደቡብ ከአጼው ገላውዴዎስ ጋር ለመገናኘት ከደባርዋ በአጋሜ በኩል ጉዞ በመጀመር በየካቲት 1542 በአጋሜ የአምባ ሰነይትን እስትራቴጂያዊ ቦታ ከአዳል ሰፋሪ ጦር በመድፍ ውጊያ አሸንፈው ያዙ ።[6]

በ1541 ክረምት የፖርቱጋል ነፍጠኞች በደባርዋ ሰራዬ በነበሩበት ወራት ኢማም አህመድ ግዳኝ ፣ ከደምብያ በሰሜን ምስራቅ በሰሜን ተራራ የደረሰጌ አዲስ ማዕከል መስርቶ የፖርቱጋል ጦርና እቴጌ ሰብለወንጌል ከሰሜን አልፈው በደቡብ የደፈጣ መከላከል ያካሂድ ከነበረው ከአጼ ገላውዲዎስ ጋር ግምባር እንዳይጥሩበት መሀል ሥፍራ በመያዝ አለያይቶ ሊወጋቸው አዲስ የጦርነት ግምባርና ታክቲክ ቀየሰ ።[7]

በመሆኑም ኢማም አህመድ ግራኝ የፖርቱጋል ጦርን የደቡብ ጉዞ ለማገድ በሚያዝያ 1542 መጀመሪያ ሳምንት ከደረስጌ ሰፈሩ ሄዶ በሰሐርት ትግራይ በከፈተው ጦርነት ሠራዊቱ በፖርቱጋል መድፈኞች ተሸንፎ ሲሸሽ ራሱም ከጦር ሜዳው ገብቶ ሲዋጋ ከጠላት ወገን በተተኮሰ ጥይት በጽኑ ቆስሎ በቃሬዛ ላይ ለትንሽ ከምርኮ አመለጠ ።[8] ከሁለት ሳምንታት በኋላ በሰሐርት የፖርቱጋል ጦር በክትትል በከፈተበት ጦርነት የቁስለኛው ኢማም አህመድ ግራኝ ሠራዊት ከጽኑ ውጊያ በኋላ በመድፍና በጠብመንጃ ሚዛን እንደገና በፖርቱጋሎች ተሸንፎ ሸሸ ።[9]

ከሰሐርት ጦርነቶች በኋላ ቁስለኛው ኢማም አህመድ ግራኝ ከነጦሩ ከአሸንጌ ሐይቅ በስተደቡብ ምስራቅ ወደ ዛቡል ተራራ ሄዶ በአዲስ ሲያደራጅ የፖርቱጋል ጦር ደግሞ ወደ ደቡብ ተጉዞ በአሸንጌ ሐይቅ አጠገብ በወፍላ ሰፍሮ የአጼ ገላውዴዎስን መምጣት ይጠብቅ ጀመር ።[10]

ኢማም አህመድ ግራኝ በሰሐርት ጦርነት በፖርቱጋል ወታደሮች ተሸንፎ በሚያዝያ 1542 ወደ ዛቡል ከሸሸ በኋላ በጦርነቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዛቢድ አረቢያ የቱርክ መንግሥት እንደራሴን የጦር መሣሪያ እርዳታ በይፋ ጠይቆ 900 ነፍጠኞችን ከ10 መድፎች ጋር በግዥ አገኘ ።[11]

---

[6] *Ibid.*, pp. 33-38.

[7] Beckingham,"Topography" pp. 364-365.

[8] ከስታንሆፕ ፣ ፖርቱጋሎች ገጽ 43-45 ።

[9] *Ibid.*, p, 46-47.

[10] *Ibid.*, pp. 48-49.

[11] *Ibid.*, p. 50.

ከዚያ በኋላ በነሐሴ 28 ቀን 1542 ኢማሙ ከዛቡል ከቱርክ ወታደ ሮችና መሣሪያ ጋር በአሸንጌ ሐይቅ አጠገብ በወፍላ ጦርነት የፖርቱጋል ወታደሮችን ገጥሞ ድል አደረጋቸው ። [12] የፖርቱጋል ጦር አዝማች ክር ስቶፍ ዳጋማ በውጊያ ቆስሎ በምርኮ ከተወሰደ በኋላ በኢማሙ ትዕዛዝ ተገደለ ። [13] ከጦር ሜዳው የተረፉ 120 የፖርቱጋል ወታደሮች ግን ከአ ቴጌ ሰብለወንጌል ጋር ወደ ሰሜን ምዕራብ ሸሽተው በመጨረሻ በጥቅ ምት — ህዳር 1542 አካባቢ በሰሜን አምባ ከአጼ ገላውዴዎስ ጋር ተገ ናኙ ። [14] ከወፍላ ድል በኋላ ኢማም አህመድ ግራኝ በጥንቃቄ ጉድለት ለመጨረሻ ጊዜ በራሱ ላይ ጥፋት ወሰነ ። [15]

በዚህ ወቅት ከውጊያ ሜዳ የተረፉት 120ው የፖርቱጋል ወታደሮች አዝማች መሪያቸውን አጥተው ብዙዎቹም ከባድ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸው ሳለ ኢማሙ በክትትል እርምጃ ሁሉን ለማጥፋት ሲችል አመቺ ሁኔታውን አልተጠቀመም። በተጨማሪም የራሱን ነጻ የሆነ የፖሊ ሲና የተግባር እርምጃ በመውሰድ ከቱርክ ባለሥልጣናች ጋር ተጣልቶ ከ200 ግለ ሰቦች በስተቀር ገንዘቡን ከፋፍሎ ሊረዱት የመጡትን የቱርክ ነፍጠኞች በወፍላ ጦርነት ፍጻሜ ወዲያውኑ ከአገር አስወጣቸው ። [16] ከዚህ በኋላ በጊዜያዊ የወፍላ ድል ተዝናንቶ ወደ ደምብያ ሂዶ ተቀ መጠ ። በዚህም ተግባሩ በራሱ ላይ ጥፋት ፈረደ ።

በሌላ በኩል ከወፍላ ጦርነት የተረፉ የፖርቱጋል ወታደሮችና አጼ ገላውዴዎስ በሰሜን አምባ ከተገናኙ በኋላ ከአምባው በአንድነት ሄደው በደምብያ በኢማሙ ላይ ዘመቱ ። በየካቲት 22 ቀን 1543 በጣና ሐይቅ አጠገብ በወይናደጋ ጦርነት በአጼውና በኢማሙ ወታደሮች መካ ከል በተከፈተው ውጊያ ኢማሙ ከአንድ የፖርቱጋል ወታደር በተተኮ ሰው ጥይት ቆስሎ ሞተ ። [17] ጦሩም ተፈታ ። ነገር ግን በኢትዮጵያ ፊው ዳል ነገሥታትና ኤሚሮች መካከል በሃይማኖት ስምና ሽፋን የተጀመረው የሥልጣን ጦርነት በወይናደጋ ጦር ሜዳ ከኢማም አህመድ ኢብራሂም ቤን አልጋዚ ጋር አልሞተም ።

---

[12] *Ibid.*, pp. 53-57.

[13] *Ibid.*, pp. 58-59.

[14] *Ibid.*, pp. 60-63.

[15] Trimingham, *Islam in Ethiopia*, p. 89.

[16] ካስታንያ ፣ ፖርቹጋሎች ፣ ገጽ 59

[17] *Ibid.*, pp. 67, 68.



## የአህመድ ግራኝ አመጽ ውጤቶች

በየካቲት 1543 ኢማም አህመድ ግራኝ በወይናደጋ ጦርነት ሲሞት በሰሜን ጦሩም አብሮ ተፈታ ። ቢሆንም የኢማሙ ጦረኛ ሚስት ቢታህ ድልወንበራ ማህፉዝ የወንድሙ ልጅ ዋዚር አባስ አቡንና የእህቱ ልጅ ኤሚር ኑር ሞጃሂድ ከወይናደጋ ጦርነት አምልጠው በ1559 በዋጅ ጦር ነት አጼ ገላውዴዎስ ራሱ በኤሚር ኑር እስኪገደል ድረስ የኢማሙን የጦርነት ፖሊሲና ተግባር በደቡብ ምስራቅ ቀጠሉ ።

በመሆኑም ድል አድራጊው አጼ ገላውዴዎስ በፖርቱጋል ወታደ ሮች እርዳታ በሰሜንና በመሀል ክፍለ ሀገራት ማዕከላዊ የአጼ መንግ ሥት ሥልጣን በቶሎ ከአረጋገጠ በኋላ የፖለቲካ ማዕከሉን በአንድ በኩል በአዲሱ የአዳል ግፊት ዞን በሌላ በኩል ደግሞ እስካሁን ያልታወቀ የኦሮሞ የፍለሳ እንቅስቃሴ አጠገብና ግምባር በአዋሽ ወንዝና በዝዋይ ሐይቅ መካከል በዋጅ አደረገ ።

ገራድ አቡን ኢብራሂም የኢማም አህመድ ግራኝ ታላቅ ወንድም ከራስ ወሰንሰገድ ጋር ሲዋጋ መሞቱ ይታወሳል ። ልጁ አባስ መጀመሪያ በደቡብ በገራድነት ማዕረግ ፣ በሰሜን ሰራዌ—ሐማሴን አካባቢ ከአስ ገበረው በኋላ ደግሞ በባህረነጋሽነት ማዕረግ እስከ 1534 ድረስ በኢማም አህመድ ግራኝና በዋዚር አዶሌ ጉንና ትእዛዝ በየጊዜው በይፋት ፣ በደ ዋር ፣ በባሌ ፣ በእንጎት ፣ በአምባ ገሼ ፣ በሰራዌና በሐማሴን ጦርነቶችና የጸጥታ ሥራዎች ብዙ ጀብድ የሠራ ጦረኛ ነበር ። [1] በ1534 የኢማሙ እንደራሴና የጦር አበጋዝ ዋዚር አዶሌ በሰራዌ ከሞተ በኋላ ባህረ ነጋሽ አባስ አቡን በዋዚርነት ማዕረግ የአጎቱ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስ ትርና የጦር አበጋዝ ሆኖ ተሾመ ። [2]

አጎቱ ኢማም አህመድ ግራኝ በወይናደጋ ጦርነት ከሞተ በኋላ አጼ ገላውዴዎስ በሰሜንና በመሀል አካባቢዎች የማዕከላዊ መንግሥትን ሥል ጣን መልሶ ለመገንባት ጥረት ሲያደርግ ሳለ ዋዚር አባስ አቡን በደቡብ አጉራባች የደዋር ፣ የባሌና የፈጠጋር ክፍለ ሀገራትን ከአዳል ጋር በጥ ምር ይዞ በመጨረሻ በጥቅምት 1544 በዋጅ ጦርነት ከአጼ ገላውዴዎስ ጋር ሲዋጋ እስኪሞት ድረስ የአጎቱን የጦርነት ፖሊሲና ተግባር ቀጠለ [3] ።

ዋዚር አባስ አቡን ሲሞት የቢታህ ድል ወንበራና የኤሚር ኑር ጥምር አመራር በአዳል ተጀመረ ። በዚህ አኳያ ኢማም አህመድ ግራኝ በወይ ናደጋ ጦርነት ሲሞት ቢታህ ድል ወንበራና ኤሚር ኑር አምልጠው ወደ

---

[1] Arab-Faqih, *Conquete*, pp. 317-318.

[2] *Ibid.*, p. 444.

[3] *Ibid.*, p. 318; *Trimingham, Islam in Ethiopia*, p. 91.

አዳል አገራቸው ተመለሱ ። በወይና ደጋ ኢማሙ ሲሞት በፊት ለኢማሙ ገብር ታማኝ የልጁ ሞግዚትና የአንድ አነስተኛ አካባቢ ገዥ የነበረው የባህረ ነጋሽ ይስሐቅ አባት በልጁ በይስሐቅ ምልጃና አስተባባሪነት የኢማሙን ልጅ አሁን ለአፄ አፄ ገላውዴዎስ በምርኮ አስረክቦ በፊት ከጠላት ጋር በመተባበር ለፈጸመው የክህደት ሥራ ከአጼው ይቅርታ ተደረገለት ። [4]

ከዚህ በፊት ደግሞ በግንቦት 1539 የአጼ ልብነድንግል ልጅ የገላውዴዎስ ወንድም አቤቶ ሚናስ በላስታ ከጦር ሜዳ በአንድ ኤሚር ኡመር በተባለ የጦር አለቃ በምርኮ ተወስዶ በሚያዝያ 1542 እስከ ሰሐርት ጦርነት ድረስ በኢማም አህመድ ሰፈር በእስር ይኖር ነበር ። [5] በሰሐርት ጦርነት ተሸንፎ ወደ ዘቡል ተራራ ከሸሸ በኋላ ኢማም አህመድ ግራኙ አቤቶ ሚናስን ከ100.000 [6] ወቄት ወርቅ ጋር በዛቢጽ አረቢያ ለቱርኩ ሱልጣን እንደራሴ ልኮ በፖርቱጋል ነፍጠኞች ላይ የቱርክ ነፍጠኞችን ድጋፍ አግኝቶ በወፍላ ጦርነት ፖርቱጋሎችን እንደአሸነፋቸው ይታወሳል ።

በወይናደጋ ጦርነት የራሷ ልጅ በምርኮ ሲወሰድ ራሷ ከኤሚር ኑር ጋር አምልጣ ወደ አዳል አገርዋ የገባችው ባታህ ድል ወንበራ በምጽዋና በዛቢጽ የቀይ ባህር ከተሞች በቱርክ ባለሥልጣኖች ምልጃና አስተባባሪነት በሁለቱም ወገን በምርኮ የተያዙትን ልጆቻችንን እንለዋወጥ በማለት ከአቤቶ ሚናስ እናት ከእቴጌ ሰብለወንጌል ጋር በእስታንቡል ወደ ቱርኩ ሱልጣን ዘንድ ደርሶ የተሳካ ፍጻሜ ያገኘውን ዓለም አቀፍ የጦር ምርኮኞች ልውውጥ ዲፕሎማሲና ድርድር ከፈተች ። በሁለቱ ብልህ እናቶች ፖለቲካና ዲፕሎማሲ በመጨረሻ በ1546 የወጣት ምርኮኞች ልውውጥ በሥነ ሥርዓት ተከናወነ ። [7]

ከፖለቲካና ዲፕሎማሲ ወደ ጦርነት ፖሊሲና ተግባር በመመለስ ቀጥሎ የአዳሉ ጦረኛ ባታህ ድልወንበራ ለሟቹ ባሏ እህት ልጅ ለኑር ሞጃሂድ የሐረር ኤሚር (1542—1567) የአጼ ገላውዴዎስን ራስ ቆርጠህ ብታመጣልኝ የሟቹ እጎትህ ወራሽ ባልና መሪ አድርጌ አገባሃለሁ በማለት ለጋቻና ለጦርነት ጋበዘችው ። [8]

---

4 ካስታንሆ ፤ ፖርቱጋሎች ፤ ገጽ 69

5 ተ.ጸ. መኩሪያ ፤ የግራኝ ወረራ ፤ ገጽ 567.

6 *Ibid*., p. 790

7 *Ibid*., p. 792 በዚህ ነገር " እንቺም ልጄን ላኪልኝ እኔም ልጅሽን ልላክልሽ " የሚል መልእክት ድልወንበራ ለእቴጌ ሰብለ ወንጌል በምጽዋ የቱርክ ባለሥልጣኖች አማካይነት እንደላከች በዘመኑ ዜና መዋዕለ ተጽፎአል ) *Ibid*., *p* 791

8 *Ibid*., *p* 815 *Arab-Faqih*, *Conquette p* 51 *note 2*., *E.A.W. Budge*, *Ahistory. of Ethiopia* (1966) *p 352*



በሌላ በኩል አጼ ገላውዴዎስ ከወይናደጋ ጦርነት በኋላ በሰሜንና በመሀል አካባቢዎች የመንግሥቱን የበላይ ሥልጣን ከሞላ ጐደል ካረጋጋ በኋላ ከዋጅ ማዕከሉ ወታደራዊ ትኩረቱን በደቡብና በምስራቅ ግምባሮች በአዳልና በኦሮሞ ግፊቶች ላይ አደረገ ። በተጨማሪም በደቡብና በመሀል ምዕራብ የሀዲያና የዳሞት አገሮችን በድህረ ኢማም አህመድ የማስገበር ዘመቻ አካሄደ ።

በዚህ አኳያ በ1547—1550 አጼ ገላውዲዎስና የጦር አበጋዙ ፋኑኤል በአዳል አገር ከሐረር እስከ አውሳና ዜላ ድረስ በዘመኑ ዜና መዋዕል ቃል "ከባር ሰዓዳዲን እስከ ባር አጀም ድረስ " ማለትም በሰሜን ምስራቅ ከአዋሽ—ዜላ የአዳል አገር ጀምሮ በደቡብ ምስራቅ በሕንድ ውቅያኖስ ጠረፍ እስከ ጥንቱ የአዛኒያ አገር (ባር አጀም) ድረስ ረጅምና ብርቱ የቅጣት ዘመቻ አካሄዱ ። [9]

በ1548—1550 ከደዋሮ—ባሌ የደቡብ ምስራቅ ክፍለ ሀገራት ገዥ ፋኑኤል በአዳል አገር በሐረር በአውሳና በዜላ አካባቢዎች ሁለት ተከታታይ ዘመቻዎችን ባካሄደ ጊዜ በሐረር ከተማ በተለይ በሕይወትና በንብረት ታላቅ ጥፋት አደረሰ ። በዚህ ወቅት የከተማው ገዥ ኤሚር ኑር ሞጃሂድ ግን በሽሽት አመለጠ ። [10] በመጋቢት 1550 በሐረር የተባለውን ከባድ ጥፋት ከፈጸመ በኋላ በጦርነት ውስጥ ይሁን በሌላ ሁኔታ በዘመኑ ሰነድ ግልጽ ባልሆነ መንገድና ሥፍራ ፋኑኤል ራሱ ሞተ ።

ከጦር አበጋዙ ሞት በኋላ በ1550ዎቹ መጀመሪያ አጼ ገላውዴዎስ ራሱ በመላው አዳል አገር " ከባር ሰዓዳዲን እስከ ባር አጀም ድረስ " በቅጣት እርምጃ የአምስት ወራት ጊዜ የወሰደ ዘመቻ አካሂዶ በሕይወትና ንብረት ብዙ ጥፋት አደረሰ ። የአዳል ከተሞችንንና መስጊዶችንን አፈራረሰ ። በዘመኑ ሰነድ ስሙ ያልተጠቀሰውን አንድ የዜላ ንጉሥን ጨምሮ ገደለ ። [11]

ይህ ከሆነ በኋላ የአዳል ኤሚር ኑር ሞጃሂድ ከሚስቱ ከባታህ ድል ወንበራ ጋር ረጅም የመልሶ ማጥቃት ድርጅትና ዝግጅት አድርጐ አጼ

---

9 *Ibid*., *History*, pp. 342, 343, 352; W.E. Conzelman, tr. and ed., Chronique *de Galawdewos*( pains, 1895), chap. 2, pp. 2, 121, 122,

10 ተ.ጸ. መኩሪያ ፤ የግራኝ ወረራ ፤ ገጽ 813 ።

11 Conzelman, *Chronique de Galawdewos* chap. 2, 28-38; Doresse, *Histoire Sommaire*, pp. 230-231.

ገላውዴዎስ በሥራ ጉዳይ ወደ ጐጃም ሂዶ ሳለ በ1559 በጋ ወራት 1800 ፈረሰኛ ፣ 500 ነፍጠኛና ብዙ ቀስተኛ ወታደሮችን ጨምሮ በጉራዴ ፣ በጦርና በጋሻ ብዙ አዳሎች የተሰለፉበትን አንድ ታላቅ ሠራዊት በአጉራባቹ የፈጠጋር ክፍል ሀገር ላይ አዘመተ ። [12]

በፊት በ1531 አጼ ልብነድንግልና ራስ ወሰን ሰገድ ኢማም አህመድ ግራኝ ከዳሞት ዘመቻው ስምሪት ወደ ኋላ ይመለስ ይሆናል በሚል ግምት በደዋሮ — አዳል አቅጣጫ የከሸፈ ዘመቻ እንቅስቃሴ እንደሞከሩት ሁሉ ፣ አሁንም አጼ ገላውዴዎስ ኤሚር ኑር ከፈጠጋር ዘመቻው ወደ አገሩ ለመከላከል ይመለስ ይሆናል በሚል የጦር ታክቲክ በራስ ሐመልማልና በራስ ፋሲል ጥምር አዝማችነት በራሱ በአዳል አገር ከሐረር እስከ ዜላ ድረስ ታላቅ የቅጣት ዘመቻ አሰማራ ። [13] በዚህ ዘመቻ ወቅት ራስ ሐመልማል በሐረር ከተማ ላይ ጦርነት ከፍቶ በመጋቢት 31 ቀን 1559 ሱልጣን ባራካትን ጨምሮ ብዙ ሕዝብ ገደለ ። ብዙ ቤቶችንና መስጊዶችንም አቃጠለ ። [14]

ይሁን እንጂ ኤሚር ኑር ከጦረኛ ሚስቱ ከባታህ ድል ወንበራ ጋር በአጼ ገላውዲዎስና በጦር አበጋዙ በራስ ሐመልማል እንደታሰበ ከፈጠጋር ጦርነቱን ትቶ ወደኋላ አልተመለሰም ። በመሆኑም አጼ ገላውዴዎስ 270 ፈረሰኛ ፣ 100 ነፍጠኛ ፣ 500 ቀስተኛ ፣ 700 ጦር ፣ ጉራዴና ጋሻ የያዙ እግረኛ ወታደሮችን [15] ይዞ በመጋቢት 30 ቀን 1559 በፈጠጋር ጦር ሜዳ ከኤሚር ኑር ሠራዊት ጋር የሦስት ቀናት ጊዜ በወሰደ ጽኑ ጦርነት ለመግጠም ተገደደ ። ጦርነቱ በአጼ ገላውዴዎስ ሽንፈትና ሞት ተፈጸመ ።

ነገር ግን ድል አድራጊድ ኤሚር ኑር ሞጃሂድ ከባታህ ድልወንበራ ማህፉዝ ጋር ከፈጠጋር ጦርነት የአጼ ገላውዲዎስን የራስ ሰለባ ከታላቅ ምርኮ ጋር ይዞ በድል ስሜትና ክብር ወደ አገሩ ሲጓዝ ሳለ በመንገድ በሐረርና በአዋሽ መካከል በዘመኑ ሀዘሎ ወይም አዘሎ ተብሎ በሚታወቅ አገር በድንገት በምችሌ ሉባ (1554—1562) የተመራ የኦሮሞ ጦር አደጋ ጥሎ ታላቅ ጉዳት አደረሰበት ። [16]

---

[12] *Ibid.*, *Chronique de Galawdewos*, pp. 175-178; Budge, *History*; 349

[13] አጥሜ ጊዮርጊስ ፤ የጋላ ታሪክ በ2 ቅጽ (ያልታተመ ሰነድ 1907) ቅጽ 1 ገጽ 14 ፤

[14] *Ibid.*

[15] ተ.ጸ. መኩሪያ ፤ የግራኝ ወረራ ፤ ገጽ 815 ።

[16] Bahrey, *History of the Galla* in C.F. Beckingham and G.W.B. Huntingford, trs. and eds., *Some Records of Ethiopia* 1593-1646 (1954), p. 117.



በተጨማሪም ከምችሌ ሉባ አደጋ በፈረሰና በበቅሉ ሸሽት አምልጠው ኤሚር ኑርና ሚስቱ ከአደጋ ከተረፈው ሠራዊት ጋር ወደ ሐረር ከተማ ሲደርሱ በራስ ሐመልማል ሠራዊት ሱልጣኑ ተገድሎ የከተማው ቤቶችና መስጊዶች ተቃጥለውና ብዙ ሕዝብ አልቆ በሐረር ዙሪያ ደግሞ የአገሩ የቢዮ ፣ የሸዋ ፣ የነጃብ (የነገብ) ፣ የጅዳያ ፣ የዳካርና የሃር ጋያ አገሮችና ሕዝቦች በኦሮሞ ሰዎች ተይዘው አገኙ ። [17]

ከ1559 እስከ 1567 ድረስ ኤሚር ኑር የሐረር የአካባቢ አገሮችን በያዙ የኦሮሞ ሰፋሪዎች እንዳይያዝ እስከዛሬም ድረስ ያለውን የከተማውን ታሪካዊ ግምብ ገነባ ። [18] በመጨረሻም እህልና እንስሳት አልቆው ሰው ሰውን የበላበት የ1566—1568 ታላቁ ረሀብና በሽታ አንድ ሌላ የአዳል መቅሰፍት ሆነ ። በ1567 ኤሚር ኑር ሞጃሂድ ራሱ በዚሁ የረሀብና በሽታ መቅሰፍት ሞተ ። [19]

ከኤሚር ኑር ሞጃሂድ ሞት በኋላ የኢትዮጵያ ከሸዋ ከይፋት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ጥንታዊና ታላቁ የአዳል ሕዝብና የአካባቢ ሱልጣኔት መንግሥት በእርስ በርስና በሥልጣን ጦርነት መዘዝ በሐረር ፣ በአውሳና በዜላ ባላባታዊ አካባቢዎች ተከፍሎ ከአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ፍጻሜ በፊት ሦስቱም አካባቢዎች በሦስት የኦሮሞ ፣ የአፋርና የሶማሌ ማህበረሰቦች ቁጥጥር ስር ዋሉ ። [20]

በዚህ ረገድ በኤሚር ኑር ሞት የኤሚሩ የቀድሞ አገልጋይ ባለሥልጣን ኡስማን በሐረር ለሦስት ዓመታት (1567—1569) የአዳል ኤሚር ሆነ ። ኤሚር ኡስማን የቀድሞ አዳል ሱልጣኖችንና የኤሚሮችን ሃይማኖታዊ የጦርነት ፖሊሲና ተግባር በመተው በአዳልና በአካባቢው በፍለሳ እንቅስቃሴ በሰፈሩ ማህበረሰቦች መካከል በተለይም ከኦሮሞ ሰፋሪዎች ጋር ከገበያና ከኢኮኖሚ አኳያ የስምምነት ውል አደረገ ። በአዳል ሕብረተሰብም ዘንድ የሃይማኖት ትምህርትና ተግባር በሚመለከት የለዘብተኝነት ፖሊሲ መከተል ጀመረ ።

ነገር ግን የኤሚር ኡስማንን የሰላምና የለዘብተኝነት ፖሊሲ የሚቃወም ጦረኛ የአዳል ጥንታዊ የሱልጣኖች ፣ የኤሚሮችና የሼኮች አንጃ በሐረር በአውሳና በዜላ ማዕከላት ተፈጠረ ። የዚህ የአዳል ጦረኛ የመሳፍንቶች ፣ የኤሚሮችና የሼኮች አንጃ መሪ በመሆን የዋዚር አባስ አቡን

---

[17] Trimingham, *Islam in Ethiopia*, pp. 9294; አጥሜ የጋላ ታሪክ ቅ 1 ገፅ፡ 14

[18] *Ibid.*

[19] *Ibid.*, *Islam in Ethiopia*, p. 94.

[20] *Ibid.*, pp. 93-97; Doresse, *Histoire Sommaire*, pp. 229-237.

ልጅ ታልሃ አባስ በ1569 በሐረር ከተማ ኤሚር ኡስማንን በኩዴታ ከሥልጣኑ አባርር ራሱን አዲሱ የአዳል ሱልጣን (1569—1571) አድርጎ ሾመ ።

በመጨረሻ በ1571 የኡስማን ለዘብተኛው አጎት ሱልጣን ታልሃ አባስን ከሥልጣን አውርዶ የኡስማን ልጅ ናስርን የአዳል የመጨረሻው ሱልጣን አድርጎት ሾመ ። የሱልጣን ናስር ልጅ ሱልጣን መሐመድ አራተኛው (1572—1577) በ1575—1577 በኢትዮጵያ ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት ላይ የአዳልን የመጨረሻ አመጽ አካሂዶ በመጋቢት 1577 በዋቢ ሸለቆ ጦርነት በአጼ ሠርጸ ድንግል ተሸንፎ ሲሸሽ በምርኮ ተወስዶ ተገደለ ። በዋቢ ጦርነት የሱልጣን መሐመድ ሞት በኢትዮጵያ ማዕከላዊ አጼዎችና በአዳል አካባቢ ሱልጣናች መካከል ለረጅም ዘመን የተካሄደው ጦርነት ፍጻሜ ሆነ ።

በ1577 ሱልጣን መሐመድ አራተኛው በዋቢ ሸለቆ ከሞቱ በኋላ በሐረር ከተማ ከኢማም አህመድ ግራኝ ወገን የሚወለድ አንድ መሐመድ ጃሳ የተባለ ግለሰብ የአዳል ኢማም ሆኖ ተሾመ ። በወቅቱ አካባቢው በኦሮሞ ማህበረሰብ ከባድ ተጽዕኖ ስር በመሆኑ ፣ በ1577 ኢማም ጃሳ በሐረር ግምብ ወንድሙን በኤሚርነት ማዕረግ ሹሞ ፣ ለራሱ በሰሜን ምስራቅ በአዋሽ ሸለቆ አውሳን የአዳል አዲሱ ኢማሞች ማዕከል አደረገ ።[21]

በመሆኑም በ1577 የኢትዮጵያ ታሪካዊ የአዳል አካባቢ መንግሥት የአውሳ አዳል ኢማማትና የሐረር አዳል ኤሚሬያት ሆኖ በሰሜንና በደቡብ በሁለት ተከፈለ ። በ1647 በኤሚር ዓሊ ዳውድ (1647—1662) አመጽ ነጻነቱን እስኪያውጅ ድረስ የሐረር አዳል ኤሚሬያት ለአውሳ አዳል ኢማማት ይገብር ነበር ።[22]

በአጭር አነጋገር ከታላቁ ኤሚር ኑር ሞጃሂድ ዘመን በኋላ በቀድሞ አዳል አገርና የአካባቢ መንግሥት በእርስ በርስ ጦርነት ከተፈጠሩ የሐረር ፣ የአውሳና የዜላ ራስ ገዝ አካባቢዎች ዜላ ከ1585 ጀምሮ በሶማሌ ማህበረሰብ ይዞታ ስር ሆነ ። ከ1590 እስከ 1608 ባለው ጊዜ ውስጥ የአውሳ አዳል ኢማማት ደግሞ በኦሮሞና በአፋር ማህበረሰቦች ተጽዕኖ ሥር ወደቀ ።[23]

---

21 Trimingham, pp. 96-97.

22 *Ibid., Islam in Ethiopia*, p. 97.

23 Doresse, *Histoire Sommaire* pp. 236-237.



ነገር ግን በታላቁ የሐረር ግምብ ውስጥ የአዳል ኤሚሬያት ከ1647 ጀምሮ በዓሊ ዳውድ ስርወ መንግሥት አመራር በመጀመሪያ በ1875 ለአሥር ዓመታት በግብጽ ወረራ እስኪያዝ ድረስ ፣ ቀጥሎም በ1887 እንደገና በኢትዮጵያ ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት ስር እስኪሆን ድረስ በአካባቢው ለሦስቱ የሶማሌ ፣ የኦሮሞና የአፋር ኩሻዊ ማህበረሰቦች የእስልምና ሃይማኖት ፣ የንግድ ሥራ ፣ የከተማ ባህልና የመንግሥት ሥርዓት ማዕከልና ምሳሌ ሆኖ ኖረ ።

ይህ ሁሉ ከሆነና ከተባለ በኋላ አሁን የሚነሳው መሠረታዊ ጥያቄ በአካባቢው ከዘርና ከቋንቋ አኳያ በዚህ ጥናት የተገለጹ ጥንታዊ የሸዋ የይፋትና የአዳል ሰዎች ከዛሬ ሦስቱ ኩሻዊ የአፋር ፣ የሶማሌና የኦሮሞ ማህበረሰቦች ጋር ያለው ግንኙነት እንዴት ነው የሚለው ነው ።

በተጨማሪም ከዚህ ጋር አብረው የሚነሱ መሠረታዊ የዘርና የቋንቋ ጥያቄዎች በአካባቢው ከ896 እስከ 1577 ድረስ በአንድ ፌውዳላዊ ሥርዓት በፈረቃ የተነሱ የሸዋ ፣ የይፋትና የአዳል ሰዎች እንዲሁም የኢትዮጵያ እስላማዊ የአካባቢ መንግሥታት ቋንቋ ምን ነበር ? ኩሻዊ ወይስ ሴማዊ ? በኋላ በአካባቢው ማለትም በሐረር ግምብ በአካባቢው ኦሮሞዎች ነዋሪዎች “ አደሬ ” ተብሎ የሚጠራውና እሱ ራሱን “ሐረሪ” ብሎ የሚጠራው የኢትዮጵያ የሴማዊ ቋንቋ ማህበረሰብ ከጥንታዊ የሸዋ፣ የይፋትና የአዳል ሕዝብ ጋር የነበረው የዘርና የቋንቋ ግንኙነት ምን ነበር ተብለው የሚቀርቡ የታሪክ ጥያቄዎች ናቸው ።

በዚህ ረገድ እስከ ዛሬ ድረስ በሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ “አዳል ” ለአፋር ሰዎች ልማዳዊ የአካባቢ ማህበረሰቦች ስያሜ ሲሆን የአፋር ሕዝብ ራሱ ግን የስድብ ስያሜ ነው በማለት አይቀበለውም ። ለምሳሌ በዚህ “አዳል ” በሚል ስያሜ ጉዳይ በሚያዝያ 1969 የአፋር ብሔረሰብ አባሎች በገዋኔ ታሪካዊ ጉባኤ መግለጫና ውሳኔ ፤

“ የወደቀው ሥርዓት ደንከል ፣ አዳልና ቱልቱል በሚል ስም የአፋርን ብሔረሰብ መጥራቱ የብሔረሰቡን ታሪክና ባህል ለማጥፋት ሲል ያደረገው ተንኮል መሆኑን ጉባኤው በአንክሮ አስታውሶ ፣ ብሔረሰቡ ከአሁን ጀምሮ አፋር በሚል ስያሜ ብቻ እንዲጠራ አሳስቧል ።[24]

በገዋኔ ታሪካዊ ጉባኤ መግለጫና ውሳኔ የአፋር ማህበረሰብ አባሎች በትክክል እንዳሉት የኢትዮጵያ “ አዳል ” የተባለው ጥንታዊ ሕዝብና እስላማዊ የአካባቢ መንግሥት በእርግጥም ኩሻዊ የሆነ የአፋር ሕዝብ

---

24 “ የአፋር ብሔረሰብ አንድ ሀገር እንዲመሠረትለት ጠየቀ ፤ ” <u>አዲስ ዘመን</u> (ሚያዝያ 12 ቀን 1969) ።

አልነበረም ። በሌላ በኩል ግን ጥንታዊው የአዳል ሕዝብና የአካባቢው መንግሥት ከጥንታዊ የሸዋና የይፋት ብሎም በኋላ በሐረር ግምብ ከአደሬ ወራሽና ተከታይ ሕዝብና ኤሚሬያት ጋር በሥፍራ ፣ በጊዜ ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት እና በታሪክ በቅርብ የተያያዘ እንደነበር በሰነድ የታወቀ የኢትዮጵያ ታሪክ ይዘትና ሂደት ያሳየናል ።

በዚህ አኳያ ፣ በአረብኛ ቋንቋ ተጽፈው ከሐረር ኤሚሬያት የተገኙ ጥንታዊ የሸዋና የይፋት ማለትም የማክህዘሚና የዋለስማ ስርወ መንግሥታትና ሱልጣኖች ዜና መዋዕሎችን በሃያኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ተርጉሞ በማሳተም የተጠቀሱትን ሱልጣኔዎች ታሪካዊ መነሻ እድገትና ሂደት ለዓለምና ለታሪክ በትክክል ያሳወቀው ታዋቂው ኢጣሊያዊ ምሁር ዶክተር ኤንሪኮ ቼሩሊ ነው ።[25]

ዶክተር ኤንሪኮ ቼሩሊ ከ896 እስከ 1285 የነገሠውን የሸዋ የማክህዙሚ ስርወ መንግሥት ሱልጣኖችን ዜና መዋዕል The Chronological Repertory of Shoa; በሚል ስያሜ ፣ ከ1285 ጀምሮ የተነሳውን የይፋት የዋለስማ ስርወ መንግግሥት ሱልጣኖችን ዜና መዋዕል ደግሞ The History of the Walasma በማለት አዘጋጅቶ በሰነዶቹም መሠረት የሸዋና የይፋት ሱልጣኔቶችን ታሪካዊ መነሻ ዕድገትና ሂደት በማብራራት በቅርቡ ዩኔስኮ ማለትም የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የባህልና የሳይንስ ድርጅት በአዘጋጀው የአፍሪካ የመጀመሪያ አጠቃላይ ታሪክ በሦስተኛው ቅጽ ለዓለምና ለታሪክ በይፋ አሳውቋል ።[26]

እስከ ዛሬ ድረስ በተጠቀሱ የሸዋ ማክህዙሚና የይፋት ዋለስማ ተከታታይ ስርወ መንግሥታት ሰነዶችና በአካባቢው የትውፊት መረጃዎች ላይ የተደረገ ምሁራዊ የምርምር ጥናቶችና አስተያየቶች እንደሚያመለክቱ ፣ በግምት ከስምንተኛው ምዕተ ዓመት ወዲህ ከአረቢያ በአመዛኙ በኤደን ባህረሰላጤ—ዜላ በር በግልና በቡድን በገቡ እስላማዊ ነጋዴዎችና የሃይማኖት ሰባኪዎች ትምህርት በአፍሪካ ቀንድ በተለይ በኤደን ባህረሰላጤና በአባይ—ጊቤ መካከል በብዙ የአካባቢ ሱልጣኔቶች ወይም እስላማዊ መንግሥታት የተደራጁ ብዙ ነባርና ተዛማጅ ሕዝቦች በዘር ኩሻዊና ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች ነበሩ ።[27]

[25] *Trimingham, Islam in Ethiopia*, p. 58; Doresse, *Histoire Sommaire*, p. 193.

[26] E. Cerulli, *Ethiopia's Relations with the Muslim World* in UNESCO, *History of Africa*, vol. III (1988), pp. 575-585.

[27] M. EL. Fasi and I. Hrbek, *Stages in the Development of Islam and its Diss. emination in Africa* in UNESCO, *African History*, III (1988). pp. 84-85.



ከእነዚህ በማክህዙሚ ስርወ መንግሥትና ሱልጣኖች ሰነድ የተካሄደው የዶክተር ኤንሪኮ ቼሩሊ ጥናት እንደሚያመለክተው ፣ የሸዋ ሱልጣኔት ቋንቋ የኢትዮጵያ ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰብ ክፍል ማለትም ከኢትዮጵያ የግዕዝ ፣ የትግረ ፣ የትግሬ ፣ የአማራ ፣ የጋፋት ፣ የጉራጌ ፣ የአርጎባና የአደሬ ሴማዊ ቋንቋዎች ጋር ተመሳሳይ ነበር ።[28]

በዚህ አኳያ በአካባቢው ከተጠቀሱ ሱልጣኔቶች በተለይ ከ896 እስከ 1577 ድረስ በሰባት ምዕተ ዓመታት ውስጥ የሸዋ ፣ የይፋት ፣ የአዳልና የሐረር ሕዝቦች ፣ ስርወ መንግሥታትና ሱልጣኔቶች በተለይ በኤደን ባህረሰላጤና በአዋሽ — ጨርጨር መካከል በአንድ በተወሰነ የመሬት ክልል በጊዜ ፣ በሥርዓት ፣ በኢኮኖሚ ፣ በሃይማኖትና በባህል እርስ በርሳቸው እንዴት በቅርብ እንደተያያዙና እንደተወራረሱ በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት ከዚህ በላይ ታይቷል ። በተጨማሪም በዚህ ጥናት በሐረር ታሪካዊ ግምብ ውስጥ የአደሬ ሴማዊ የቋንቋ ማህበረሰብ በሥፍራ ፣ በጊዜ ፣ በሃይማኖትና በባህል የጥንታዊ ሸዋ ፣ ይፋት ፣ አዳልና ሐረር ሱልጣኔቶች ተከታይና ወራሽ እንደሆነ ከሰነድ መረጃ ታውቋል ።

በዚህ የአካባቢ ነባር ሕዝብና ቋንቋ ጥያቄ በአስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት በ1332 በአጼ ዓምደ ጽዮን ዜና መዋዕለ እንደተመለከተው ፣ በዘመኑ በይፋት ሱልጣኔት ስር አስራ ሰባት የአዳል ፣ የሞራ ፣ የለበካ ፣ የሀገራት ፣ የፈድቤ ፣ የገዳድ ፣ የነገብ ፣ የዙባ ፣ የሀርላ ፣ የሁባት ፣ የተርላ ፣ የዕዶም ፣ የአልበሮ ፣ የዜላ ፣ የእስቴ ፣ የደዋርና . . . በአካባቢ ነገሥታት የሚገዙ ንዑስ አገሮች እንደነበሩ ይታመናል ።

ከእነዚህ አገሮች ውስጥ በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት በኢማም አህመድ ግራኝ ዜና መዋዕል እንደተጻፈው የሀርላ እስላማዊ ሕዝብ ዛሙ ባራህ ፣ ባርዛራህ ፣ ያቆላህ ፣ ጃዛር ፣ አራብታከላና አልቃ በተባሉ ጎሳዎች የተከፈለ በእንስሳት እርባታ ፣ በእርሻና በንግድ ተግባራት የተሰማራ የቋንቋ ማህበረሰብ እንደነበር አይዘነጋም ። በመጨረሻ በ1585 ፣ በዘመኑ የረሀብ የበሽታና የፖለቲካ ችግር ማዕከል ከነበረው ከሐረር አካባቢ የሀርላ ነባር ሕዝብ በከፊል ከኢማም መሐመድ ኢብራሂም ጋር በሽሽት ወደ ዘላፈለሰ ።[29]

[28] Cerulli, *Ethiopia's Relations With the Muslim World*, P. 580.

[29] Doresse, *Histoire Sommaire*; p. 236.

በዚህ በምስራቅ ኢትዮጵያ ትውፊት በአካባቢው የሚገኙ የጥቫ ድንጋይ ላይ ስዕሎችን ፣ የድንጋይ ገንዳዎችንና የመቃብር ላይ ሐውልቶችን የሠራው ጥንታዊ ሕዝብ ሀርላ ተብሎ እንደሚታወቅ ተመዝግቧል ። [30] ስለዚህ ከዚህ በላይ የቀረቡት የትውፊት ፣ የሰነድ ፣ የታሪክ ፣ የቅድመ ታሪክ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን በሥፍራና በጊዜ በማገናዘብ በአፍሪካ ቀንድ ለጥንታዊ የሸዋ ፣ የይፋት ፣ የአዳል ፣ የአደሬ እስላማዊ ሱልጣኔቶችና ማህበረሰቦች ታሪካዊ መነሻና መሠረት የሆነው ነባር ሴማዊ የሀርላ ሕዝብ ነው የሚል ትምህርታዊ የታሪክ ቴሲስ በአንድ ምሁር ቀርቧል ። [31]



ጥንታዊው የሐረር ከተማ በ1850ዎቹ በእንግሊዛዊ መንገደኛ ሪቻርድ በርተን እንደታየው ፣

---

[30] U. Braukamper, " Islamic Principalities in Southeast Ethiopia between the Thirteen and Sixteenth Centuries" part I and II, *Ethiopianist Notes*, vol. 1, Nos. 1,2 (1977) pp. 21-22.

[31] *Ibid.*



## መደምደሚያ

በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ውስጥ የኢማም አህመድ ግራኝ ጦርነት ያስከተላቸው ውጤቶች ብዙና መሠረታዊ ናቸው ። አንደኛ በአንድ በኩል የአካባቢ ሱልጣኖችና የማዕከላዊ አጼዎች ኃይል እየደከመ በሌላ በኩል ደግሞ በየአካባቢው የጦር አበጋዞች ሥርዓትና ኃይል እያደገ ሄደ ። በሌላ አነጋገር በአገሪቱ የፊውዳሊዝም ሥርዓት እያደገና እየተስፋፋ ሄደ ።

ሁለተኛ ፣ ከዚሁ ሁኔታ ጋር በቅርብ የተያያዘው ማዕከላዊው የአጼ መንግሥት የበላይ ሥልጣንና አመራር እስከ ዳግማዊ ቴዎድሮስ (1855—1868) ድረስ ለአራት ምዕተ ዓመታት በጦር አበጋዞች ኃይል ተጽዕኖ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ ሄደ ። ማለትም በአገሪቱ አንድ ጠንካራ የሆነ ብሔራዊ የፖለቲካ ሥልጣን ማዕከል ጠፋ ።

ሦስተኛ ፣ የኢትዮጵያ ታላቁ የሕዝቦች ፍለሳና መወራረስ ሂደትና ዘመን ተጀመረ ። ባጭሩ በዚህ የማዕከላዊው የአጼ መንግሥት የበላይ ሥልጣንና ቁጥጥር በወደቀበት ዘመን ፣ በአንጻሩ በሥፍራ ፣ በቋንቋ ፣ በሃይማኖት በባህል የኢትዮጵያ የአራቱ ኩሻዊ ፣ ሴማዊ ፣ ኦሞአዊና ናይሎቲካዊ ነባርና ተዛማጅ ሕዝቦች ታላቅ አገር አቀፍ እንቅስቃሴና መወራረስ ተካሄደ ።

አራተኛ ፣ በአንጻሩ ደግሞ በአገሪቱ መሠረታዊ የንግድ ፣ የዕደጥበብ፣ የከተማ ፣ የትምህርትና የቴክኖሎጂ ዕድገት ከሞላው ጐደል እየተገታ ሄደ ። በሌላ አባባል በአገሪቱ ጠንካራ የሆነ የፖለቲካ ማዕከልና የኢኮኖሚ ሥርዓት ባልዳበረበት ዘመን በማህበረሰቦች ፍለሳና መወራረስ ሂደት የኢትዮጵያ በሀውርታዊ ሕብረተሰብ ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ ተካሄደ ።

አምስተኛ ፣ ከኢማም አህመድ ግራኝ እስከ ዳግማዊ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ታላቅ የዘላኖችና የጦር አበጋዞች ዘመንና ሥርዓት ( The Era of Nomadism and Regional Warlordism) በአገር አቀፍ ደረጃ ተስፋፋ ። በዚህ አኳያ ለምሳሌ በደቡብና በምስራቅ በእርሻና በንግድ ተግባራት በከፍተኛ ደረጃ ዳብረው በነበሩ በጥንቱ የይፋት—አዳል ፣ የደዋሮ ፣ የአራባቢኒ ፣ የሀዲያ—ሲዳማ ፣ የሻርካ ፣ የባሌና የደራ አገሮች ሦስቱ ዘላን የአፋር ፣ የሶማሌና የኦሮሞ ማህበረሰቦች ሲሰራጩ በሰሜንና በመሀል ምዕራብ አካባቢዎች ደግሞ ታላላቅ የጦር አበጋዝ ግዛቶች በብዛት አደጉ።

ማለትም የቀላኛው ኖማዲዝምና የደጋኛው ፊውዳሊዝም የአገሪቱ ሁለት ታላላቅ የሥርዓት ገጽታዎች ሆነው ተከሰቱ ።

ስድስተኛ ፣ በሥርዓትና በተግባር የተያያዙ የጐሳ ፣ የሃይማኖት ፣ የባህልና የፖለቲካ ጭቆና ዘመን በአንድ በኩል ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የካስት ዕደ ጥበብና የባርያ ንግድ ኢኮኖሚ ጐን ለጐን በተለይ በመሀል አገር ተከሰቱ።በዚህ አኳያ በኢማም አህመድ ግራኝ ጦርነትና በሕዝቦች እንቅስቃሴ ምክንያቶች በኢኮኖሚና በፖለቲካ ከደረሰበት ጊዜያዊ ጥቃትና ጥፋት የተንሰራራው የኢትዮጵያ ክርስቲያኑ ንጉሣዊ የገዥ መደብ በቅጣት ፖሊሲና ተግባር በተወሰኑ የሕብረተሰቡ ክፍሎች ላይ በተለይም በፈላሽና በእስላም ማህበረሰቦች ላይ የዘውዱ ቋሚ የሥልጣን ጠላቶች ናቸው በሚል ክስ ከባድ የሆነ የጐሳ ፣ የሃይማኖት ፣ የባህልና የፖለቲካ ጭቆና መሠረተ ።

ለምሳሌ የጐንደሩ አጼ ጻድቁ ዮሐንስ በአገሪቱ በሥፍራ ፣ በቋንቋና በታሪክ አንድ የሆኑ የክርስቲያን ፣ የፈላሻና የእስላም ማህበረሰቦችን በተለያዩ መንደሮች የሚኖሩበትን የጭቆና ሕግ እንደመሠረተውና ሕጉም ለረጅም ዘመን ጸንቶ እንደኖረ ይታወሳል ። በዚህ የጭቆና ሕግና ሥርዓት መሠረት የፈላሻና የእስላም ማህበረሰቦች ከክርስቲያን ወገኖች ጋር የመሬት ባለቤቶች እንዳይሆኑ እንዲሁም በመንግሥት የሥልጣንና የአገልግሎት ሥፍራዎችና ሥራዎችም በዜግነት መብትና ግዴታ መሠረት ተካፋዮችና ተሳታፊዎች እንዳይሆኑ ፣ መሣሪያ ታጥቀው ራሳቸውንና አገራቸውን ከጠላት እንዳይከላከሉ ተደረጉ ። በመሆኑ እርሻ የክርስቲያኑ፣ ዕደ ጥበብ የፈላሻው ንግድ ደግሞ የእስላሙ ማህበረሰባዊና ካስታዊ የሥራ ድርሻና ክፍፍል ሆነ ።

በዚህ ሥርዓታዊ ፖሊሲና አሠራር በዘመኑ በአገሪቱ የክርስትና ሃይማኖትና ማህበረሰብ ከፊውዳላዊ የመሬት ሥሪትና ግብር ጋር የእስላሙ ሃይማኖትና ማህበረሰብ ደግሞ ከባርያ ፍንጋላና ንግድ ጋር በቅርብ የተያያዙ ሆኑ ። የዕደ ጥበብ ሙያና ተግባር ደግሞ ፈላሾችን ጨምሮ የካስቶች ባህላዊ የሥራ ድርሻና የመለያ ምልክት መሆን ጀመረ ። ይህ በመደባዊ ብዝበዛና ጭቆና የተመሠረተው ማህበራዊ የፖለቲካ ሥልጣንና የሙያ ክፍፍል በአገሪቱ በኢኮኖሚያዊና በቴክኖሎጂያዊ ዕድገት ላይ ከባድ ሥርዓታዊና ባህላዊ ተጽዕኖ አሳደረ ።


ሰባተኛ ፣ በሥፍራና በጊዜ የማይቋረጥ የእርስ በርስ ፣ የጐሳ ፣ የሥልጣን ፣ የሃይማኖትና የጦር አበጋዞች የዘወትር ጠብና ግጭት በአገሪቱ ሰላማዊ ሕይወትና ማኅበራዊ ዕድገት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕና አስከተለ ። በተለይም ከ1531 ጀምሮ በተከታታይ በኢማም




አህመድ ግራኝ ጦርነትና በታላቁ የሕዝቦች እንቅስቃሴ ምክንያቶች በምስራቅ ፣ በደቡብ ፣ በመሀልና በመሀል ምዕራብ ሰፊና ሀብታም አካባቢዎች የኢኮኖሚ ይዞታና ገበያ ያጣው የአገሪቱ ክርስቲያኑ የገዥ መደብ በሰሜኑ ደጋማ ቀበሌዎች በአማራ፣በአገው ፣ በፈላሻና በትግሬ ማኅበረሰቦች ላይ በተለይ በሥፍራና በጊዜ የማያቋርጥ የዘረፋ ጦርነት ዘወትር በማካሄድ በአካባቢው በሕይወት ፣ በንብረትና በባህል ለምዕተ ዓመታት ዘላቂ ጥቃትና ጥፋት አደረሰ ።

ስምንተኛ ፣ በ1542 ፖርቱጋሎችና ቱርኮች በየበኩላቸው በሃይማኖት ስምና ሽፋን በአገሪቱ ውስጣዊ የእርስ በርስ ጦርነት ጉዳይ ጣልቃ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ ጠረፎችና በሮች የውጭ ኃይሎች ግፊት ከዚሁ ከቀይ ባህርና ከአባይ ሸለቆ ጂኦፖለቲካ ጋር በቅርብ የተቀራኘው አገርና ዓለም አቀፍ የባርያ ንግድ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ነጻነት ፣ የግዛት አንድነት ሰላምና ማኅበራዊ ዕድገት ላይ አንድ ታላቅ የውጭ ተጽዕኖ አሳደረ ።


ከዚህ በላይ በአጭርና በጥቅል በተዘረዘሩና በሌላም ብዙ መሠረታዊ ምክንያቶች ታላቁ የ1524—1543 የኢማም አህመድ ግራኝ አመጽ በዝርዝርና በትክክል ሊጠናና ሊታወቅ የሚገባ የኢትዮጵያ አንድ ልዩ የታሪክ ዘመንና ምዕራፍ ነው ።



በ1500ዎቹ በንግሥት እሌኒ የተሠራና በ1536 በአህመድ ግራኝ በከፊል የተቃጠለ የመርጦለ ማርያም ቤተክርስቲያን በጎጃም



በ1500ዎቹ በንግሥት እሌኒ የተሠራና በ1536 በአህመድ ግራኝ በከፊል የተቃጠለ የመርጦለ ማርያም ቤተክርስቲያን በጐጃም






## 4. ታላቁ የሕዝቦች ፍለሳ ከ1520 እስከ 1660

### የታሪክ መረጃ ፤

በኢትዮጵያ የ1520—1660 ታላቁ የሕዝቦች እንቅስቃሴና መወራረስ ታሪክ ላይ መሠረታዊ የሰነድ ፣ የጉንጉዊስቲክስና የትውፊት መረጃ ምንጮችንና ጥናቶችን በሚመለከት ፣ በአረብፋ ቂህ የተጻፈው የአህመድ ግራኝ ዜና መዋዕል ፣[1] የአጼ ገላውዴዎስ (1540—1559) ዜና መዋዕል ፣[2] በጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ ሃይማኖት የተጻፈው የሠርጸ ድንግል (1563—1597) ዜና መዋዕል ፣[3] በ1593 ዜና ዘጋላ በሚል ርዕስ በአባ ባሕርይ የተጻፈው የኦሮሞ ፍለሳ ታሪክ ፣[4] በጸሐፊ ትእዛዝ ተክለ ሥላሴ የተጻፈው የአጼ ሱስንዮስ (1605—1632) ዜና መዋዕል ፣[5] በአስራ ስምንተኛው ምዕተ ዓመት በጐንደሩ ደጃዝማች ኃይሉ እሸቴ የተዘጋጀው አጭር የዜና መዋዕሎች ሰነድ[6] በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት በአለቃ አጥሜ ጊዮርጊስ የተጻፈው የጋለ ታሪክ ፣[7] እስከ ዛሬ ድረስ በእነዚህ ሰነዶችና አግባብ ባላቸው የሊንጉዊስቲክስና የትውፊት መረጃዎች ላይ የተካሄዱ ጥቂት ምሁራዊ ጥናቶች[8] በመጀመሪያ ደረጃ ይቀርባሉ ።

ከእነዚህ ቁልፍ የታሪክ ምንጮች የአረብፋ ቂህ መጽሐፍ በኢማም አህመድ ግራኝ አመጽ ወቅትና ሂደት ከምስራቅ ወደ መሀል ወደ ምዕራብና ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ አንድ ታላቅ የሕዝቦች እንቅስቃሴ መጀመሩን ያሳያል ። በመጽሐፉ ፍጻሜ ቀላኛና በሃይማኖት እስላም የሆኑ የምስራቅ ሰፋሪዎች በኢማም አህመድ ግራኝ መሪነት በመሀል ፣ በሰሜንና በምዕራብ አካባቢ ነባር ሕዝቦችን በገባርነት ይዘው በነዋሪነት የእርሻ ፣ የመንደርና የመስጊድ ሥራዎችን ሲሠሩና ሲያሰሩ በዘመቻ መልክና መንፈስ ይታያል ። በዚህ ዘመን ከየአካባቢው ሕዝቦች ዘጠና በመቶ በውድም በግ

---

1 Arab-Faqih, *Histoire De La Conquete De L' Abyssinie*, tr. and ed. by R. Basset (1897).

2 W.E. Conzelman, tr. and ed., *Chronique de Galawdewos* 1540 1559 (1895)

3 Conti Rossini, tr. and ed., *Historia Regis Sarsa Dengel* 1563-1597 (1907)

4 Bahrey, *History of the Galla* in C.F. *Beckingham* and G.W.B. Hinting ford, trs. and eds., *Some* Records *of Ethiopia* 1593-1646 ( 1954), pp. 110-129.

5 ተክለ ሥላሴ ፤ የአጼ ሱስንዮስ ታሪክ 1605-1632 ታሪክ ( ያልታተመ ዜና መዋዕል ፤ በአዲስ አበባ በብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት በግዕዝ ክፍል )።

6 C. Basset,tr. and ed. *Etudes Sur L' Histoire D'Ethioie* (1881).

7 አጥሜ ጊዮርጊስ ፤ የጋላ ታሪክ ( ያልታተመ ጽሑፍ በሁለት ቅጽ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናት ኢንስቲትዩት ።)

8 U. Braukamper, *Geschichte Der Hadiya Sud-Athiopiens* ( 1980) *Asmarom* Legesse, *Gada* (1973)

ድም በአገር አቀፍ ደረጃ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች እንደሆኑ በኋላ
በአጼ ገላውዴዎስ ዜና መዋዕል በይፋ ተገልጾአል ።

የአጼ ገላውዴዎስና የአጼ ሠርጸ ድንግል ዜና መዋዕሎች በአንድ
በኩል በአገር ውስጥ በ1520ዎቹ የተጀመረውን አገር አቀፍ የሕዝቦች እን
ቅስቃሴን ለመቆጣጠርና በእንቅስቃሴውም ግፊት በከፋኛ የተናጋውን
ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት ኃይልና ሥልጣን መልሰው ለማጠናከር ፣
በሌላ በኩል ደግሞ ከውጭ የፖርቱጋልና የቱርክ ግፊቶችን ለመከላከል
በትጥቅና በፖለቲካ የተወሰዱ ብርቱ ንጉሣዊ ጥረቶችን ያሳያሉ ።

ዜና ዘጋላ በሚል ርዕስ በ1593 በአባ ባሕርይ የተጻፈውና የኦሮሞን
የፍለሳ ምንጭና እንቅስቃሴ በሚመለከት ብቸኛ ዘገባ የሆነው የታሪክ
ሰነድ ፣ በርቱማና ቦረና የተባሉ ሁለት አውራ የኦሮሞ ጉሳዎች ገዳ በተባ
ለው የጉላ ሥርዓትና ሉባ በተባለ ልዩ የደፈጣ ውጊያ ስልት ተደራጅ
ተው በግምት ከ1520ዎቹ መባቻ እስከ 1590ዎቹ መጨረሻ ድረስ በፍለሳ
ስምሪትና ስርጭት በደቡብ ምስራቅ በአባያ—ቦረና አካባቢ ከነበረው እገ
ራቸው ወደ ምስራቅና ወደ ሰሜን አቅጣጫዎች በመንቀሳቀስ በስምንት
አሥርታት ውስጥ በጥንቱ የሀዲያ—ሲዳማ ፣ የባሌ ፣ የደዋሮ ፣ የአዳል ፣
የሻርካ ፣ የፈጠጋር ፣ የይፋት ፣ የማያ ፣ የዋጅ ፣ የገበርጌ ፣ የወረብ ፣ የሸዋ ፣
የዳሞት ፣ የጋፋት ወዘተ አገሮችና አውራጃዎች ላይ ያካሄዱትንና የሚያ
ካሂዱትን ታላቅ የመስፋፋት ጦርነት ሁኔታ በሥፍራና በጊዜ ይገልጻል ።

በጸሐፊ ትእዛዝ ተክለሥላሴ የተጻፈው የአጼ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል
እንዲሁም አንደኛ ፤ ከ1540 እስከ 1632 ድረስ ለአንድ ምዕተ ዓመት
ከሦስቱ ጦረኛ አጼ ነገሥታት ገላውዴዎስ ፣ ሠርጸ ድንግልና ሱስንዮስ
ጋር ረጅምና መራራ ጦርነት አካሂደው በኢትዮጵያ ማዕከላዊ የአጼ መን
ግሥት ጦርና አመራር ላይ ግልጽ የሆነ የኃይልና የድል ሚዛን በማግ
ኘት ፣ የሜጫ ፣ የቱላማ ፣ የወሎ ፣ የከረዩ ፣ የጅሌ ፣ የኢቱ ፣ የወረንጨሻ
(አርሲ) ፤ የቦዶ . . . ወዘተ ኦሮሞ ጉሳዎች ፣ በሰሜኑ ደጋ ከትግራይ ፣
ከላስታና ከበጌምድር በመለስ ፤ በምዕራብ ደግሞ ከአባይ — ጉጃም
በመለስ ፤ በምስራቅ ፣ በደቡብ ፣ በመሀልና በመሀል — ምዕራብ በትድሞ
የሀዲያ—ሲዳማ ፣ የባሌ ፣ የደዋሮ ፣ የአዳል ፣ የሻርካ ፣ የፈጠጋር ፣ የይፋት ፣
የማያ ፣ የዋጅ ፣ የገበርጌ የወረብ ፣ የሸዋ ፣ የዳሞት ፣ የጋፋትና የእርያ
አገሮችና ሕዝቦች ላይ እንዴት በነዋሪነት እየሰፈሩ አዲስ የእርሻ ሥራና
ባህል እንደጀመሩ ብሎም ጥንታዊ የገዳ ሥርዓታቸው በአዲስ አካባቢና
የኑሮ ሁኔታ ማለትም በሥርዓታዊ ዕድገትና ለውስጥ መፍረስ እንደጀመረ፤



ሁለተኛ ፤ በረጅምና መራራ ጦርነት ደጋግመውን የትግራይ ፣ የበጌም
ድር ፣ የደምብያና የጉጃም ጥንታዊ አገሮችንና አውራጃዎችን ከኦሮሞ
ዎች ይዞታና ሰፈራ ነጻ አካባቢዎች ካደረጋቸው በኋላ ጦረኛው አጼ
ሲስንዮስ በሰሜን ምዕራብ በታላቁ የጣና ሐይቅ አካባቢ በራት ከ1536
እስከ1543 ድረስ ኢማም አህመድ ግራኝ የመንግሥቱ መሠረትና ማዕከል
አድርጉ በቆረቆረው በአገው በፈላሻና በጉሙዝ ምድር አዲሱን አካባቢ
ያዊ የጉንደር ስርወ መንግሥትና ዘመነ መንግሥት (1605—1855) እን
ዴት እንደመሠረተ ፤

ሦስተኛ ፤ ከ1603 እስከ 1632 ድረስ የፖርቱጋል ነባር ወታደሮችና
አዲስ ኢየሱሳውያን የተባሉ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን በአጼ ሱስንዮስ
መሪነት የገኘ መደብ መሪዎችንና አባሎችን ከግብጻዊ የኦርቶዶክስ ክር
ስትና ወደ ሮማዊ የካቶሊክ ክርስትና በመለወጥ እንዴት ረጅምና መ
ራራ የሆነ የሃይማኖትና የእርስ በርስ ጦርነት እንዳንቀሳቀሱ ፣ በጦርነቱም
ምክንያት አጼ ሱስንዮስ ራሱ በአመጽ ግፊት ከዙፋኑ ሲወርድ በልጁና
በወራሹ በአጼ ፋሲል የፖርቱጋል ሚሲዮናውያን ከኢትዮጵያ እንዴት
እንደተባረሩ ፤

በዝርዝር የሚገልጽ በአገሪቱ በኦሮሞ ሰፈራና በጉንደር ስርወ መን
ግሥት ምስረታ ቁልፍ የታሪክ ምንጭ ነው ።

በአስራ ስምንተኛው ምዕተ ዓመት በጉንደሩ ደጃዝማች ኃይሉ እሸቴ
ተዘጋጅቶ በ1881 በሬኔ ባሴት ወደ ፈረንሳይኛ ፣ የተተረጎመው የታሪክ
ሰነድ የኢማም አህመድ ግራኝ አመጽ ፣ የታላቁ የ1520—1660 ሕዝቦች
ፍለሳ የእነ አጼ ገላውዴዎስ የእነ አጼ ሠርጸ ድንግል ዜና መዋዕሎች የጉ
ንደር ስርወ መንግሥትና ነገሥታት በዘመነ ጉንደር የተነሱ የሃይማኖት
ጉዳዮች ሁሉ አጭርና አጠቃላይ ዘገባ ነው ።

በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት በአለቃ አጥሜ ጊዮርጊስ (1825—
1907) የጋለ ታሪክ በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ጽሑፍ ከዚህ በላይ በተጠ
ቀሱ የታሪክ ምንጮችና በትውፊታዊ መረጃዎች መሠረት የተካሄደ የታ
ሪክ ጅምር ጥናት ነው ። ጥናቱ ከኦሮሞ የፍለሳ አነሳስ እስከ ዳግማዊ ቴዎ
ድሮስ ዘመነ መንግሥት ድረስ የማህበረሰቡ የተለያዩ ጉሳዎች በሰሜን
ከጉንደር ስርወ መንግሥትና ነገሥታት (1605—1855) ጋር በደቡብ
ደግሞ በሸዋ ከነጋሢ ክርስቶስ ስርወ መንግሥት (1696—1855) ጋር
የነበራቸውን ግንኙነት በመግለጽ በዘመኑ በሁለቱም አካባቢዎች በሥ
ፍራ ፣ በኢኮኖሚ ፣ በሃይማኖት ፣ በፖለቲካና በቋንቋ በኦሮሞና በአማራ
ማህበረሰቦች መካከል የተፈጠረውን መቀላቀልና መወራረስ በአንድ አስ
ተዋይ ጸሐፊ አመለካከትና ግንዛቤ ያሳያል ።

በዚህ ረገድ አንድ መሠረታዊ የግንዛቤ ጉዳይ አለ ። ይኸውም በአገሪቱ ረጅም ታሪክ በአስራ ስድስተኛውና በአስራ ሰባተኛው ምዕተ ዓመታት በአንድ በኩል በእርስ በርስ ጦርነት የአገሪቱ የግዥ መደቦች ድክመትና ውድቀት በሌላ በኩል የታላቁ የሕዝቦች ፍለሳ በሥፍራ ፣ በቋንቋ ፣ በእምነትና በባህል የብዙ ማህበረሰቦችን መቀላቀልና መወራረስ ብሎም በኋላ ከዚሁ ታሪካዊ ሁኔታና ሂደት የሚፈጠረው የኢትዮጵያ የዛሬው በህውርታዊ መንግሥትና ሕብረተሰብ ነው ።

## የፍለሳው ሂደትና ብሔራዊ ስፋት ።

የአገሪቱን ማዕከላዊና በህወርታዊ የአፄ መንግሥት ኃይልና ሥልጣን በከፋኛ ያናጋው የኢማም አህመድ ግራኙ አመጽ ከ1520ዎቹ እስከ 1660ዎቹ ድረስ ደግሞ ለሚከተለው ለታላቁ የሕዝቦች ፍለሳና መወራረስ አንዱና ዋነኛው ቅድመ ሁኔታ ሆነ ።

በዚህ አኳያ አንደኛ ፤ የገንዘ ፤ የጐደላ ፣ የዋቶጅራ ፣ የገደብ ፣ የአላባ ፣ የቀቤና ፣ የኡልባራግ ፣ የአዘርነት በርበሬ ፣ የስልጤ ፣ የሸሾጐ ፣ የማረቆ (ሊቢዶ) ፣ የማልጌና የቡኼ ሀዲያ—ሲዳማ የተለያዩ ጐሳዎች ፤

ሁለተኛ ፤ የኢቱ ፣ የወረንጨሻ (የአርሲ) ፣ የከረዩ ፣ የወሎ ፣ የጅሌ የቱለማና የሜጫ አሮሞ (የበርቱማ—ቦረና) ጐሳዎች ፤

ሦስተኛ ፤ የደራሳ—ጌዴኦ ፣ የዳሞት ፣ የጋፋት ፣ የሂናሮ (የእናርያ) ፣ የቦሻ ፣ የአዳልና የሶማሌ የተለያዩ ሕዝቦችና ማህበረሰቦች ፣

በልዩ ልዩ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ከጥንት አገሮቻቸው እንደ እየአካባቢውና የወቅቱ ግፊት በሙሉ ወይም በከፊል በመላው ደቡብ ፣ ምስራቅ ፣ መሀልና መሀል—ምዕራብ ኢትዮጵያ በፍለሳ ስምሪት ለተንቀሳቀሱበት እርስ በርሳቸው በሥፍራ በቋንቋ ፣ በስርዓትና በባህል ለተወራረሱበት ለታላቅ የሕዝቦች ፍለሳና ስርጭት ዘመን ታሪካዊ መነሻ ሆነ።

ነገሩ በዝርዝር ሲታይ በሁለቱ ተከታታይ የኢማም አህመድ ግራኝ፣ አመጽና በታላቁ የሕዝቦች እንቅስቃሴ ምክንያቶች በደቡብ ፣ በምስራቅና በመሀል ኢትዮጵያ ጥንታዊ የባሌ ፣ የደዋሮ ፣ የአዳል ፣ የሻርካ ፣ የፈጠጋር ፣ የማያ ፣ የዳሞት ፣ የጋፋት ፣ የቦሻ ፣ የሄናሮ (የእናርያ) ፣ የጐንጋና የቢዛም ነባር ሕዝቦች ከአገሮቻቸው ሙሉ በሙሉ ጠፉ ወይም በሦስቱ የኦሮሞ ፣ ሶማሌና አፋር ማህበረሰቦች ከጊዜው በኋላ ተውጠው ቀሩ ።

በደቡብ ምስራቅ ጥንታዊ የገደብቾ የጐደላ ፣ የዲሆ ፣ የሀደቦ ፣ የገንዘ ፣ የሰጋ ፣ የገብ ፣ የቀቤና ፣ የጐጋላ ፣ የአላባ ፣ የአዘርነት በርበሬ የኡልባራግ የስልጤ ፣ የዋቶጅራ ፣ የሸሸጉ ፣ የማልጌ ፣ የቡሼና የማረቆ ሀዲያ—



ሲዳማ የተለያዩ ጐሳዎችና ማህበረሰቦች በግምት ከ1530 እስከ 1600 ድረስ በብዛት አገሮቻቸውን በፍለሳ እንቅስቃሴ በመተው በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ በዛሬው ደቡብ ሸዋና ሰሜናዊ ምዕራብ ሲዳሞ ከአካባቢው ነባር የደራሳ—ጌዶአ የጉራጌ የከምባታ ሕዝቦች ጋር በሥፍራ በጊዜና በባህል እስከዛሬ ድረስ በመካሄድ ላይ ያለውን ታሪካዊ የአንድነት ሂደት ጀመሩ ።

በዚህ ረገድ እስከ ኢማም አህመድ ግራኙ ጦርነት ድረስ ከብላቴ ወንዝ በስተምዕራብ ከጉራጌ በስተደቡብ በዛሬው አንጋጫ ወረዳ ደጋማው የከምባታ አገር የማዕከላዊው የአፄ መንግሥት ክርስቲያን ሰፋሪዎች የሚኖሩበት ውስጣዊ የአውራጃ ግዛት ሲሆን (ማለትም ራስ ገዝ አልነበረም) በኋላ በ1531—1532 የኢማሙ የአዳል ሠራዊት በገራድ አብድ ናስር አዝማችነት በአውራጃው ክርስቲያን ሰፋሪዎችና በቤተ መንግሥት ንብረት ላይ ታላቅ ጉዳት በማድረስ አካባቢውን በኋላ በታላቁ የሕዝብ ፍለሳ ወቅትና ሂደት በቋንቋ በታሪክ ተዛማጅ ለሆኑ ለሀዲያ ለሲዳማና ለደራሳ—ጌዲኦ ማህበረሰቦች ሰፈራ አንድ ክፍት ክልል አደረገ [9] ። በተጨማሪም በ1620ዎቹ ከሰሜን ምዕራብ የዳሞትና የጋፋት ስደተኞች በጥቂቱ በዚሁ የከምባታ ደጋ እንደሰፈሩበት የታሪክና የትውፊት መረጃዎች ያሳያሉ ።

በመሆኑም በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት የሁለተኛው አጋማሽ በብላቴና በጊቤ ወንዞች መካከል የከምባታ ደጋማና እስትራቴጂያዊ ምድር በሰሜን ምዕራብ ከዳሞትና ከጋፋት ለፈለሱ ስደተኞች በምስራቅና በደቡብ ምስራቅ ከሀዲያ ፣ ከሲዳማና ከደራሳ ለተለያዩ የገንዘ ፣ የኤጃቤና ፣ የኤፌጌና ፣ የጉሮግ ፣ የቃምበራ (የጥምባሮ)፣የዶንጋ፣የዱባሞ ፣የዋቶጅራ ተዛማጅ የቋንቋ ማህበረሰቦች አዲሱ በህውርታዊ መኖሪያ ሆነ።[10]

በአካባቢው ማለትም በሻላ ሐይቅና በጊቤ ወንዝ መካከል የዛሬው የአላባ ፤ የሀዲያ ፣ የማረቆ (ሊቢዶ) የከምባታና የቃምብራ (ጥምባሮ) ተዛማጅ የቋንቋ ማኅበረሰቦች አጠገብ ለአጠገብ አደጉ ። የተጠቀሱ ተዛማጅ ማህበረሰቦች በደቡብ ምስራቅ ከዛሬ ሲዳማ ፣ ደራሳ (ጌዴኦ) እና ቡርጂ ማህበረሰቦች ጋር በቋንቋ ያላቸው የቀረበ ግንኙነት በሚከተለው ሊንጉዊስቲካዊ ሠንጠረዥ ከመቶ ስሌት በግልጽ ይታያል ። በሰሜን ከጉራጌ ፣ በምስራቅ ከኦሮሞ በደቡብ ምዕራብ ከወላይታ ማህበረሰቦች ጋር የሚኖ

[9] Arab-Faqih, *Conquete*, pp. 365, 378.

[10] U. Braukamper, *Die Kambata* (1983), pp. 26,37,43, 294-297.

ሰኑ እነዚህ የሀዲያ ፣ የማረቆ (ሊቢዶ) ፣ የሲዳማ ፣ የጌዴኦ ፣ የቡርጂ ፣ የአላባ ፣ የከምባታና የጥምባሮ ተዛማጅ የቋንቋ ማህበረሰቦች በሕብረት በአካባቢው የጥንቱ የሀዲያ ሕዝብና የአካባቢ መንግሥት ታሪካዊ ተወላጆችና ወራሾች ናቸው ።

## ሠንጠረዥ 4

## በታላቁ ፍለሳ ሂደት በሀዲያ — ሲዳማ ተዛማጅ ማህበረሰቦች መካከል የተፈጠረው ሊንጉዊስቲካዊ ግንኙነት

| የቋንቋ ማህበረሰብ | ሊንጉዊስቲካዊ የቃላት ተመሳሳይነት ከመቶ ስሌት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከምባትኛ | ጥምባርኛ | አላብኛ | ሲዳምኛ | ጌዴኦኛ | ቡርጂኛ | ሊቢዲኛ | ቀቤንኛ |
| ሀዲይኛ | 61 | 58 | 58 | 58 | 51 | 41 | ? | ? |
| ከምባትኛ | | 86 | 82 | 64 | 54 | 40 | ? | ? |
| ጥምባርኛ | | | 82 | 64 | 58 | 41 | ? | ? |
| አላብኛ | | | | 67 | 57 | 42 | ? | ? |
| ሲዳምኛ | | | | | 63 | 47 | ? | ? |
| ጌዴኦኛ | | | | | | 45 | ? | ? |
| ማረቆ/ሊቢዲኛ | | | | | | ? | ? | ? |
| ቀቤንኛ/ በወልቅጤ | | | | | | | ? | |

*Source*: F.P. Cotterell, *Born At Midnight* (1973). p. 109;

ላጵሶ ጌ. ድሌቦ ፣ የምርትና የባህል ዘመቻ ገጽ 30 ።



የአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት የሁለቱ ተከታታይ የኢማም አህመድ ግራኝ ጦርነትና የታላቁ የሕዝቦች ፍለሳ አንድ ሌላ ታሪካዊ ውጤት አስከትሏል ። ይኸውም በአገሪቱ በደቡብ ፣ በምስራቅ ፣ በመሀልና በመሀል—ምዕራብ አካባቢዎች በእርሻና በንግድ ተግባራት በተሰማሩ ነባር ማህበረሰቦች ውድቀት በሥፍራና በሕዝብ ብዛት የሦስቱ የሶማሌ ፣ የአፋርና የኦሮሞ ማህበረሰቦች ዕድገትና መስፋፋት ሁኔታ ነው ። በመሆኑም እስከ ዛሬ በተገኙ የሰነድ ፣ የሊንጉዊስቲክስና የትውፊት መረጃዎችና ጥናቶች መሠረት የማህበረሰቦቹን የዕድገትና የመስፋፋት ሁኔታ በሥፍራና በጊዜ እንደሚከተለው ባጭሩ ማገናዘብ ወቅታዊም ተገቢም ሥራ ነው ።

በዚህ ረገድ በአፍሪካ ቀንድ የሶማሌን የዘር አመጣጥና የጐሳ ስርጭት በሚመለከት ፣ በጥንታዊ የሰነድ መረጃዎችና በቅርብ ምዕተ ዓመታት በተፈጠሩ ትውፊቶች መካከል በጥናትና ምርምር የማይገለጽ ልዩነት ይታያል ። በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም በአራቱ የኢትዮጵያ ፣ የጂቡቲ የሶማሊያና የኬንያ አጐራባች አገሮች መካከል የተከፈለው የሶማሌ የቋንቋ ማህበረሰብ ከመልከዓ ምድራዊ አሰፋፈርና ከማኅበራዊ ጥንቅር አኳያ በሰሜን በድር ፣ በኢሳቅና በዳሮድ ጐሳዎች ፣ በደቡብ ምስራቅ በዋቤ ሸበሌ ሸለቆ በእንስሳት እርባታና በእርሻ ተግባራት በሚተዳደረው የሀዊያ ጐሳ፣ በደቡብ ምዕራብ በዋቢ ሸበሌና በጁባ ሸለቆዎች ክልል በቅይጥ የእርሻና የእንስሳት እርባታ ተግባራት በሚኖረው የሰብ ጐሳ ፣ በሩቅ ደቡብ ምስራቅ በጣና ፣ በጁባና በዳዋ ወንዞች ክልል በዳሮድ ጐሳና በሦስቱ በዕደ ጥበብ ተግባራት በሚኖሩ ማለትም የቱማል ፣ የይባርና የምድጋን ካስት ወገኖች ይከፈላል ።[11]

በቅርብ ዘመን በተፈጠሩና በዘር ሐረግ በቀረቡ የአግል ፣ የሄል ፣ የኤረር ፣ የድር ፣ የዳሮድና የኢሳቅ ጐሳ ትውፊት መሠረት ፣ የሶማሌ የተለያዩ ጐሳዎች በመጤ የአረብ ቅዱሳን ሼኮች ትውልድ የተገኙት ፣ በግምት ከስምንተኛው ምዕተ ዓመት እስከ አስራ አምስተኛው ምዕተ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ፣ ከነቢዩ መሀመድ ዘር ወይም ወገን ነው ።

ነገር ግን ይህ የሶማሌ ሕዝብ ከነቢዩ መሀመድ ትውልድ የመጣ የአረብ ዘር ነው የሚለው አዲስ ትውፊት ከዚህ በላይ እንደተባለው ፣ በሥፍራና በጊዜ በሰነድ ከተጻፈው ከሶማሌ ጥንታዊ ታሪክ ጋር አብሮ አይሄድም ። በዚህ አኳያ የሶማሌ የሀዊያ ጐሳ በደቡብ ምስራቅ በሞቃዲሾ—ጁባ ክልል እስከዛሬም በሚገኝበት አካባቢ ኢብን ሰይድ (1214—1274) የአረቡ ደራሲ በአስራ ሦስተኛው ምዕተ ዓመት በጻፈው መጽሐፍ ለመ

[11] Trimingham, *Islam in Ethiopia*, pp. 210-211, Lewis *Peoples*, pp. 51-55

ጀመሪያ ፣ ጊዜ በታሪክ ሰነድ በስሙ ታውቋል ። [12] የሶማሌ የቋንቋ ማህበረሰብ በታሪክ ሰነድ ለመጀመሪያ ጊዜ በስሙ የታወቀው ግን በአስራ አምስተኛው ምዕተ ዓመት በኢትዮጵያ የአፄ ይስሐቅ (1414—1429) ዜና መዋዕል በአዳሉ የአካባቢ መንግሥት ውስጥ ነው ። [13]

በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት በኢማም አህመድ ግራኙ ጦርነት (1524—1543) ዘገባ አሁንም በአዳሉ የአካባቢ መንግሥት ውስጥ ከታላቁ የሐረር ከተማ በስተምሥራቅና በስተደቡብ በዛሬው ኦጋዴንና ድሬዳዋ ክልል የሶማሌ የተለያዩ የጊሪ ፣ የመራሃን ፣ የይበሪ ፣ የባርትሬ ፣ የሀብርማጋዲ ፣ የያባሬ ፣ የሀዋያ ፣ የጃራን ፣ የማዘር ፣ የበርሱክና የጉርጉራ ጐሳዎች [14] ዘሙባሬህ ፣ ባርዛራህ ፣ ያቆላህ ፣ ጃሳር ፣ አራብታክሃና አልቃ ከተባሉ [15] የሀርላ አጐራባች ጐሳዎች ጐን በሥፍራና በጐሳ መሪዎች ተለይተው " ሶማሌ " በሚል ጥቅል የቋንቋ ማህበረሰብ ስም በዝርዝር ተመዝግበው ሲገኙ ፣ በሌላ በኩል አግል ፣ ሂል ፣ ዳሮዳና ኢሳቅ በተባሉ የአረብ ቅዱሳን መጢዎች የትውልድ ሐረግ የሶማሌ ሕዝብ ከነቢዩ መሀመድ የተገኘው የአረብ ዘር ነው የሚለው አዲሱ ትውፊት ግን በአስተዋዩ የአረብ ደራሲ ማለትም በአረብፋ ቂህ አብሮ አልተጻፈም ።

በመሆኑም ሶማሌ ከነቢዩ ሐመድ ወገን የተገኘው የአረብ ዘር ነው የሚለው ትውፊት ከጊዜ በኋላ በቅርቡ ዘመን የተፈጠረው የራሱን ጥንታዊ በሰነድ የሰፈረውን ታሪክ አንብቦ የማያውቀው ሕብረተሰብ አዲስ ሃይማኖታዊ ተረት ነው ለማለት ይቻላል ።

የሶማሌን የታሪክ ዘገባና ትውፊት በማገናዘብ የተካሄዱ ምሁራዊ ጥናቶች እንደሚያመለክቱ ፣ ዛሬ በሶማሌ የዘር ሐረግ የሚጠቀሱት ኤረር ፣ ድር ፣ ዳሮድና ኢሳቅ የተባሉ የትውፊት ጐሳ አባቶች በታሪክ ሰነድ ጊሪ ፣ መራሃን ፣ ይበሪ ፣ ባርትሬ ፣ ሀብርማጋዲ ፣ ያባሬ ፣ ሀዋያ ፣ ጀራን ፣ ማዛር ፣ በርሱክና ጉራጉራ ለተባሉ የሶማሌ ጐሳዎች ከጊዜ በኋላ የተሰጡ ትውፊታዊ ስሞች ናቸው ።

በዚህ አኳያ በሐረርና በዋቢ ሸበሌ መካከል በታሪክ ሰነድ የታወቁ ጥንታዊ የጊሪ ፣ የበርሱክ ፣ የባርትሬ ፣ ያባሬ ፣ የጉርጉራና የመራሃን ሶማሌ ማለትም የኦጋዴን ሶማሌ ጐሳዎች በአዲሱ ትውፊት የዳሮድ [16] ሶማሌ ፣

[12] Doresse, *Histoire Sommaire*, p. 184.

[13] *Ibid*., p. 185.

[14] Arab-Faqih, *Conquete*, pp. 14, 34-35, 44-45, 69, 118-119.

[15] *Ibid., Doresse, Histoire Sommaire*, p. 183.

[16] Doresse, *Histoire Sommaire*, pp. 210-211; Lewis, *Peoples*, pp. 20-22



በሐረርና በጂቡቲ ፣ በዜላና በበርበራ መካከል በሰነዱ ጥንታዊ የሀብርማጋዲና የይበር ሶማሌ ጐሳዎች በአዲሱ ትውፊት ደግሞ የኤረር ፣ የድር ፣ የኢሳ ፣ የኢሳቅ ፣ የጋዳቡርሲ ፣ የሀብርአዋል [17] ሶማሌ ፣ በሩቅ ምስራቅ ከኤደን ባህረሰላጤ አካባቢ ጀምሮ የሰፈረው የሰነዱ የሀርቲ ሶማሌ ጐሳ በአዲሱ ትውፊታዊ የትውልድ ሐረግ የዳሮድ ሶማሌ ማለትም የሚጀርቴን ፣ የደልባሃንታና የዋርሰንጌሊ [18] ሶማሌ ጐሳዎች ተብሎአል ።

በአፍሪካ ቀንድ የተለያዩ የሶማሌ ጐሳዎች ከሰሜን ምስራቅ ወደ ምዕራብ ፣ ወደ ያቡብና ወደ ደቡብ ምዕራብ በፍለሳ እንቅስቃሴ የተሰራጩት በሁለቱ ጥንታዊ የባንቱ አዛኒያና የአዳል አገሮች ላይ እንደሆነ ይታወቃል ። በዚህ ረገድ የአዳል አካባቢ አገርና መንግሥት በሦስቱ የሶማሌ ፣ የአፋርና የኦሮሞ ማህበረሰቦች የተያዘው ከታላቁ የኢማም አህመድ ጦርነት በኋላ በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት በሁለተኛው አጋማሽ ሲሆን ፣ በ1580ዎቹ መጨረሻ የአዳሉ ታሪካዊው የዜላ ክፍለ ሀገርና የወደብ ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ በሶማሊዎች ተያዘ ። [19]

በአፍሪካ ቀንድ የሶማሌ ሕዝብ ታሪካዊ አመጣጥና ስርጭት ከዚህ በላይ አጭር የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ይህንን መሠረታዊ የሕዝብን የታሪክ ጉዳይ በተመለከተ የዛሬ የሶማሊያ መንግሥት ባለሥልጣኖች የፖለቲካ ተረት የሚጫወቱ ይመስላሉ ።

ለምሳሌ የሶማሊያ መንግሥት መሪዎችና ባለሥልጣኖች በአንድ በኩል ከ3500 ዓመታት በፊት የግብጿ ንግሥት የሃትሸፕሱት መርከበኛው ሰዓሊ በቀይ ባህር ዳርቻ ላይ የቀረፀውን የፑንታውያንን ታሪካዊ ስዕል ቅጂን በሞቃዲሾ ከተማ በአንድ ሙዚየም ውስጥ በማኖር በአፍሪካ ቀንድ የጥንቱ የፑንት ሕዝብና መንግሥት የሶማሊያ ጥንታዊ ሕዝብና መንግሥት ነበር በማለት ያምናሉ ። [20]

በሌላ በኩል ደግሞ አግል ፣ ሄል ፣ ዳሮድ ፣ ኢሳቅ . . . ወዘተ በተባሉ የአረብ ቅዱሳን መጤዎች የትውልድ ሐረግ የሶማሌ ጐሳዎች ከነቢዩ መሀመድ ተወላጅ አረቦች ናቸው በማለት ያምናሉ ። [21] የአካባቢው ጥንታዊ የፑንት ፣ የአዛኒያ ፣ የሀርላና የአዳል ሰዎች ፣ መንግሥታትና ታሪክ በሙሉ የዛሬው ሶማሌ ጐሳዎች የጥንት ሕዝቦች መንግሥታትና ታሪክ ናቸው

[17] *Ibid., Histoire Sommaire*, p. 210; *Peoples*, pp. 23-26,51-56.

[18] *Ibid., Histoire Sommaire*, pp. 31,211; *Peoples*, pp. 19-21.

[19] Ibid., *Histoire Sommaire*, p. 236.

[20] *Ibid*., pp. 47-48.

[21] Lewis, *Peoples*, pp. 15-24.

በማለትም ያምናሉ ያስተምራሉ ። በዚህም እምነታቸውም በአጐራባች አገሮች ላይ የወረራ ጦርነት በማካሄድ በአካባቢው ሽብር ይፈጥራሉ ።

ለዚህ አባባል በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ አዲሱ የሶማሊያ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ በተከታታይ የከፈተቻቸው ጦርነቶች ምሳሌዎች ናቸው ። በተጨማሪም የሶማሌ ዜጋና የወረራ መሪ ነበር በማለት የሶማሊያ መንግሥት መሪዎችና ባለሥልጣኖች በቅርቡ ለአዳሉ ኢማም አህመድ ግራኙ በሞቃዲሾ ከተማ የመታሰቢያ ሐውልት አቁመውለታል ። እንዲሁም የአረብ መንግሥታት ሊግ አባል መንግሥት በመሆን የፖለቲካና የኢኮኖሚ እርዳታ ለማግኘት ሲሉ የአገራቸው ሕዝብና መንግሥት በአፍሪካ አህጉር “ የአረብ ” ሕዝብና መንግሥት ነው በማለት በዓለም ፊት በይፋ አሳውቋል ።

ይህ ሁሉ የተረት ቅኝት ከእውነተኛው የሶማሌ ሕዝብ ታሪክ ጋር አብሮ የማይሄድ የውሸት ነገር ነው ። ለሶማሊያ መንግሥትና ሕዝብ ጥሩ የአገር ግምባታ መሠረትና መሣሪያ የሚሆን ነገርም አይደለም ። በአካባቢው የሶማሊያ መንግሥት የወረራ ፖሊሲ ከዚህ የጐሳ ተረት ጋር የተያያዘ ነገር ስለሆነ ከሁሉ በፊት ለራሱ ለአዳጊው የሶማሊያ ሕዝብና መንግስት በጣም ጐጂ ነገር ነው ። በመሆኑም ለሶማሊያ መንግሥት ለራሱ ጥቅም በተለይ ለአፍሪካ ቀንድ አካባቢያዊ ሰላምና ልማት ሲባል በአጠቃላይ በሶማሊያባለ ሥልጣናች ዘንድ የጐሳ ተረትና ከዚሁ ጋር የተያያዘው የጦረኝነት ፖሊሲ መታረም ይኖርበታል ።

በአፍሪካ ቀንድ ይህ የሶማሌ ሕዝብና ታሪክ ጉዳይ በአካባቢው የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች በጥብቅ ይመለከታል ። አንደኛ ፥ ከሶማሊያና ከጂቡቲ አጐራባች ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር በቋንቋ ፥ በሃይማኖትና በታሪክ የጠበቀ አንድነት ያላቸው የሶማሌ ሁለቱ ታላላቅ የኢሳና የኦጋዴን ማህበረሰቦች ኢትዮጵያውያን ናቸው ። ሁለተኛ ፥ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢያዊ ሰላም ፥ ትብብርና ልማት ለሦስቱ የኢትዮጵያ ፥ የሶማሊያና የጂቡቲ መንግሥታት አንድ አስፈላጊና ተቀዳሚ የፖለቲካም የኢኮኖሚም ጉዳይ ነው ። በእነዚህና በሌላም ብዙ መሠረታዊ ምክንያቶች ለኢትዮጵያውያን የሶማሌ ጉዳይ በገለልተኝነት የሚታይ ነገር ሊሆን አይችልም ።

የአፋር ስም “ ደንኬል ” በሚል ስያሜ በታሪክ ሰነድ ለመጀመሪያ ጊዜ የታወቀው በአሥራ ሦስተኛው ምዕተ ዓመት አረቡ ኢብን ሰይድ (1214—1274) የጂኦግራፊያ ምሁር በጻፈው መጽሐፍ ነው [22] ። የአፋር ማህ

[22] Trimingham, *Islam in Ethiopia*, p. 171.



በረሰብ በታሪክ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ የመኖሪያው መደበኛ ሥፍራ በጠረፍ ከባቤልማንደብ ጀምሮ እስከ መካከለኛው አዋሽ ሸለቆ ድረስ ያለው ቆላማ መሬት ሲሆን አገሩም የጥንታዊው ይፋት—አዳል የአካባቢ መንግሥት ግዛት እንደነበር በዚሁ ጥናት ከዚህ በፊት ተገልጾአል ።

በኦሮሞ የፍለሳ ግፊት በ1577 ታላቁ የአዳል ሱልጣኔት በሰሜንና በደቡብ በሁለት አካላት ማለትም በአውሳ ኢማማትና በሐረር ኤሜሪያት ከተከፈለበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1672 ድረስ በመካከለኛው አዋሽ ሸለቆ የአፋር ምድር ለአዳሉ ሰሜናዊ የአውሳ ኢማማት መሠረትና ማዕከል ሰለ ነበር በአገሪቱ ታሪክ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በዘልማድ የአፋር ሕዝብና ምድር በስህተት “ አዳል ” እየተባለ ይጠራ እንደነበር ይታወሳል ።

በመጨረሻም በአሥራ ሰባተኛው ምዕተ ዓመት የአዳሉ የአውሳ ኢማማት በሦስቱ የሶማሌ ፥ የኦሮሞና የአፋር ማህበረሰቦችና ጐሳዎች ከየአቅጣጫው ለረጅም ጊዜ ተከቦ ከተደመሰሰ በኋላ [23] በአካባቢው ማለትም በመካከለኛው አዋሽ ሸለቆ የተነሳው የአፋር የጐሳ “ ሱልጣኔት ” ራሱ “ አውሳ ” በሚል በጥንታዊው የአዳል ስያሜ እስከ አብዮቱ ማለትም እስከ ሱልጣን አሊሚራ ውድቀት ድረስ ይጠራ እንደነበር አይዘነጋም ።

የኦሮሞ ሕዝብ በአፍሪካ ቀንድ ለመጀመሪያ ጊዜ በታሪክ ሰነድ “ ጋላ ” በሚል ስም ተጽፎ የተገኘው በአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ሲሆን እርሱም በዘመኑ በርቱማና ቦረና በተባሉ ሁለት ዋና ጐሳዎች የተከፈለ ማህበረሰብ ነበር ። እስከ ዛሬ ድረስ የተገኙ የሰነድ የሊንጉዊስቲክስና የትውፊት መረጃዎች በአንድነት እንደሚያመለክቱት ማህበረሰቡ በ1520ዎቹ መጀመሪያ በፍለሳ ስምሪት የተንቀሳቀሰው በደቡብ ምሥራቅ በግምት በአባያታ ሐይቅና በገናሌ ወንዝ መካከል ከቦረና አካባቢ ነበር ። [24]

በኦሮሞ አገር አቀፍ የፍለሳና የሰፈራ ታሪክ የማህበረሰቡ የጐሳ ድርጅትና የገዳ ሥርዓት ቁልፍ ነገሮች ናቸው ። በመሆኑም በአባ ባሕርይ የተመዘገበው የኦሮሞ የበርቱማና የቦረና የዘር ሐረጎች እንደሚከተለው ቀርቦአል ። እነዚህ የኦሮሞ የጐሳ ስሞች ከአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት በኋላ በምሥራቅ ፥ በደቡብ በመሀልና በምዕራብ ኢትዮጵያ ብዙ ጥንታዊ ሕዝቦችንና አገሮችን ተተክተው ስለሚገኙ ለታሪክ ጥናት አንድ ታላቅ


[23] *Ibid.*, p. 97; Dorese, *Histore Sommaire*, pp. 236-237.

[24] H.S. Lewis, " Origins of the Galla and Somali," *Journal of African History*, vol. 7, No. 1 (1966); Bahrey, *History of the Galla*, pp. 110-129; Asmarom Legesse, *Gada*, pp. 6-10; Braukamper, *Hadiya*, pp. 144-153.

የመረጃ ምንጭ ናቸው ። ከተጠቀሱት ሁለት ዋና ጐሳዎች የቦረና ወገን ቱለማና ሜጫ በተባሉ ፤ ሁለት ዘርፎች ተመድበው በመሀልና በምዕራብ ኢትዮጵያ ሰፈሩ ። የበርቱማ እንጃው ደግሞ በኢቱ በወረንጢሻ (በአርሲ) ፤ በከረዩ በወሎ . . ንዑስ ጐሳዎች ተከፍሎ በደቡብ ፤ በምስራቅና በሰሜን ኢትዮጵያ ሰፈረ ። የሁለቱም ወገኖች የፍለሳና የሰፈራ ዝርዝር ባጭሩ የሚከተለው ነው ።

## መንጠረዥ 5

## የኦሮሞ የዘር ሐረግ ከባሕርይ ዘገባ






በግምት ከ1520ዎቹ እስከ 1620ዎቹ ባለው በአንድ ምዕተ ዓመት ጊዜ ውስጥ በደቡብ ምስራቅ ከቦረና በፍለሳ ስምሪት በመንቀሳቀስ የበርቱማ ኦሮሞ ጐሳዎች በምስራቅና በሰሜን በጥንቱ የባሌ ፤ የደዋሮ ፤ የአዳል ፤ የአርጐባ ፤ የፈጠጋር ፡ የይፋት ፤ የአንጐትና የላስታ አገሮች እስከ ትግራይ ወሰን ድረስ እንደአካባቢው ሁኔታ በሙሉ ወይም በከፊል ሰፈሩ ። የቦረና ኦሮሞ ጐሳዎች ደግሞ በተመሳሳይ እንቅስቃሴ በደቡብ ፤ በመሀልና በመሀል — ምዕራብ በጥንቱ የሀዲያ ፤ የሻርካ ፤ የማያ ፤ የዋጅ ፤ የገበርጌ ፤ የወረባ ፤ የሸዋ ፤ የአማራ ፤ የበጌምድር ፤ የደምብያ ፤ የጉጃም ፤ የዳሞት ፤ የጋፋት ፤ በጊቤ—አባይ—ዴዴሳ ክልል በነባሩ የሂናሮ (እናርያ) ፤ የአንጎሎ ፤የቦሻ ፤ የጂማ ፤ የቢዛሞ ወዘተ አገሮች ላይ ተመሳሳይ የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴዎችን አካሄዱ ።

ለዚህ ታላቅ የኦሮሞ ጐሳዊ የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴ መሳካት አስተዋጽኦ ያደረጉ የውስጥና የውጭ ሁኔታዎችና ኃይሎች ብዙና መሠረታዊ ናቸው ። ለኦሮሞ አገር አቀፍ የፍለሳና የሰፈራ ስምሪት መሳካት ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ የማህበረሰቡ ጐሳዊ ሁኔታዎችና ኃይሎች የገዳ ሥርዓት ፤ የሉባ ስልተ ጦርነት (የደፈጣ ውጊያ) እና በዘመኑ የኦሮሞ ሰዎች ባዕዳንን እንደራሳቸው አድርገው የሚቀበሉባቸው የጉዲፈቻ እና የሞገሳ ሥርዓቶችና ማኅበራዊ ሕጐች ናቸው ።

በዘመኑ የገዳ ሥርዓት የኦሮሞ ወንድ የሕብረተሰቡ አባሎች ከልደት እስከ አርባ ስምንት ዓመት ዕድሜ ድረስ እያንዳንዱ ወቅት የስምንት ዓመት ጊዜ በሚወስድ የሙጫ (ሕፃን) ፤ የኢልማ (ልጅ) ፤ የጉርባ (ወጣት) ፤ የቁንዳላ (ጐልማሳ) ፤ የሉባ (ዕጩ ጦረኛ) እና የገዳ (መሪና አዝማች) ስድስት ተከታታይ በመደብና በሀብት ሳይሆን በወንድ ጾታ ፤ ዕድሜና ትውልድ ክልሎች ወይም ዘመናት ተመድበው በተግባራዊ ትምህርትና ልምድ የሕብረተሰቡን ወግና ልማድ ፤ የአስተዳደር ፤ የጦርነት የዘመቻና የወረራ ስልቶችና ሕጐችን ደረጃ በደረጃ እየተማሩ በምርት ግንኙነትና በመደብ ሥርዓት ያልተከፈለውን ሕዝብ በልዩ ልዩ መስኮችና መንገዶች የሚያገለግሉበት አንድ ልዩ ማህበራዊ ሥርዓትና አሠራር ነበር ።

“ በዚህ ጐሳዊ ሥርዓት መሠረት ከ40 እስከ 48 ዕድሜ ክልል የሚገኙ የኦሮሞ ወንዶች ለስምንት ዓመት ጊዜ የሕብረተሰቡን የአመራር ሥልጣንና ተግባር በመያዝ ያለፈው ትውልድ (ማለትም የገዳ ትውልድ) ያልደረሰበትን አገር በወረራ ሂዶ መያዙ የሥርዓቱ ባህላዊ ሕግና ግዴታ ነበር ። በዚህ በገዳ ሕግና ሥርዓት እየተመሩ የኦሮሞ ሰዎች ከ1520 እስከ 1600 ድረስ በ80 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ብቻ በደቡብ ፤ በምስራቅ በመሀል፣ በሰሜንና በምዕራብ ኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥቱን ማዕከላዊ መንግሥት ጨምሮ በከፍተኛ የዕድገት ደረጃ የተደራጁ አያሌ አገሮችን ሕዝቦችንና

ንውስ መንግሥታትን በጦርነት በማሸነፍ በመላው አገሩ በፍለሳና በሰፈራ ተስፋፉ ”። [25]

በባሕርይ ዘገባ መሠረት ፤ በምርት ግንኙነትና በመደብ ሥርዓት ገና ያልተከፈሉና ሉባ በተባለው ጉሳዊ የጦር እለቃ የሚመሩ የኦርሞ ሰዎች በዘመኑ ፤

“ እንደ ሌላ ሕዝቦች ንጉሥ ወይም ጌታ የላቸውም ። ነገር ግን ለስ ምንት ዓመት በሉባው ይገዛሉ ። በስምንተኛው ዓመት ፍጻሜ ላይ ሌላ ሉባ ይመርጣሉ ። የቀድሞው ሉባ እመራሩን ለሚቀጥለው ይለቃል ። ይህንንም ስነ ሥርዓት በተወሰነ ዘመን ያከናውናሉ ። ሉባ በአንድ ዘመን የተገረዙ ሰዎች መጠሪያ ስም ነው ። የግዝረታቸውም ሕግ ይህ ነው ። እንዱ ሉባ በተሰየመ ጊዜ ሁሉም የበርቱግና የቦረና ወገኖች አዲስ የጋራ ስም ይመርጣሉ ። ” [26]

ባጭሩ በኦርሞ የገዳ ዘመንና ሥርዓት “ ሉባ ” ለስምንት ዓመት ጊዜ የኦርሞ የጦርም የሕብረተሰብም መሪና አዝማች ነበር።የጉሳ አለቃም፣ ዳኛም መሪም ነበር ። የሉባ ጦር ዓይነተኛው ድርጅትና ስልት ደግሞ የደ ፈጣ ውጊያ ነው ። በሌላ በኩል በዘመኑ የኢትዮጵያ “ ጪዋ ” የተባለው ማዕከላዊ የአፄው ጦር ሆነ “ መለሳይ ” የተባለው የአዳሉ የአካባቢ ጦር ማለትም የአፄውና የሱልጣኑ ፊውዳል ሠራዊት ዓይነተኛው ድርጅትና የጦርነት ስልት የግምባር ውጊያ ነበር ። በዘመኑ የአፄው የጪዋ ጦር በግ ምባር ሲመጣባቸው ኦርሞዎች ከእንስሶቻቸው ጋር አካባቢውን ይለቃ ሉ ። ከዚያ በኋላ በድንገት እየመጡ በአጼው ጦርና ሹማምንቶች ላይ የደ ፈጣ ውጊያ ይከፍታሉ ።

በ1550ዎቹ መጀመሪያ በቢፍሌ ሉባ (1546—1554) ዘመን አፄ ገላውዴዎስ 150 ነፍጠኞችን በጀብደኛው ቤርሙዴዝ አዝማችነት በደ ዋሮ አገር በኦሮሞ ግምባር አሰማራቸው ። በዚህ ወቅት የፖርቱጋል ነፍ ጠኞች በደዋር የንጉሡን መምጣት እየጠበቁ ከኦርሞ የሉባ ጦር ጋር የነ በራቸውን የትጥቅ መስተጋብር አዝማቹ ቤርሙዴዝ በሸንፈት ከሸሸ በኋላ እንደሚከተለው ይገልጻል ። በፖርቱጋሉ የነፍጠኞች አለቃ ቃል ፤

“ እኛ ተዘጋጅተን ስንጠብቃቸው ጋሎች አንድ ቀን ደረሱ ። ብዛ ታቸውም ከቁጥር በላይ ነበር ። የሰልፋቸውም ሁኔታ ያልሰለጠነ ሕዝብ ሰልፍ ሳይሆን በሥርዓቱ የተደራጀ ስምሪት ነበር ። ስኳድሮን በሚመስሉ አካላት (ቡድኖች) ተሰልፈው ቀረቡ ። ፊታውራሪው ቡድን እኛን ባየ ጊዜ የደጀኑ ኃይል እስኪደርስ ድረስ ቆሞ ጠበቀ ። ከዚያ በኋላ ሁሉም

[25] ላጵሶ ጌ. ድሌቦ ፤ የምርትና የባህል ዕድገት ዘመቻ ፡ ገጽ 30

[26] Bahrey, *History of the Galla*, p. 115



በአንድነት ወደፊት በመምጣት በአጠገባችን የእኛ ጥይት በማይደርሳ ቸው ርቀት ሰፈሩ ። ቁጥራችን ከእነርሱ ብዛት ጋር የማይመጣጠን ስለሆነ እኛም ለውጊያ ወደ ጋሎቹ ሳንሄድ በሰፈራችን ተቀመጥን ።

“ ሰፈራችንም ጠላቶቻችንን ከላይ ወደታች በሚያሳይ ኮረብታ ላይ ነበር ። በዚህ ሥፍራ የንጉሡን መምጣት እየጠበቅን ራሳችንን ለአ ሥራ ሁለት ቀናት ያህል ጊዜ ስንከላከል ቆየን ። በዚህ ጊዜ ብዙ ጋሎችን በጥይት ገደልን ። በውጊያ ጊዜ ጠላቶቹ በታላቅ ድፍረትና ፍጥነት ወደ እኛ ይመጡ ነበር ። በአንድ በኩል ንጉሡ ስለዘገየ በሌላ በኩል ደግሞ ባሩዳችን ስለአለቀብን ሰፈራችንን ለቀን ወደ ንጉሡ ፍለጋ ሄድን ። ጋሎቹ ግን በክትትል ተነስተው አላባረሩንም ።

“ ከንጉሡ ጋር በመንገድ ተገናኘን ። እርሱም አገሩ በጋሎቹ እጅ መያዙን ሰምቶ በኃይል አዘነ ። አለቀሰም ። በዚህ ጊዜ ሦስቱ የባሌ ፣ የደ ዋሮና የሀዲያ አገሮች በጋሎች ተይዘውበት ነበር ። በስፋት ባሌና ደዋር በአንድነት ፖርቱጋልንና ከስታሊን ይሆናሉ ። በመልንዲ (በዛሬው ኬ ንያ) ወሰን የሚገኘው ሀዲያ አገር ብቻውን በስፋት የፈረንሳይን አገር በ ሙሉ ያክላል ። ” [27]

ቢታሪክ በየትም ሥፍራና በምንም ጊዜ የሰውን ጉልበትና ጊዜ ለመ በዝበዝ የሚያስችል መደባዊ የኢኮኖሚ መሠረት ከመንግሥት ድርጅት ጋር የሌለው ማኅበረሰብ በጠላት ላይ የበላይነትን ቢያገኝ ጠላቶቹን ከመ ግደል ወይም በመብትና ግዴታ የራሱ ሕብረተሰብ ውስጣዊ አባሎች አድርጎ ከመቀበል ሦስተኛ አማራጭ መንገድ አይኖረውም ። በመደብ ያልተከፈለ ሕብረተሰብ ጠላቱን እንደገባር ለመግዛትም ሆነ እንደባርያ ለመጠቀም አስፈላጊ የኢኮኖሚና የፖለቲካ መሠረት የለውምና ።

በዚህ አኳያ በገዳ ዘመንና ሥርዓት የኦርሞ ማህበረሰብ ባዕዳን ግለ ሰቦችንና ጉሳዎችን በጉሳዊና ባህላዊ ሥነ ሥርዓት በመብትና ግዴታ የራሱ ሕብረተሰብ አባሎችና አካሎች አድርጎ የሚቀበላቸው ጉዲፈቻና ሞጋሳ የተባሉ ሁለት ማህበራዊ ሥርዓቶችና ሕጎች ነበሩት ። [28]

በአጭሩ በአስራ ስድስተኛውና በአስራ ሰባተኛው ምዕተ ዓመታት የኦርሞ ሰዎች በጉዲፈቻና በሞጋሳ ሥርዓቶች ፣ አሠራሮችና ሕጎች በብዙ አካባቢዎች ብዙ ነባር ሕዝቦችን እንደራሳቸው ሰዎች በመቀበልና በማ ዋሀድ በአጭር ታሪካዊ ዘመን በአገሪቱ የራሳቸውን የጉሳ ቁጥር አበዙ ።

[27] Bermudez, *A Short Account of the Embassy with the Patriarch Joao Bermudez brought from the Emperor of Ethiopia* In Castanhoso, *The portuguese Expedition to Abyssinia in* 1541-1543, tr. and ed. by *R.* Whiteway (1902). pp 229-230.

[28] ላጵሶ ጌ. ድሌቦ ፤ የምርትና የባህል ዕድገት ዘመቻ ፤ ገጽ 30

በሌላ በኩል በሰፈሩበት አካባቢ ሁሉ የነባር ሕዝቦችን ከፍተኛ ባህልና የግብርና ተግባር በመማር እንዲሁም የእስልምናና የክርስትና ሃይማኖቶችንና ሥርዓቶችን በመቀበል በዘመኑ በማህበራዊ ዕድገት በዝቅተኛ ደረጃ የነበሩ የኦሮሞ ጐሳዎች ራሳቸው በባህላዊ ለውጥና ዕድገት ከአካባቢ ሕዝቦች ጋር እየተዋሀዱ በመሄድ ከጊዜ በኋላ ለዛሬው የኢትዮጵያ በሀውርታዊ ሕብረተሰብና መንግሥት ዕድገትና ጥንካሬ የራሳቸውን ታሪካዊ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል የኦሮሞ ውስጣዊ የገዳ ፣ የሉባ ፣ የጉዲፈቻና የሞጋሰ ማህበራዊ ሥርዓቶች ፣ ሕጐች ፣ ድርጅቶችና አሰራሮች ብቻቸውን የማህበረሰቡን ታሪካዊ የፍለሳና የሰፈራ ሁኔታዎችን በትክክል አይገልጹም ። ሊገልጹም አይችሉም ። በዚህ ረገድ ለማህበረሰቡ አገር አቀፍ የፍለሳና የሰፈራ ድል ወሳኝ አስተዋጽኦ ያደረገው ሁኔታ የአገሪቱን ሁለቱንም ማለትም የአካባቢ የሱልጣኖችንና የማዕከላዊ አፄዎችን የፖለቲካ ፣ የጦርና የኢኮኖሚ መሠረቶችንና መሣሪያዎችን ያፈራረሰው የ1524—1543 የአዳሉ የኢማም አህመድ ግራኙ የአመፅ ጦርነት ነው ።

ከዚህ በላይ በጥቅል በተዘረዘሩ የውስጥና የውጭ ምክንያቶች የኦሮሞ ተከታታይ ዘጠኙ የመልባህ ፣ የሙዳና ፣ የኪሎሌ ፣ የቢፎሌ ፣ የምችሌ ፣ የሀርሙፋ ፣ የሮባሌ ፣ የቤርሙጂና የሙላታ ሉባዎች በግምት ከ1520 እስከ 1600 ድረስ በስምንት አሥርታት ውስጥ ማህበረሰቡን በፍለሳና በሰፈራ ስምሪት እንደሚከተለው በአገር አቀፍ ደረጃ እንቀሳቀሱ ። እስፋፉ ።[29] በዚህ በፍለሳና በሰፈራ ስምሪት ፤

የተለያዩ የኦሮሞ ጐሳዎች በመልባህ ሉባ (1522—1530) አመራር ከቦረና አካባቢ የገላን ወንዝ ተሻግረው ከምዕራብ በኩል ወደ ባሌ አገር ደረሱ ። ቀጥሎም በሙዳና ሉባ (1530—1538) ዘመን የዋቢን ወንዝ ተሻግረው የተወሰኑ ወገኖች በባሌ አገር በነዋሪነት ሰፈሩ ። ወደፊት በመቀጠል በኪሎሌ ሉባ (1538—1546) ጊዜ ባሌን አልፈው ወደ ደዋሮ ማለትም ወደ ሰሜናዊ ሐረርጌና አዋሽ ሸለቆ አካባቢ ደረሱ ። በቢፍሌ ሉባ ( 1546—1554 ) አመራር ከደዋሮ ወደ ፈጠጋር ማለትም ወደ ዛሬው አርሲ ፣ የረርና ከረዩ አካባቢ ደረሱ ። በምችሌ ሉባ (1554—1562) ዘመን ከፈጠጋር በአዋሽ ወንዝና በዝዋይ ሐይቅ ክልል ወደ ዋጅ ወደ ገበርጌ ወደ ወረባ አገሮች ደረሱ ። በዚህ በምችሌ ዘመን የኦሮሞ ሰዎች የበቅሎና የፈረስ አጠቃቀም በመማር በጦር ድርጅትና ስልት በፍለሳ እንቅስቃሴያቸው ፈጣን የዕድገት ለውጥ አመጡ ።[30] በደረሱበት አካባቢ ሁሉ በነዋሪነት መስፈርም ጀመሩ ።

[29] Bahrey, *History of the Galla*, pp. 115-125.
[30] *Ibid.*, p. 117.



የቦረና ኦሮሞ ጐሳዎች በሀርሙፋ ሉባ (1562—1570) ጊዜ በሰሜኑ ዲጋ በዛሬው ወሎና ጐንደር የዘረፋ ጦርነት ከፈቱ ። በሮባሌ ሉባ (1570—1578) ዘመን በሰሜናዊ ሸዋና በምስራቃዊ ጐጃም ዘረፋ አካሄዱ ። በዚህ በሮባሌ ሉባ ዘመን በምስራቅ የኦሮሞ ሰፋሪዎች በሐረር አካባቢ በመቶ የሚቆጠሩ የአዳል ማለትም የሀርላ መንደሮችን አጠፉ ።[31] በሐረር ከተማም ላይ ከበባ አካሄዱ። የአዳልን መንግሥት በሐረርና በአውሳ ከፍለው መሀሉን ያዙ።በቢርመጂ ሉባ (1578—1586) አመራር በሰሜናዊ ምዕራብ ወደ ደምብያ በመሀል ምዕራብ ደግሞ ወደ ዳሞትና ጋፋት አገሮች ደረሱ።

በዚህ በሮባሌ ሉባ ዘመን ኦሮሞዎች በጦር ድርጅትና ስልት ጋሻ መጠቀም ጀመሩ ።[32] ከዚህ አዲስ የጦር መሣሪያ የማያን የመርዛማ ቀስት ጦርነት ጨምሮ የብዙ ነባር ሕዝቦችን የቀስት ጦርነት ከአገልግሎት ውጭ አደረጉ ። ባጭሩ በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት አዲሱ የነፍጥ መሣሪያ በአገሪቱ በጦር ድርጅትና ስልት መሠረታዊ ለውጥ እስካስከተለው ድረስ ፣ የፈረስና የጋሻ መሣሪያዎች አገልግሎት በአገሪቱ ማዕከላዊ መንግሥት ላይ ለኦሮሞ ማህበረሰብ ለረጅም ጊዜ የኃይል ሚዛን እንደ ሰጠው የዘመኑ ታሪክ ያስተምረናል ።

በመጨረሻም በሙለታ ሉባ ዘመን (1586—1594) ኦሮሞዎች በታላቅ ዝግጅትና ግፊት በሸዋና በጐጃም ላይ ዘመቱ ። ይሁን እንጂ ከሙለታ ሉባ ዘመን በኋላ በኦሮሞ የገዳ ሥርዓትና አመራር ላይ መሠረታዊ የለውጥ ሁኔታና ሂደት መከሰት ጀመረ ። በዚህ አኳያ ፣ ጦረኛው አፄ ሠርፀ ድንግል (1563—1597) በሙለታ ሉባ ዘመን ማህበረሰቡን የፍለሳ ስምሪት ለተወሰነ ጊዜ ከትግራይ ፣ ከበጌምድርና ከጐጃም ወደ ኋላ ስለመለሰው የማህበረሰቡ የተለያዩ ጐሳዎች በደረሱበት አካባቢ ሁሉ በነዋሪነት የሰፈራ ሂደትና ልምድ ጀመሩ ። በሰፈራ ኑሮና በአዲስ የእርሻ ሥራ ምክንያት በራሱ በኦሮሞ ሕብረተሰብ ዘንድ ውስጣዊ የገዳ ሥርዓት ለውጥና የገባር ሥርዓት ጥንስስ ቀስ በቀስ መታየት ጀመረ ።

ከዚህ ከኦሮሞ የሥርዓት ለውጥ ሂደት ጋር የአፄ ሱስንዮስ ታሪክና በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የጐንደር አካባቢ መንግሥት (1605—1855) ምስረታና ዕድገት በቅርብ የተያያዙ ነገሮች ናቸው ።

የጐንደር ዘመነ መንግሥት መሥራቹ አጼ ሱስንዮስ (1605—1632) የኦሮሞ ገዳ ሥርዓት ወደ ባላባታዊ ሥርዓት የመለወጥ ሂደትን የጀመረ ሰው ነው ። የአጼ ልብነ ድንግል የልጅ ልጅ የነበረው ልዑል ሱስንዮስ በ1565 ገደማ ተወለደ ። በ1580 በምርኮ ተወስዶ የአንድ ቡኮ የተባለ የቦረና ኦሮሞ የጉዲፈቻ ልጁ ተደረገ ። በዚህ በምርኮው ዘመኑ ሱስንዮስ የኦሮሞን ቋንቋ

[31] *Trimingham, Islam in Ethiopia*, p. 96.
[32] Bahrey, *History of the Galla*, p. 120.

የገዳ ሥርዓትና የሉባ የጦር ድርጅትና ስልት አጠናቅቆ አወቀ ። በ1586 ገዳማ በአርነት ወደ ሠርፀድንግል ቤተ መንግሥት ከተመለሰ በኋላ የመንግሥቱን ወግና ሥርዓት ጨምሮ ተማረ ።

በ1597 አፄ ሠርፀ ድንግል ሲሞት በወራሾችና ቁርባን ፣ አቴትዝር ፣ ጨረታ ፣ ጊዮርጊስ ኃይሌ ፣ አፍር አይገባ ፣ ኮከብ . . . ወዘተ በተባሉ ታላላቅ የጦር ድርጅቶች መካከል የሥልጣንና የእርስ በርስ ጦርነት ተቀሰቀሰ። ራስ ዘሥላሴ ፣ ራስ አትናቴዎስ ፣ ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ፣ የልዮስ ፣ ክፍሎም ፣ ዩናኤል ፣ ጌዴአን ፣ ተክለ ጊዮርጊስ ፣ ሠርፀ ክርስቶስ . . . ወዘተ የተባሉ የዘመኑ ታላላቅ የጦር አበጋዞችና አገረ ገዥዎች የተጠቀሱትን የጦር ድርጅቶች ይዘው ከ1597 ጀምሮ በአንድ አሥርት ውስጥ በዙፋን ላይ ሦስቱን የጐንደር መጀመሪያ አፄዎችን ማለትም የአፃ ያዕቆብን ፣ የአፄ ዘድንግልንና የአፄ ሱስንዮስን ሹም ሽር አደረጉ ።[33]

በዚህ የሽግግር ወቅትና ሁኔታ መጀመሪያ ሱስንዮስ ወደኦሮሞ ጉዲፈቻ ዘመዶቹ በሽሽት አምልጦ ለአንድ አሥርት የሥልጣን ሽፍታ ሆነ። የገዳ ሥርዓታቸውን ከሉባ ጦርነት ጋር ስለሚያውቅ ኦሮሞዎች ሽፍታውን እንደየሉባ መሪያቸው ተከተሉት።በመጨረሻም በ400 የኦሮሞ ወታደሮች ወሳኝ ርዳታ [34] የሥልጣን ጠላቶቹን ደምስሶ በአፄው ዙፋን ላይ ወጣ ። ከ1605 እስከ 1632 ድል አድራጊው ሱስንዮስ ፣ አንደኛ በሰሜን ምዕራብ ከ1535 እስከ 1543 ድረስ ኢማም አህመድ ግራኝ ማዕከሉ አድርጐ በቆረቆረው በደምቢያ አገር የጐንደር ዘመነ መንግሥቱን (1605—1855) መሠረተ ። ሁለተኛ ፤ ከሠርፀድንግል በኋላ የኦሮሞዎችን የፍልሳና የሰፈራ ስምሪት ከሰሜኑ የትግራይ ፣ የበጌምድር፣የላስታ ፣ የደምብያና የጐጃም አካባቢዎች በረጅምና ብርቱ ጦርነት ወደ ምስራቅ፣ ወደ ደቡብና ወደ መሀል ምዕራብ መለሰ ። ሦስተኛ ፣ ኢየሱሳውያን በተባሉ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ጅምር እርዳታ ከዘመነ ዘአገው መንግሥት በኋላ የአገሪቱን የመጀመሪያውን ቋሚ መዲና ከከተማ ባህል ጋር በደንቀዝ ደምብያ ላይ መሠረተ ።


ከ1605 እስከ 1855 በሰሜን ምዕራብ በአፄ ሱስንዮስ የተቆረቆረው የጐንደር መንግሥትና የከተማ ሥርዓት ለአገሪቱ አካባቢያዊ የኦሮሞ ፣ የአማራ ፣ የአገው ፣ የፈላሻ ፣ የጉሙዝ ፣ የኩናማ ፣ የናራ ፣ የቤጃ ፣ የትግሬ ፣ የትግረ ፣ የሳሆ ፣ የቢለን በሀወርታዊ ሕብረተሰብና ሥርዓት መሠረትና ማዕከል ሆነ ። በዚህ ሁኔታና ሂደት በኢትዮጵያ ረጅምና ውስብስብ ታሪክ የሕዝቦች ፍለሳና ሰፈራ ለዛሬው በሀውርታዊ መንግሥትና ሕብረተሰብ ዕድገት አንድ ታሪካዊ መሠረት ፣ መንገድና መግሪያ እንደሚሆን በዚህ ጥናት ከዚህ በታች አገባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ይታያል ።

---

[33] ተክለሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ምዕራፍ1-21 ።

[34] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ምዕራፍ. 22 ።





## 5. የአጼው መንግሥት የምክልና ትግልና የውጭ ኃይሎች ግፊት

## 1540—1597

በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት በመጨረሻዎቹ ስድስት አሥርታት ፣ ሦስቱ የኢትዮጵያ አጼ ነገሥታት ገላውዴዎስ (1540—1559) ፣ ሚናስ (1559—1563) እና ሠርጸ ድንግል (1563—1597) ከውስጥ በኢማም አህመድ ግራኝ አመጽና በታላቁ የሕዝቦች ፍለሳ ከውጭ ደግሞ በቱርኮችና በፖርቱጋሎች ግፊት በከፋኛ የተናጋውን ማዕከላዊ የአጼ መንግሥትን ፣ ሥልጣን መልሰው ለመገንባት ከአዳሎች ፣ ከሀዲያዎች ፣ ከጉራጌዎች ፣ ከዳሞቶች ፣ ከእናሪያዎች ፣ ከፈላሻዎች ፣ ከአገዎች ፣ ከጉሙዞች ፣ ከቱርኮች ፣ ከፖርቱጋሎች ጋር በትጥቅና በፖለቲካ ረጅም ወታደራዊ ትግል እንዳካሄዱ ይታወሳል ።[1]

ከ1540 እስከ 1559 ድረስ ፣ አጼ ገላውዴዎስ በፖርቱጋል ወታደሮች ድጋፍ በአዳል አመጸኞችና በኦሮሞ ሰፋሪዎች ላይ የአጼ መንግሥትን የበላይ ኃይልና ሥልጣን መልሶ ለማረጋገጥ እንዲሁም በሰሜን ኢትዮጵያ የተካሄደውን የቱርኮችን ወረራ ለመመከት ብርቱ የመጀመሪያ እርምጃዎችን ወሰደ ። የአዳሎች አመጽና የኦሮሞዎች የፍለሳ ስምሪት ግምባር በነበረው በመሀል ደቡብ ማለትም በዋጅ የመንግሥቱን የሥልጣን ማዕከል አቋቋመ ።

በ1540 አጼ ገላውዴዎስ የአባቱን ዙፋን በያዘ ጊዜ ፣ ኢማም አህመድ ግራኝ ከደምብያ ማዕከሉ የኢትዮጵያ ገዥ እንደነበር ይታወሳል ። በ1541 ወጣቱ አጼ በደቡብ ምስራቅ ትግራይ በሰሐርት ቀበሌ ከአዳሎች ጋር ባደረገው የመጀመሪያው ግጥሚያ ከተሸነፈ በኋላ የፈላሻን ተራራማ አገር ሰሜንን አቋርጦና በዋድላ—በጌምድር መንገድ የአባይን ወንዝ ከሰሜን ምስራቅ በኩል ተሻግሮ ወደ ጉጃም ከጉጃም አባይን ከደቡብ ምዕራብ ማለትም በግንደበረት በኩል እንደገና በመሻገር በደቡብ ወደ ይፋት፣ ሸዋ ፣ ፈጠጋርና ደዋሮ ሸሸ ።

400 የፖርቱጋል ነፍጠኞች በቤርሙዲዝና በክርስቶፍዳጋማ ጥምር መሪነት በጦርነቱ ጉዳይ የአጼውን ማዕከላዊ መንግሥት በኢማሙ ላይ ለመርዳት በሐምሌ 1541 ወደ ምጽዋ በደረሱ ጊዜ አጼ ገላውዲዎስ በሸዋ፣ በይፋት ፣ በፈጠጋርና በደዋሮ ከቦታ ወደ ቦታ እየተንቀሳቀሰ በአዳሎች

[1] Conzelman, *Chronique de Galawdeos*; *Bahrey*, *History of the Gallac*; *Basset*, *Etudes sur L Histoire*; *Castannhoso*, *The Portuguese Expedition*; Conti; *Rossini*, *Sarsa Dengel*; C.F. Beckingham," A Note on the Topography of Ahmed Gran's Campaign in 1542," *Journal of Semitic Studies*, vol. 4(1955), pp. 362-373.



ላይ የደፈጣ ውጊያ በመካሄድ ላይ ነበር ። ፖርቱጋሎች ከምጽዋ—አርኪኮ ተነስተው በባህረነጋሽ ይስሐቅና በእቴጌ ሰብለ ወንጌል አስተናጋጅነት በሰራየ አውራጃ በደባርዋ ከተማ እስከ ታህሣስ 1541 ድረስ ከቆዩ በኋላ በደቡብ ከአጼ ገላውዴዎስ ጋር ግምባር ለመፍጠር በአጋሜ መንገድ ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። በጉዞአቸውም በየካቲት 1542 በአጋሜ የአምባ ሰነይትን ምሽግ ከአዳሎች አስለቀቁ ። በተጨማሪም አሁንም በአጋሜ በሁለት ተከታታይ ግጥሚያዎቹ ራሱን ኢማም አህመድ ግራኝን አቁስለው በሽንፈት መለሱት ።

ነገር ግን በነሐሴ 1542 በአሸንጌ ሐይቅ አጠገብ በተካሄደው በወፍላ ጦርነት በቱርክ ነፍጠኞች እርዳታ ኢማም አህመድ ግራኝ ፖርቱጋሎችን አሸነፈ ። አዝማች መሪያዎችውን ክርስቶፍዳጋማን ገደለ ። ከወፍላ ጦርነት ከተረፉ ፖርቱጋሎች ውስጥ አምሳ ነፍጠኞች በሽሽት ወደ ምጽዋ ሲገቡ ፣ አንድ መቶ ሃያ ነፍጠኞች ከቤርሙዴዝና ከእቴጌ ሰብለ ወንጌል ጋር ወደ ሰሜን ምዕራብ በመሸሽ በሰሜን አምባ ከአጼ ገላውዴዎስ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ተገናኙ ።

በሰሜን አጼ ገላውዴዎስና ፖርቱጋሎች እንደተገናኙ ራሱን የኢትዮጵያ " ፓትርያርክ " ብሎ የሰየመው ቤርሙዲዝ ለአጼ ገላውዴዎስ በ1535 ለወታደራዊ እርዳታ ወደ ሮማ ፓፓና ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ በአባትህ ንጉሥ ልብነ ድንግል በተላኩ ጊዜ ንጉሡና በወቅቱ የአገሪቱ የቤተ ክርስቲያን መሪ የነበረው ግብጻዊው አቡነ ማርቆስ ከእሱ በኋላ የኢትዮጵያ የሚቀጥለው ፓትርያሪክ እንድሆን እኔን መርጠውኛል ፣ መመረጤም በሮማ ፓፓና በፖርቱጋሉ ንጉሥ ዘንድም የጸደቀልኝ ስለሆነ በዚሁ መሠረት በኢትዮጵያ የሮማ ፓፓ እንደራሴ መሆኔን በመቀበል አገርህንና መንግሥትህን በመንፈሳዊ አመራሬ ሥር አውለህ ሥልጣኔን ተቀበል በማለት አጥብቆ ጠየቀው ።[2] ይህንን ባታደርግ ግን በእኔ መሪነት የመጡ የፖርቱጋል ነፍጠኞች በኢማም አህመድ ግራኝ ላይ አይረዱህም በማለት አስፈራራው ። አጼ ገላውዴዎስ ግን ጥያቄውን ውድቅ አደረገ ። በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያ እስከ 1632 የሚቆየው የፖርቱጋል የቅኝ ግዛት ግፊትና የፖለቲካ ሴራ ተጀመረ ።

በአጼ ገላውዴዎስና " በፓትሪያርክ " ቤርሙዴዝ መካከል የከረረ የሥልጣን ትግል ቢፈጠርም ፣ በእቴጌ ሰብለወንጌል ብልህ አስተባባሪነት ፣ የፖርቱጋል ነፍጠኞች ከመሪያቸው ከቤርሙዴዝ ጋር ከሰሜንአምባ ከአጼው ጉን ተሰልፈው ወደ ደምብያ በመሄድ በየካቲት 22 ቀን1543 በጣና

[2] ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ ፤ የግራኝ ወረራ ገጽ 521-22።

ሐይቅ አጠገብ በወይናደጋ ጦር ሜዳ በአጼውና በኢማሙ ወታደሮች መካከል በተካሄደው ጦርነት ከአንድ የፖርቱጋል ነፍጠኛ በተተኮሰው ጥይት ተመቶ ኢማሙ ሞተ ። ከሞት የተረፉ የአዳል ወታደሮችና የጦር አለቆች ከሰሜኑ ደጋ በሽሽት ወደ አገራቸው ወደ አዳል ገቡ ።

ከኢማም አህሙድ ግራኝ ሞት በኋላ ፣ ከየካቲት እስከ መስከረም 1543 ፣ አጼ ገላውዴዎስ ከደምብያ ጊዜያዊ ማዕከል ሆኖ ፣ በሰሜንና ምዕራብ የደምብያ ፣ የጐጃም ፣ የበገምድር ፣ የላስታ ፣ የሰሜንና የትግራይ ክፍለ ሀገራትን በአጼው ማዕከላዊ መንግሥት ሥር መልሶ አደራጃቸው ።[3] በዚሁ ጊዜ የሟቹ ኢማም የወንድም ልጅና ወራሽ ዋዚር አባስ አቡን ከበገምድር የቀደሞ ግዛቱ በሽሽት አምልጦ በደቡብ ምስራቅ ፈጠጋርን ፣ ደዋሮንና ባሌን በአንድነት አጣምሮ ያዘ ። በደቡብ ምስራቅ በዋዚር አባስ አቡን ወደሚመራው ወደ አዲሱ የአዳል ኃይል ከመመለሱ በፊት ፣ አጼ ገላውዴዎስ በፖርቱጋል ነፍጠኞች እርዳታ በደቡብ ፣ በደቡብ ምስራቅና በመሀል ምዕራብ የሸዋ ፣ የፈጠጋር ፣ የዳሞት ፣ የጋፋት ፣ የእናርያ ፣ የጉራጌ ፣ የዋጅና የሀዲያ አገሮችን እንደ ገና መልሶ በአጼው ማዕከላዊ መንግሥት ሥልጣን ሥር ለማምጣት ብርቱ ጥረት አደረገ ። በተጨማሪም በ1543 መጨረሻ በዝዋይ — አዋሽ ክልል ዋጅን የመንግሥቱ አዲስ ማዕከል አድርጎ ቆረቆረ ። ከ1543 እስከ 1559 ድረስ በአዳልና በኦሮሞ እንቅስቃሴዎች ግምባር ዋጅ የኢትዮጵያ ዋናው የፖለቲካና የአመራር ማዕከል ሆነ ።

በጥቅምት 1544 አጼ ገላውዴዎስ ዋዚር አባስ አቡንን በዋጅ ጦርነት ገደለው ።[4] ከዋዚር አባስ አቡን ሞት በኋላ ከዋጅ ማዕከሉ አጼ ገላውዴዎስ በተከታታይ በሀዲያ ፣ በጉራጌ ፣ በዳሞት ፣ በጋፋትና በእናርያ ብዙ የቅጣት ፣ የጸጥታና የግብር ዘመቻዎችን አካሄደ ። በተጨማሪም ፣ በቤፎሌ ሉባ ዘመን (1546—1554) ከዋጅ ተነስቶ ከኦሮሞዎች ጋር በደዋሮ የመጀመሪያውን ጦርነት አካሄደ ።[5]

ከ1540ዎቹ ሁለተኛው አጋማሽ እስከ 1550ዎቹ ፍጻሜ ድረስ አጼ ገላ ውዴዎስ ከዋጅ ማዕከሉ ከአዳሎች ፣ ከኦሮሞዎች ፣ ከሀዲያዎች ፣ ከፖርቱጋሎችና ከቱርኮች ጋር በትጥቅ ፣ በፖለቲካና በሃይማኖት የመከላከል ጦርነት ሲያካሂድ ዘመኑን በትግል ፈጸመ።በዚህ አኳያ፣ ከ1547 እስከ1550 ድረስ አጼ ገላውዴዎስና ሁለቱ ታላላቅ የጦር መሪዎች ራስ ፋኑኤልና

[3] Conzelman, *Chronique de Galawdewos*, chap. 23.

[4] *Ibid.*, chap. 25

[5] *Ibid.*, chap. chap. 27; Castanhoso, ***Portuguese Expedition***, pp. 2, 29-30.



ራስ ሐመልማል ከሐረር እስከ ዜላ " ከባር ሰዓዳዲን እስከ ባር አጀም ድረስ" ማለትም ከአዋሽ እስከ ኤደን ባህረሰላጤና እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ጠረፍ ድረስ በመላው የአዳል አገር ብዙ ተከታታይ የቅጣት ዘመቻዎችን በማካሄድ በሕይወትና በንብረት ታላቅ ጥፋት እንዳደረሱ መንደሮችን ከተሞችንና መስጊዶችን እንዳፈራረሱ አይዘነጋም ።[6]

ኢማም አህመድ ግራኝ ገና በሕይወቱ ሳለ በ1542 አገሪቱን በፖርቱጋል ዘውድና በሮማ ፓፓ ሥልጣን ሥር ለማምጣት በነበራቸው ዓላማ የፖርቱጋል ነፍጠኞች " በፓትሪያርክ " ቤርሙዴዝ መሪነት በአጼ ገላውዴዎስ ላይ ያልተሳካ ጥረት ማድረጋቸው ይታወሳል ። ከኢማሙም ሞት በኋላ የፖርቱጋል ነፍጠኞች ለአመጽ የማነሳሳት ሴራቸውን ስለቀጠሉ " ፓትሪያርኩ " ቤርሙዴዝ በአጼ ገላውዴዎስ ትእዛዝ ከነፍጠኞቹ ተለይቶ ወደ ግዞት ተላከ ።[7]

በሌላ በኩል ደግሞ በ1554 በፖርቱጋሉ ንጉሥ ጆን ጥያቄ ፣ በፖርቱጋል የካቶሊክ ኢየሱሳውያን አንጃ መሥራች ኢግናቲዮስ ሎዮላ ከአንጃው ተከታዮች በኢትዮጵያ ላይ የሚሾሙትን አንድ ፓትሪያርክና ሁለት አቡኖች ከአሥር ቄሶች ጋር መርጦ ለሹመት ለሮማው ፓፓ አቀረባቸው ።[8] ምርጫቸውም በየካቲት 1554 በሮም ከተማ በቅዱስ ጴጥሮስ ካቴድራል በሮማ ፓፓ ጁሊየስ ሳልሳዊው ከጸደቀ በኋላ ኢየሱሳውያን የተባሉ የፖርቱጋል ሚሲዮናውያን ወደ ሕንድ ደርሰው ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ ከሊዝቦን ከተማ ተነሱ ። ፓትሪያርኩና ረዳቶቹ ወደ ሕንድ ከመድረሳቸው በፊት ፣ በንጉሥ ጆን ትእዛዝ በሕንድ የፖርቱጋል አገረ ገዥ የነበረው ፒድሮ የሚሲዮናውያኑን መምጣትና ተግባር በቅድሚያ ለአጼ ገላውዲዴዎስ የሚያሳውቅ አንድ የልዑካን ቡድን በመጋቢት 1555 ወደ ኢትዮጵያ ላከ ።

የልዑካኑ ቡድን " ከፓትሪያርኩ " ቤርሙዴዝ ጋር ከኢትዮጵያ በመጋቢት 1556 ወደ ሕንድ ከተመለሰ በኋላ በመስከረም በዚሁ ዓመት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ኢየሱሳውያን ከፖርቱጋል ወደ ሕንድ ደረሱ ። በኢትዮጵያ ጉዳይ በሕንድ አገር በተካሄደው የፖሊሲ ጉባኤ ፣ " ከፓትሪያርኩ " ቤርሙዴዝ ጋር ከኢትዮጵያ የተመለሰው ቡድን ቢያንስ በ600 በሚቆጠሩ ነፍጠኞች ካልታጀቡ በስተቀር የኢትዮጵያ አጼ የሚሲዮና

[6] *Ibid.*, *Chronoque de Galawdewos*, chap. 2, 28-38.

[7] Getahun Dilebo, " Early Portuguese Imperialism in Ethiopia 1490-1632: Origins Responses, Consequences" Unpublished MA Thesis( Howard University, Wash. D.C., 1971), pp. 96-99.

[8] Ibid. p. 111

ውያንን ትምህርትና ሥልጣን በመቀበል አገሩን ሕዝቡንና መንግሥቱን በፈቃዱ በፖርቱጋል ዘውድና በሮማ ፓፓ ስር ፈጽሞ እያደርግም የሚል አስተያየቱን አቀረበ ። [9]

ነገር ግን በሕንድ የፖርቱጋል ንጉሥ እንደራሴ ፔድሮ ሚሲዮናውያኑን አጅቦ ወደ ኢትዮጵያ የሚሄድ የጦር ኃይል አልነበረውም ። በመሆኑም ነገሩን በሊዝቦን ለፖርቱጋል መሪዎች በደብዳቤ አሳውቆ መልሱን ከፓትሪያርኩ ጋር በሕንድ ሲጠባበቅ ፣ ከአቡኑ ጋር ስድስት ኢየሱሳውያን ከሕንድ በሰኔ 1557 [10] በምጽዋ በር ወደ ኢትዮጵያ መግባት በዋጅ ወደ አጼ ገላውዴዎስ ቤተ መንግሥት ደረሱ ።

በሚሲዮናውያኑ አማካይነት የአገሩን ሕዝብና መንግሥት ይዞ የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ እንዲሆን ከኢየሱሳውያን አንጃ መሥራች ሎዮላ ፣ ከሮማ ፓፓ ጁሊየስ ሳልሳዊና ከፖርቱጋል ንጉሥ ጆን ሳልሳዊ በሕብረት የቀረበውን ጥያቄ አጼ ገላውዴዎስ ውድቅ በማድረግ [11] የአገሩ ጥንታዊ የኦርቶዶክስ ክርስትና የሚገልጸውን የራሱን ታሪካዊ ማኒፌስቶ ጻፈ ። [12]

በአጸፋ እርምጃቸው የፖርቱጋል ኢየሱሳውያን በኢትዮጵያ በአንድ በኩል የእርስ በርስ ጦርነት ደገፉ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአገሪቱ መንግሥት ላይ በሰሜኑ የባህረነጋሽ ግዛት ማለትም በዛሬው ኤርትራ ከቱርክ ወራሪዎች ጋር ጊዜያዊ ስምምነት ፈጠሩ ። በዚህ አኳያ ፣ በ1557 መጀመሪያ ለፖርቱጋል ኢየሱሳውያን በምጽዋ በር ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ በዚሁ ዓመት ቱርኮች የምጽዋን ደሴት በጦር ኃይል ያዙ ። ቀጥሎም ከ1557 እስከ 1589 ለሦስት አሥርታቱ ከምጽዋና ከሱዊኪን ተነስተው በአርኪኮ ፣ በሐማሴን ፣ በሰራየ ፣ በደባርዋ ፣ በአካለጉዛይ ፣ በቡር ፣ በትግራይና በመዘጋ ከተሞች ፣ ቀበሌዎችና አውራጃዎች ረጅም የወረራ ጦርነት ከፈቱ ። [13]

ቱርኮች በሰሜኑ ክፍለ ሀገር የወረራ ጦርነት በከፈቱበት ወቅት አጼ ገላውዴዎስ በደቡብ ማለትም በአዋሽ—ዝዋይ አካባቢ ከኦሮሞ የምችሉ ሉባ ጋር (1554—1562) በጦርነት ላይ ነበር ። በመሆኑም በ1558 የባህረ ነጋሽ ይስሐቅን ጦር በቱርኮች ላይ አስዘመተ ። [14] በ1558 አጼውና ባህረነጋሹ በየግምባራቸው በጠላቶቻቸው ላይ ድል ከተቀዳጁ በኋላ ፣ በመጋቢት 1559 በዋጅ ከአዳሉ ኤሚር ኑር ጋር ሲዋጋ ገላውዴዎስ ራሱ ሞተ።

በአጼ ገላውዴዎስ ድንገተኛ ሞት የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት በሥልጣን ትግል በሁለት አንጃዎች ተከፈለ ። በሥልጣን አንጃ ቀዳድ ደግሞ ፖርቱጋሎችና ቱርኮች በአገሪቱ ጉዳይ ጣልቃ መግባት ጀመሩ ። በዚህ ነገር ፣ በአጼ ገላውዴዎስ ሞት ወንድሙ ሚናስ (1559—1563) የሟቹን ዙፋን ያዘ ። ነገር ግን ከ1541 ጀምሮ ከፖርቱጋል ነፍጠኞችና ሚሲዮናውያን ጋር የቀረበ ግንኙነትና ወዳጅነት የነበረው ባህረነጋሽ ይስሐቅ ሚናስን በመቃወም የአጼ ልብነ ድንግልን የልጅ ልጅ ልዑል ታዝካሮን ለማንገስ በ1561 ያልተሳካ ሙከራ አደረገ ።

የአመጽ ሙከራው ከከሸፈበት በኋላ ፣ ባህረነጋሽ ይስሐቅ በአጼ ሚናስ ላይ በሰሜኑ ክፍለ ሀገር ከቱርኮችና ከፖርቱጋሎች ጋር ተባበረ ። በዚህ ሁኔታ የመሣሪያና የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኘት ለቱርኩ ፓሻ የክፍለ ሀገሩን ከምጽዋ እስከ ደባርዋ ድረስ የሚገኘውን ቀበሌ ሰጠ ። [15] በተጨማሪም ፣ ከሕንድ የፖርቱጋል ወታደራዊ እርዳታ እናስመጣልሃለን የሚል ተስፋ ስለሰጡት ከአጼ ገላውዴዎስና ከአጼ ሚናስ ጋር በሃይማኖት ጉዳይ ከተጋጩ ከፖርቱጋል ኢየሱሳውያንና ነፍጠኞች ጋር አሴረ ። [16] በመሆኑም አጼ ሚናስ ለኢየሱሳውያን በአገሪቱ ሃይማኖታቸውን እንዳያስተምሩ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ከሰጣቸው በኋላ በግዞት እነሱንም ወደ አንድ ተራራ ሰደዳቸው ። ነገር ግን ሚሲዮናውያኑ ከተጋዙበት ስፍራ አምልጠው በአጼው ላይ ከቱርኮችና ከአመጸኛው ባህረ ነጋሽ ይስሐቅ ጋር የሴራ ግምባር ፈጠሩ ። በሚያዝያ 1562 አጼ ሚናስ ሴረኞቹን በጦር ሜዳ በማሸነፍ በታተናቸው ። በተጨማሪም በዘመኑ መጀመሪያ ፣ አጼ ሚናስ በሰሜን በፈላሻ አመጸኞች ላይ የቅጣትና የዘረፋ ጦርነት በማካሄድ በሕይወትና ንብረት ታላቅ ጥፋት አደረሰ ። [18]

ባጭሩ የአጼ ሚናስ ዘመነ መንግሥት በጣም የውጥረት ወቅት ነበር። መንግሥቱ በደቡብ በአዳል ፣ በሀዲያና በኦሮሞ እንቅስቃሴዎች በሰሜን ደግሞ በፈላሻና በባህረ ነጋሽ ይስሐቅ አመጽ እንዲሁም በፖርቱጋሎችና በቱርኮች ግፊት እንደተወጠረ አጼው ራሱ በየካቲት 1563 በዋግ የጸጥታ ዘመቻ በማካሄድ ላይ ሳለ በድንገተኛ ሕመም ሞተ ።

---

[9] *Ibid.*, p. 113.

[10] *Ibid.*, p. 114.

[11] M. Geddes, *The Church History of Ethiopia* (London; 1696), p. 196.

[12] E.A.W. Budge, *A History of Ethiopia* (1966), pp. 353-355.

[13] *Ibid.*, pp. 347-49; Conti Rossini, *Sarsa Dengel*, parts 5,6,7.

[14] Budge, *History*, p. 348.



[15] *Ibid.*, p. 357

[16] *Ibid.*, pp. 357,158.

[17] *Ibid.*, p. 359.

[18] *Ibid.*, pp. 356- 57

አጼ ሚናስ በ1563 ከሞተበት እስከ 1568 ድረስ አሁንም በዙፋን ውርስ ጉዳይ በአገሪቱ ታላላቅ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የአካባቢ የጦር አበጋዞች መካከል ረጅም የሥልጣን ጦርነት ተካሄደ ። [19] በዚህ አኳያ የአጼ ሚናስ ሞት እንደ ተሰማ በቤተ መንግሥቱ አንድ ከፍተኛ የባለሥልጣኖች አንጃ የሚቹን የአሥራ ሦስት ዓመት ልጅ ሠርጸ ድንግልን (1563—1597) መለክ ሰገድ በሚል የዙፋን ስም በአክሱም ከተማ አነገሠ ። [20] በ1563—1564 ራስ ሐመልማል [21] ከአጼ ገላውዴዎስ ከፍተኛ የጦር አበጋዞች አንዱ የነበረው በበኩሉ በሸዋ ተክለማርያም የሚባል አንድ ሌላ መስፍን አነገሠ ።

አጼ ሠርጸ ድንግል በአዳሉ የመለሳይ [22] ምንደኞች ኃይል የሐመልማልን የሥልጣን አንጃ ከደመሰሰው በኋላ ደግሞ ፣ በ1565—1566 ፋሲል የሚባል አንድ ሌላ ከፍተኛ የጦር አበጋዝ በመሀል ምዕራብ ማለትም በዳሞት የራሱን የዘውድ አንጃ አደራጀ ። [23] በሰሜን ደግሞ ሌላ የጦር አበጋዝ ማለትም ባህረ ነጋሽ ይስሐቅ በቱርኮችና በፖርቱጋሎች የፖለቲካና የመሣሪያ ድጋፍ በ1562—1563 በአጼ ሚናስ ዘመነ መንግሥት የጀመረውን የሥልጣን አመጽ በ1570ዎቹ በአጼ ሠርጸ ድንግል መንግሥት ላይ የበለጠ አጠናክሮ ቀጠለ ። [24]

በአዳሉ የመለሳይ ምንደኛ ወታደሮች ድጋፍ በሥልጣን ባላንጣዎቹ ላይ የኃይል ሚዛን ካገኘ በኋላ ፣ ጦረኛው አጼ ሠርጸ ድንግል በ1597 እስከ ሞት ድረስ በሦስት አሥርታት ውስጥ በአገር ውስጥና በውጭ ጠላቶቹ ላይ ማለትም በደቡብ በሀዲያዎች ፣ [25] በጉራጌዎች ፣ በኦሮሞዎችና [26] በአዳሎች [27] ላይ ፣ በሰሜን በባህረ ነጋሽ ይስሐቅ፣ በቱርኮችና [28] በፈላሻዎች [29] ላይ ፣ በሰሜን ምዕራብ በአገዎችና በጉሙዞች [30] ላይ ፣ በመሀል ምዕራብ በዳሞቶች ፣ በጋፋቶች ፣ በእናርያ ፣ በቢዛሞ ፣ በጐንጋና [31] በቦሻ ላይ ባካሄዳቸው የቅጣት ፣ የጸጥታ ፣ የግብርና የመከላከል ጦርነቶች ድል

---

[19] *Ibid.*, pp. 360-365.
[20] *Ibid.*, pp. 360
[21] *Ibid.*, pp. 360-361.
[22] *Ibid.*, pp .361
[23] *Ibid.*,
[24] *Ibid.*, pp. 364-365
[25] *Ibid.*, pp. 362-363-370.
[26] *Ibid.*, pp. 366,370.
[27] *Ibid.*, pp. 365.
[28] *Ibid.*, pp. 370-371.
[29] *Ibid.*, 366-367.
[30] *Ibid.*, pp. 368-369.
[31] *Ibid:* pp. 362, 364, 369,370



ያስገኙለት "ቋርባን" ፣ " አቄተዝር" ፣ "ጨረቃ"፣ "ጊዮርጊስ ኃይሌ"፣ " ቱርክ " ፣ "አፍሮ አይገባ " ፣ " ኮከብ " ፣ ወዘተ ተብለው በልዩ ልዩ ጥቅል ስሞች የሚጠሩና በአገሬው በአርሶ አደሩ ሀብትና ጉልበት የሚኖሩ ንጉሣዊ በከፍተኛ የጦር አበጋዞችና አለቆች የሚታዘዙ አያሌ "የጨዋ " ወይም በዛሬው አነጋገር ወታደራዊ ድርጅቶችና ኃይሎች ነበሩ ።

የኢትዮጵያ ንጉሣዊ የጨዋ ወታደሮችና የጦር አበጋዞች ከ1557 እስከ 1589 ድረስ በሦስት አሥርታት ውስጥ በሐማሴን ፣ በሰራዬና በትግራይ ከቱርክ ወራሪዎችና ከአካባቢ ወኪሎች ጋር ከአሥር በሚበልጡ ጦርነቶች ተዋግተው የአገሪቱን ነጻነት ከውጭ አደጋ እንዴት እንደአዳኑ ይታወሳል ። በተጨማሪም ከውስጥ በአካባቢው ኃይሎች ላይ ማዕከላዊ የአጼ መንግሥትን ሥርዓትና ሥልጣን ለማስከበር በ1559 በአጼ ሚናስ መሪነት በፈላሻ አመጸኛው ረዲኤት ላይ ፣ በ1566 በአጼ ሠርጸ ድንግል መሪነት በዘውድ አንጃው መሪ በፋሲል ላይ ፣ በ1569 በሀዲያ የአካባቢ አመጸኞች አዜና ጁሁር ላይ ፣ በ1577 በአዳሉ የአካባቢ ሱልጣን መሐመድ አራተኛ ላይ ፣ እንዲሁም በ1582 እና በ1587 በፈላሻ የአካባቢ አመጸኞች ካሊፍና ጐሸን ላይ የንጉሡ የጨዋ ወታደሮችና የጦር አበጋዞች ያካሄዱት ወሳኝ የቅጣት ፣ የጸጥታና የግብር ጦርነቶች በዘመኑ ዜና መዋዕሎች ሰፍረዋል ።

በዚህ አኳያ በ1578 እና በ1589 የቋንቋ ፣ የጐሳ ፣ የሃይማኖትና የአካባቢ ልዩነት ሳይለያቸው የኢትዮጵያ የተለያዩ የአካባቢና የንጉሡ ወታደሮች ማለትም ማዕከላዊ የአጼው ጨዋዎች ፣ የአዳሉ የመለሳይ ወታደሮችና የኦሮሞ የሉባ ወታደሮች በብሔራዊ አንድነት በአጼ ሠርጸ ድንግል መሪነት በሰሜን ከቱርክ ወራሪዎችና ባህረ ነጋሽ ይስሐቅን በመሰሉ ከአካባቢ ወኪሎች ጋር ያካሄዱትን ረጅም ትግል የዘመኑ የሠርጸ ድንግል ዜና መዋዕል ጸሐፊ ወልደ ሃይማኖት እንደሚከተለው ይተርካል ።

በህዳር—ታህሳስ 1578 ብቻ ቱርኮችና ኢትዮጵያውያን በሰራዬ አምስት ታላላቅ ጦርነቶች ተዋጉ ። በመጀመሪያ በህዳር 15 ቀን በተካሄደው ጦርትነ ጠላት በወገን ላይ ጊዜያዊ ድል አገኘ ። ከሦስት ቀናት በኋላ ቅዳሜ በህዳር 19 ቀን የወገን ጦር በቱርኮችና በይስሐቅ ወታደሮች ላይ ታላቅ ድል ተቀዳጀ ። በዜና መዋዕሉ ቃል ፣ በዚያ ቀን ፣ " ፓሻውና ይስሐቅ በማታ ጨለማ ከሰፈራቸው ተነስተው የምድረ ጨውን የአቀበት መንገድ በመንዝ በተራራው ኬላ ላይ በሰፈሩ ሰዎች ሳይታዩ በድንገት ከንጉሡ ሠፈር ለመድረስ በቁልቁለት መንገድ ሲሄዱ አደሩ ። ነገር ግን በዚች ሌሊት የተንቤን ተወላጅና የትግሬ ገዥ ገብረየሱስ ከወደላይ ኬላውን ጠብቆ ሳለ የይስሐቅ ወታደሮች በድንገት ደረሱበት ። እርሱ ከእነርሱ አምልጦ እነሆ ቱርኮችና ይስሐቅ መጡ ! እርበኞች ለጦርነት ይዘጋጁ እያለ ወደ

ንጉሡ በሩጫ ደረሰ ። ከዚያ በኋላ ንጉሡ ወታደሮቹን አሰልፎ ጠላቶቹን ጠበቀ ። ፓሻው ከላይ አንድ ከፍተኛ ሥፍራ ያዘ ። ንጉሡ ከታች ሆኖ አንድ ሰፊ ቦታ ያዘ ። ከላይ ከቱርኮች የሚተኮሰው የመድፍ ጥይት ማንንም ሰው ሳይመታ ከወታደሮቹ ፊትና ኋላ እየወደቀ ከስምንት መድፎች ለሰባት ሰዓት ጥይት ሳያቋርጥ ሲተኮስ ከብዙ ሺህ ወታደሮች መካከል አንድም አልሞተም ። [32]

በዚህ ታሪካዊ ጦርነት የንጉሡ የቁርባን ፤ የጨዋ ፤ የመለሳይና የሉባ ምርጥ ወታደሮችና የጦር አበጋዞች ቱርኮችንና የይስሐቅን ወታደሮች አሸንፈው መለሱ ። በማግሥቱ በህዳር 20 ቀን ቱርኮችንና ኢትዮጵያውያን በሌላ የጦር ሜዳ እንደገና ተጋጠሙ ። በዜና መዋዕሉ እንደተባለው ፤

" ያን ቀን ንጉሡ ከአጠገቡ የማይለዩትን ቁርባን የተባሉ ምርጥ ወታደሮቹን ወደ ጦርነቱ ቦታ ላካቸው ። እነርሱም ከቱርክ ፈረሰኞች ጋር ጽኑ ውጊያ ገጠሙ ። ከቱርክ አርበኞች ብዙ ሞቱ ። ከቁርባኖች ደግሞ ብዙ ቆሰሉ ። ነገር ግን የሞተ አልነበረም ።

" በዚች ቀን ምንም የእሳት ድንጋይ ከነፍጡ እየወጣ እንደ በረዶ ቢዘንብባቸውም ከእነርሱ ፊቱን ያዞረ አንድም አልነበረም ። እየተዋጋ የሚወድቀውን እያነሱ ይወስዱ ነበር ። የሞቱትንም ሰዎች ሬሳ እየወሰዱ ይቀብሩ ነበር ። ከሞት የተረፉት ደግሞ የሞቱትን የተመረጡ ወንድሞቻችን ናቸው ይሉ ነበር ። እኛም ፈለጋቸውን እንከተላለን ። አገልግሎታቸው ለደጉ አምላክ ነው በማለት ወደፊት እየተሽቀዳደሙ በቱርኮች መካከል ገብተው የሞቱም የገደሉም ነበሩ ። ድል አድራጊው ንጉሥ በጦርነቱ ውስጥ የአርበኞችን ብርታትና ቆራጥነት አይቶ ብዙ ፈረሰኞችንና 150 ነፍጠኞችን ከብዙ የጋላ ወታደሮች ጋር ለእርዳታ ላከላቸው ።

" እነርሱም እኔ ልቅደም እኔ ልቅደም እየተባባሉ ወደ ጦር ሜዳ በሩጫ ገቡ ። በዚያን ጊዜ ቱርኮችና የይስሐቅ ወታደሮች ሰንደቃቸውን ከተከሉበት ነቅለው ሸሹ ። ከዚያ በኋላ የድል አድራጊው ንጉሥ ወታደሮች ሰንደቁ በነበረበት ደርሰው ቆሙ ። [33]

በህዳር 19—20 በተደረጉ ጦርነቶች በኢትዮጵያውያን እጅ ወታደሮቻቸው ከተሸነፉ በኋላ ይስሐቅና የቱርኩ ፓሻው ከጦር ሜዳው ፈርጥጠው ወደ አንድ ተራራ ላይ ወጡ ። ከተራራው ላይ ይስሐቅ ወለቶ በተባለች አገር ወዳድ የፖለቲካ ሴት አማካይነት በመካከላቸው ጦርነቱ ቆሞ የሰላም ድርድር እንዲጀመር ወደ ንጉሡ መልእክት ላከ ። ንጉሡም የሃይማኖታችን ጠላት ከሆነው ከቱርኩ ፓሻ ሠፈር ተመልሰህ ብትመጣ እን

[32] ታሪክ ሠርጸ ድንግል ( ያልታተመ ዜና መዋዕል በአማርኛ ትርጉም) ክፍል 6

[33] ታሪክ ሠርጸ ድንግል ። ክፍል 7 ።



ታረቃለን ። ነገር ግን ከቱርኮች ባትለይ በመካከላችን ጦርነት እንጂ ሰላምና እርቅ አይኖርም የሚል መልስ ሰጠ ። የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ እንደ አገናዘበው የወገን ጦር በጠላቱ ላይ ያለፈውን ድል ፤

" የተቀዳጀበት ቀን ቅዳሚት ሰንበት ናት ። የሰልፉም ቦታ የተመረጠበት ምክንያት በውጊያ ጊዜ ለፈረሰኞች ለእግረኞችም የሚያመች ሰፊ ሜዳ በመሆኑ ነው ። ከጦርነቱ በኋላ ፓሻውና ይስሐቅ ሰኞ ቀን በላይኛው መንገድ ሸሽተው በመሄድ ለመድረስ አስቸጋሪ በሆነው በአንድ ከፍተኛ ሥፍራ ሠፈሩ ። ከዚያ ሥፍራ ሆኖ ይስሐቅ የእርቅ መልእክት ወደ ንጉሡ ላከ ። በመልእክቱም ቃል " የረዥም ዘመን ወዳጄ ስለሆነች የልቤን አሳብ እንድነግራት ወለቶ ወደ እኔ ትምጣ " ብሎ ንጉሡን ጠየቀ ። ሰላም ፈላጊ የሆነው ንጉሥ በጥያቄው መሠረት ወለቶን ወደ ይስሐቅ ሲልካት ፣ ለእርሱም ፤

" እርቅ ከፈለግህ ከቱርክ ከተማ ውጣ ። የሃይማኖታችንን ጠላቶች አብረን እንውጋቸው ። እኔም አንተን ወደ ድሮ ሥፍራህ እመልስሃለሁ ። አንተ ግን ከዚያ ባትወጣ ቆራ እንኳን ነጭ ቢሆን ውሃም አቅጣጫውን ለውጦ ወደላይ ቢፈስ ከአንተ ጋር እርቅ አይኖረኝም ብሏል ብለሽ ንገሪው አላት ። "

ይስሐቅም በወለቶ እጅ ለንጉሡ መልሶ በላከው ቃል ፤

" ቱርኩ እኔን ሊረዳኝ መጥቷል ። ስለዚህ ለምን እወጋዋለሁ ? እንዴትስ የሚወደኝን እጠላዋለሁ ? ስለዚህ ንጉሡ ከእኔ ጋር እርቅ ከፈለገ ለፓሻው ወርቅ ሰጥቶና ጠቡንም ትቶ ወደ ሠፈሩ ይመልሰው ። ከፓሻው ጋር የፈጸምኩትን መሀላ ግን አላፈርስም ። ከእርሱ ጋር የገባሁት ስምምነት አልተወውም አላት ። [34]

ከንጉሡ ለቀረበው የሰላም ጥሪ ከከሀዲው ይስሐቅ የተሰጠው መልስ የኢትዮጵያን ሕዝብ በኃይል አስቆጣ ። ይህን የሕዝብ ቁጣ አስመልክቶ፣ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ እንዳስቀመጠው ፤


አንደኛ ፣ ነፍጥና መድፍ ሳትፈራ ከአርበኞች ጋር በየጦሩ ሜዳ የምትውል ወለቶ ከቱርኮች አልለይም በማለቱ ይስሐቅን በጥብቅ ዘለፈችው።

ሁለተኛ ፣ ንጉሡ በበኩሉ ከእንግዲህ ወዲህ ከይስሐቅ ጋር ስለእርቅ የሚነጋገር ሰው ይገደላል በማለት ማስጠንቀቂያ ሰጠ ።

ሦስተኛ ፣ የሃይማኖት መሪና ምሁር አባ ንዋይ በስብከቱና በግዝቱ ብዙ የይስሐቅን ተከታዮች ወደ ወገኑ ሠፈር እንዲመጡ አደረገ ።

[34] ታሪክ ሠርጸ ድንግል ክፍል 7 ።

አራተኛ ፤ የንጉሡ ወታደሮችና የጦር አለቆች እንደ አንድ ሰው ሆነ ው በቱርኮቹና በውስጥ ወኪሎቻቸው ላይ በሕብረት ተሰለፉ ። በዚህ አኳያ ፤ ከዚህ በታች እንደሚታየው ፤ የመለሳይ ፤ የጨዋ ፤ የቀርባንና የ ሉባ ወታደሮችንና የጦር አበጋዞች በታላቅ ወኔና ቁጣ የጠላትን አንገት በጉራዴ እንደቅጠል ሊቀነጥሱ ፎክረው ተነሱ ።



ጥንታዊው ከብረት የተሠራ ሙሉ የጦር መግሪያ ከነባርኔጣው ፤ ይህ በጉጃም ከመርጡለማርያም የተገኘው ጥሩር የአህመድ ግራኝ እንደሆነ ይነገርለታል ።

አምስተኛ ፤ የአካባቢ ወላጆች ልጆቻቸውን አስከትለው በጦር ሜዳ ተሰለፉ ። ለምሳሌ በታህሳስ 1 ቀን 1578 በወገንና በጠላት መካከል በ ካሄደው የጨበጣ ጦርነት አንድ አባት ልጁን በጉራዴ ጥሩር ለብሶ በፈ ረስ ላይ ተቀምጦ የሚዋጋውን አንድ የቱርክ ወታደር ከወገቡ ላይ በሁ ለት በመሰየፍ ፋንታ ለምን አንገቱን ቆረጥኸው በማለት ሲዘልፈው ሌላ አባት ደግሞ ወጣት ልጁን ፈረሰኛውን ቱርክ እንደ መግደል እግረ ኛውን እንዴት ትገላለህ ብሎ በንጉሡ ውሳኔ እስኪፈታ ድረስ በቅጣት እርምጃ ልጁን ወስዶ አሰረው ። ይህንን አስመልክቶ የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ እንዳለው፤ በታህሳስ 1 ቀን በቱርኮችና በኢትዮጵያውያን መካከል በተካሄደው የጨበጣ ጦርነት ፤

" ከንጉሡ ሠራዊት ብዙ ሰዎች በነፍጥ ቆሰሉ ። ከይስሐቅ ፈረሰ ኞች እንዲሁም በነፍጥ የቆሰሉ በጦርም ተወግተው የሞቱ ብዙ ነበሩ



የዚባራስ ልጅ ከቱርክ ፈረሰኞች የአንዱን አንገት ከቀኝ እጁ ጋር በፈረስ ላይ እንደነበረ በሰይፍ ቆረጠ ። ወታደሩም ጥሩር ለብሶ ነበር ። አካሉ በ ልጁ ጉራዴ ከሁለት ከተቆረጠ በኋላ የወታደሩ ፈረስ ግማሽ አካሉን ተሸ ክሞ በቱርኮች መካከል ገባ ። ዚባራስ ግን ልጁን ጥሩር የለበሰውን የቱ ርክ ወታደር ከወገቡ በመቁረጥ ፈንታ ለምን ከላይ አንገቱን ብቻ ቆረጥ ከው በማለት ተቆጣው ። ከዚባራስ ልጅ በዕድሜ ከሚያንሱ ወጣቶች አንዱ ደግሞ እግራኞቹን ቢገድል አባቱ ልጁን በቁጣ ፈረሰኞችን እንደ መግደል እንዴት እግረኞችን ትገድላለህ አንተ እግረኛ ገዳይ የእኔ ልጅ ትባላለህ ወይ በማለት በሰንሰለት ካሰረበት ንጉሡ እስረኛውን ልጅ አስ ፈታው ። ነገር ግን አባቱ ከዚያ በኋላ በውጊያ ፈረሰኛ ጠላት እንጂ እግረ ኛን እንዳይገድል ለልጁ ገደብ ሰራለት ። ይህ በእውነቱ የሚያስደንቅ ነው ። ይህ ሁሉ በሐሙስ ታህሳስ 1 ቀን ሆነ ። [35]

በተጨማሪም በተጠቀሰው ቀንና የጦር ሜዳ በሃይማኖት እስላሞች የነበሩ የኢትዮጵያ የአዳሉ ዝነኛ የመለሳይ ወታደሮች ከሐረር ጌሎ በተ ባለው አለቃቸው መሪነትና አዝማችነት በሃይማኖት ከእነርሱ ጋር አንድ ወገን ከነበሩ ከቱርክ ወራሪዎች ጋር የጨበጣ ውጊያ በማድረግ የቱ ርኮችን አንገት በታላቅ ወኔና አርበኝነት በጉራዴ ስለት እንደቅጠል እየቀነጠሱ በጦር ሜዳ ለአገሪቱ ብሔራዊ ነጻነትና አንድነት በአጼው መንግሥት ስርና አመራር በክብር የጀግና ሞት ሞቱ ። አሁንም በዜና መዋዕሉ ቃል ፤

" በዚህ ቀን ጌሎ የተባለው የመለሳዮች አለቃ በመካከላቸው ገብቶ ብዙ ቱርኮችን ከበታተናቸው በኋላ ሞተ ። እርሱም በመለሳዮች ዘንድ በኃይሉና በብርታቱ የታወቀ ሰው ነበር ። ይህ ሰውዬ በመጀመሪያ መሐ መድን ከድተው ወደ ንጉሡ የገቡ መለሳዮች አለቃ ነበር ። በኋላ ሌሎ ች የእነርሱን ምሳሌ በመከተል መሐመድ ብቻውን እስኪቀር ትተውት ወደ ንጉሡ መጡ ። [36] ።


ከታህሳስ 1 ቀን 1578 ጦርነት በኋላ አንድ ጁዳር የሚባል ሌላ ከፍ ተኛ ባለሥልጣን ንጉሡን ከድቶ ወደ ፓሻውና ወደ ይስሐቅ በመሄድ ሁለቱም ሸሽተው ከተቀመጡበት ተራራ ወርደው የንጉሡን ሠራዊት እንዲወጉ አነሳሳቸው ። በዚህ በጁዳር ምክርና ትምህርት ቱርኮችና ይስ ሐቅ በታህሳስ 7 ቀን የንጉሡን ሠፈር ለመውጋት ከተራራው ወረዱ ። በዜና መዋዕሉ እንደተመለከተው ፤

" ጁዳር ወደ ፓሻው በደረሰ ጊዜ ለጦርነቱ ከተራራው ይወርድ ዘንድ አነሳሳው ። ስለዚህም ብዙ የቱርክ ፈረሰኞችና ነፍጠኞች ከተራራው

---

35 ታሪክ ሠርጸ ድንግል ፤ ክፍል 7 ።

36 ታሪክ ሠርጸ ድንግል ፤ ክፍል 7 ።



ጥንታዊው ከብረት የተሠራ ሙሉ የጦር መሣሪያ ከነባርኔጣው ፤ ይህ በጉጃም ከመርጡለማርያም የተገኘው ጥሩር የአህመድ ግራኝ እንደሆነ ይነገርለታል ።

ወረዱ ። ንጉሡም አርበኞቹን በፍጥነት አደራጅቶ ወጣ ። ከዚያ በኋላ ጨዋ
ዎችንና ቀርባኖችን በአንድነት እያከታተለ ወደ ውጊያ ሥፍራ ሲልክባ
ቸው ጠላቶች ከፊታቸው ሸሹ ። የንጉሡ ወታደሮች ሰንደቅ ከመድፍ
ጋር ከነበረበት ቦታ ደረሱ ። መድፉን ከተቀመጠበት ቦታ በጣሉት ጊዜ
ባለሰንደቁ እየሸሸ ተመልሶ ወደ ፓሻው ሠፈር ደረሰ ። የንጉሡ ወታደ
ሮች ከመድፉ ቦታ አልፈው ወደ ላይ በመውጣት ወደ ፓሻውና ወደ ይስ
ሐቅ ሠፈር ቀረቡ ። ይህ የረቡዕ ቀን ለንጉሡ የኃይልና የድል ለጋሻውና
ለይስሐቅ ደግሞ እያንዳንዱ ሰዓት እስከ ምሽቱ ድረስ የፍርሃት ቀን ሆነ።"[37]

ከረቡዕ ታህሳስ 7 ቀን ጦርነት በኋላ ከፓሻውና ከይስሐቅ ወደታሮ
ችና የጦር አበጋዞች ብዙ በየቀኑ ወደ ንጉሡ ሠፈር መግባት ጀመሩ ።
በዚህ ሁኔታ የ1578 የቱርክ—ኢትዮጵያ ጦርነት የመጨረሻ ፍልሚያ
በታህሳስ 17 ቀን ተጀመረ ። በዚህ ቀን የንጉሡ ወታደሮች ለምግብ ፍለጋ
በአካባቢው ተበትነዋል በማለት ይስሐቅ በንጉሡ ሠፈር ላይ በድንገት
ጦርነት እንዲከፈት ፓሻውን ቀስቀሰው ። አሁንም በዜና መዋዕሉ ቃል፤

" በታህሳስ 17 ቀን ጥዋት ይስሐቅ የንጉሡ ሰዎች ወደ ዘረፋ ሄደ
ዋል የሚል ወሬ ሰማ ። ከዚያ በኋላ ወደ ፓሻው ሂዶ ሰዎቹ ወደ ዘረፋ ሄደ
ዋልና በንጉሡ ሠፈር ላይ ጦርነት እንክፈትበት አለው ። ምንም እርሱ
ራሱ በዚያን ቀን ጦርነት ባይፈለግ ሁልጊዜም እንደሚያደርገው
የይስሐቅን ምክር ተቀበለ ።

" በዚያን ቀን ሁለት የይስሐቅ ጠንቋዮች አባ እስካልና አባ ሐሊብ
ተጣሉ ። የመጀመሪያው ዛሬ ዘመቻ ብትጀምር ድል ታደርጋለህ ሲል ሁለ
ተኛው ግን ዛሬ ከንጉሡ ከመላክ ሰገድ ጋር ጦርነት ብትገጥም አንተ ት
ሸነፋለህ አለው ። ይስሐቅ ዕለተ ፍጻሜው ደርሶበታልና የእውነተኛውን
ሳይሆን የሐሰተኛውን ጠንቋይ ቃል ሰማ ።

" ከዚያ በኋላ ፓሻውና ይስሐቅ ከመሸጉበት ተራራ መድፎቻቸውን
አሸክመው ወደ ውጊያ ሜዳ ወረዱ ። ፈረሰኞችንና ነፍጠኞችን ደግሞ
በቱርኮች የውጊያ ስልት አሰለፉ ። ንጉሡ ግን ዋጋቸውን ለመስጠት ከሜ
ጉላው እንደሚወጣ ሙሽራ ከሠፈሩ ወጥቶ አርበኞቹን በሦስት ግምባሮች
አሰለፈ ። በቀኝና በግራ ግምባሮች የተሰለፉ ወታደሮችን በተክለ ጊዮር
ጊስና በደህራጎት ሥር አድርጐ እርሱ ራሱ ከመሀል ሆኖ ሁለቱንም ግም
ባሮች በውጊያ ማስተባበርና ማበረታታት ጀመረ ። በዚያን ጊዜ ቱርኮቹ
ድምጹ እንደ መብረቅና ነጐድጓድ እስኪሆን ድረስ ነፍጥና መድፍ ተኮሱ።
ነገር ግን የተክለ ጊዮርጊስ ወታደሮች በድፍረት በቱርኮች መካከል ሰን

---

37 ታሪክ ሠርጸ ድንግል ፤ ክፍል 7 ።



ጥቀው ገቡ ። እነርሱንም በተኑ ። ሁለት ነጋሪቶችንና ይስሐቅ የተቀመ
ጠበትን በቅሎ ማረኩ ። ከዚያ በኋላ ብዙ በበቅሎ ላይ ሆነው የሚዋጉ
ቱርኮች ቆሰሉ ። ብዙዎችም በምርኮ ተወሰዱ ።

" ከዚያ በኋላ ይስሐቅ አርባና ሠላሳ የሚሆኑ የቱርክ ፈረሰኞች አስ
ከትሎ ከመካከላቸው ወጣ ። ነገር ግን ቱርኮች ከእርሱ ተለይተው ወደኋላ
ቀሩ ። እርሱ ብቻውን ሲሄድ ከመዳባይ ሮቤል ልጅ ከተክለ ዮሐንስ ሰዎች
ይስሐቅን በሽመቃ ይጠብቅ የነበረ አንድ እግረኛ ወታደር አግኝቶት ከኋላ
በጦር ወጋው ። በገዳይ ደምብ ፎከረ ። ከዚያ በኋላ ይስሐቅ ደሙ እንደ ውሀ
እየፈሰሰበት ወደ ጦር ሜዳ ተመለሰ ። ልብሱ በሙሉ በደሙ ተነከረ ። ያን
ጊዜ ከፈረሱ አውርደውት በምድር አስተኙት ። የልብስ መጋረጃም
አደረጉለት ።

" ከዚያም በኋላ ዋና አማካሪው የነበረ ገራድ ቀድሞት መሞቱን
ሰምቶ ይስሐቅ በሞት አንድ መሆናችን መልካም ነው ። ነገር ግን ከእር
ኩሶች ጋር ሆነን በመዋጋታችን ከፉ ስም አስቀረን አለ ።" [38]

በታህሳስ 1578 ይስሐቅ ከቱርክ ጌቶቹ ጋር በኢትዮጵያ ጦር ከተደ
መሰሰ በኋላ አሥር ዓመታት ቆይቶ በአካባቢው የእዙም ልጅ የሚባል
አንድ ሌላ ምንደኛ ሰው ተነሳ ። ከእርሱ በፊት ይስሐቅ እንደ አደረገው
ሁሉ የእዙም ልጅም ሂዶ በምጽዋ ከቱርኩ ፓሻ ጋር በአገሪቱ ላይ ተባ
በረ ። ፓሻውም ከህጂውን ግለሰብ በክፍለ ሀገሩ ላይ ባህረ ነጋሽ ብሎ ሾ
መው ። ከዚያ በኋላ በ1588 መጨረሻ በእዙም ልጅ አስተባባሪነት የቱ
ርኩ ፓሻ ከነወታደሮቹ ከደኽና ማለትም ከአርኪኮ ተነስቶ አካባቢውን
በጦር ኃይል ያዘ ። በድንገት ደርሶ የባህረ ነጋሽ ደህራጐትን ወታደሮች
ንና የጦር አለቆች ደመሰሰ ። በተጨማሪም የሐማሴኑን ከንቲባ የሰራዩን
አቀጽ ጭምር የክፍለ ሀገሩን አያሌ ታላላቅ ሰዎችና መኳንንቶች በግፍ
ገደል ። ወራሪው ፓሻው በሰራዮ የክፍለ ሀገሩን ርዕሰ ከተማ የነበረውን
ደባርዋን ይዞ ተቀመጠ ።

የክፍለ ሀገሩ በጠላት የመያዝ ወሬ አጼ ሠርጸ ድንግል በሰሜን ምዕ
ራብ በደምብያ ሳለ በህዳር 1588 መጨረሻ በመልእክት ደረሰው ። ከዚያ
በኋላ በደቡብ ፣ በመሀልና በምዕራብ ከባሌ ፣ ከሻርካ ፣ ከሀዲያ ፣ ከዋጅ ፣
ከሸዋ ፣ ከዳሞት ፣ ከአማራ ፣ ከጐጃም ፣ ከደምብያ ፣ ከሺሬ ከትግራይ ወዘተ
የተውጣጡ ወታደሮችንና የጦር አበጋዞችን አስከትሎ አጼ ሠርጸ ድንልግ

---

38 ታሪክ ሠርጸ ድንግል ፤ ክፍል 7 ።

በምጽዋና በትግራይ መካከል ከታህሳስ እስከ ጥር ብርቱና ፈጣን የመከ ላከልና መልሶ የማጥቃት ዘመቻ በማካሄድ የቱርክ ወራሪዎችን ለአንድና ለመጨረሻ ከአካባቢው አስወጣ ።

በጥር 1589 በዳኽኖ (በአርክኮ) ጦርነት በኢትዮጵያ ጦር ተሸንፎ በጀልባ ወደ ምጽዋ ደሴት ከተመለሰ በኋላ የቱርኩ ፓሻ ለድል አድራጊው አጼ ሠርጸ ድንግል ከደሴቱ በጻፈው ደብዳቤ " ከዚህ በኋላ የአገርህን ምድር ሁለተኛ አልረግጥም ። " በማለት የጠላት ቃል ገባ ። የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ እንደመዘገበው ፣ ከዳኽኖ በተነሳው በአምስተኛው ቀን ንጉሡ ከፓ ሻው ደብዳቤ አገኘ ። ፓሻው ለንጉሡ በጻፈው ደብዳቤ ፤

"ጌታዬ ሆይ ! ከፊትህ ወድቄ ለጌትነትህና ለግርማዊነትህ እንደሚገባ እጅ እነሳለሁ ። ድምጽህን ሰምቼ ፈራሁ ። ሥራህንም አይቼ ደነገጥኩ ። ከዚህ በፊት የአገር ሰዎች አሳስተውኝ እስከ ደባርዋ መጣሁ ። አገርህን ልገዛ ፈለኩ ። ማድረግ የማይገባኝ ነገር ለማድረግ ሞከርኩ ። ጌታዬ ሆይ ለዚች ስህተቴ ይቅርታ አድርግልኝ ። ከዚህ በኋላ ግን የአገርህን ምድር ሁለተኛ አልረግጥም ። የምታዘኝን ሁሉ አደርጋለሁ ። ከሎሌዎችህም እንደ አንዱ እሆናለሁ " አለ ።[39]


ከታሪክ አኳያ ሲገመገም ፣ ከ1540 እስከ 1597 ድረስ የኢትዮጵያ አጼ ነገሥታት ገላውዴዎስ ፣ ሚናስና ሠርጸ ድንግል ከውጭ በፖርቱጋ ልና በቱርክ ግፊት ላይ ፣ ከውስጥ ደግሞ በእርስ በርስ ጦርነትና በሕዝቦች እንቅስቃሴ ላይ የአገሪቱን ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት የበላይ ሥልጣንና ሥርዓት መልሰው ለማቋቋም ባካሄዱት ብርቱ የፖሊሲና የተግባር እርም ጃዎች የውጭ ኃይሎችን ግፊት ለመግታት ቢችሉም በአገር ውስጥ የማ ዕከላዊ መንግሥትን የበላይ ሥልጣንና ሥርዓት ለማጠናከር የወሰዱአ ቸው የፖሊሲና የተግባር እርምጃዎች ግን ከግባቸው አልደረሱም ።




ጥንታዊው የምፅዋ ከተማ በ1904
(Schoenfeld, Erythaa.....)

[39] ታሪክ ሠርጸ ድንግል ክፍል 7።







ጥንታዊው የምፅዋ ከተማ በ1904

# 6. የጎንደር መንግሥት ምስረታና የሃይማኖት ጦርነት

## 1597-1632

በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ሦስቱ ተደራራቢ ክስተቶች ማለትም ከውጭ የፖርቱጋሎችና የቱርኮች ግፊት ከአገር ውስጥ ደግሞ የኢማም አህመድ ግራኝ አመፅና ታላቁ የሕዝቦች እንቅስቃሴ በአንድነት የኢትዮጵያን ማዕከላዊ የአፄ መንግሥት ሥርዓትና ሥልጣን አዳከሙት። እነዚህ ሁኔታዎች በአንድ በኩል ለፊውዳላዊ የአካባቢ ኃይሎች ዕድገት ብሎም ለረጅም የእርስ በርስ ፣ የጎሳ ፣ የአካባቢ ፣ የሥልጣንና የሃይማኖት ጦርነቶች ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በኢኮኖሚ ፣ በባህል ፣ በእርሻ በዕደ ጥበብ ፣ በንግድ ፣ በትምህርት ፣ በመገናኛ ፣ በከተማ ባህል ፣ በቴክኖሎጂና በዓለም አቀፍ ግንኙነት አጠቃላይ ለሆነው ብሔራዊ ኋላ ቀርነት ውስጣዊና ውጫዊ አስተዋጽኦ አደረጉ ።

በተጠቀሱት ምክንያቶችና ሁኔታዎች የኢትዮጵያ ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት ሥልጣን ውድቀትና የአካባቢ ፊውዳላዊ ኃይሎች ዕድገት በተግባር የተከሰተው በአፄ ሠርጸ ድንግል ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ በሰሜኑ ደጋ አካባቢ በከፍተኛ የጦር አበጋዞችና ነገሥታት መካከል ለረጅም ጊዜ በተካሄደው የሥልጣን ጦርነትና በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት በአገሪቱ ውስጥ ኢየሱሳውያን የተባሉ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ባስተማሩት ትምህርት ነው ።

በአፄ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት በተካሄዱ ንጉሣዊ አገር አቀፍ ጦርነቶች በሕብረተሰቡ ላይ የኢኮኖሚና የፖለቲካ መሠረታቸውን የገነቡ የመንግሥቱ ቁርባን ፣ አቄትዝር ፣ ጨረቃ ፣ ጊዮርጊስ ኃይሌ ፣ “ ቱርክ ” ፣ “ ናራ” ፣ አፍሮ አይገባ ፣ ኮከብ የተባሉ የጦር ድርጅቶችና አበጋዞች በ1597 አጼ ሠርፀ ድንግል ከሞተ በኋላ የነገሥታት ሹም ሽር ማድረግ ጀመሩ ። ለምሳሌ ከ1597 እስከ 1604 ድረስ የጦር አበጋዞች የሦስት ነገሥታት ሹም ሽር እንዳደረጉ ታውቋል ። በዚህ ሁኔታና ሂደት በተለይ በሰሜኑ አካባቢ የጐጃም የደምብያ ፣ የበጌምድር ፣ የአማራ የአንጐት ፣ የላስታ የሰሜን የትግራይ የምድረ ባሕሪ ክፍለ ሀገራትን ለብዙ አሥርታት የጦር ሜዳዎች አደረጉ ። በአካባቢው በአማራ ፣ በአገው ፣ በትግሬ ፣ በፈላሻ ፣ በጉሙዝ፣ በቤጃ ፣ በኩናማ ፣ በባርያ በትግረ ሕዝቦችና ማህበረሰቦች ላይ በሕይወትና በንብረት ከፍተኛ ጥፋት አደረሱ ። በተጨማሪም በተጠቀሱ ነገሥታት ፣ የጦር ኃይሎችና በኦሮሞ ሰፋ



ሪዎች መካከል ለረጅም ጊዜ የተካሄደው ጦርነት በአካባቢው ለብዙ ሕይወትና ንብረት መጥፋት አንድ ሌላ ምክንያት ሆነ ።

በሌላ በኩል በአስራ ሰባተኛው ምዕተ ዓመት የመጀመሪያዎቹ ሦስት አሥርታት ውስጥ የእስፔን ኢየሱሳውያንን ( Spanish Jesuits ) ዘመናዊ ትምህርት ፣ የሙያ ጥበብ ፣ አዲስ የቤት ፣ የከተማ ፣ የመንገድ የድልድይ ሥራ በማየት የኢትዮጵያ ነገሥታት በባላንጣዎቻቸው ላይ ሥልጣናቸውን የበለጠ ለማጠናከር ከውጭ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ፣ ትምህርትና የለውጥ ሀሳቦች ሲፈልጉ ፣ በሌላ በኩል ማዕከላዊ ጠንካራ ዘውድ በእነርሱ ላይ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ተጽዕና የሚያስከትል ኃይል ስለሆነ የአካባቢ የጦር አበጋዞችና ጥንታዊ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በግብጻዊ አቡናች መሪነት “ ፀረ- ማርያም ” ነው በሚል ቀስቃሽ የፖለቲካና የሃይማኖት መፈክር ሥር የትግል ግምባር ፈጥረው የአገሪቱን ገበሬ ሕብረተሰብ በነገሥታቱ የትምህርትና የለውጥ ፖሊሲ ላይ በትጥቅ አስነሱ ። በዚህ በኢየሱሳውያን ፣ በነገሥታት ፣ በጦር አበጋዞችና በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ባለሥልጣኖች መካከል በተፈጠረው ግጭት በሁሉም አንጃዎች ዘንድ ሃይማኖት የፖለቲካ ትግል መሣሪያ ሆነ ።

የእስፔን ኢየሱሳውያንን አመጣጥ በሚመለከት ፣ በ1550ዎቹ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የፖርቱጋል ኢየሱሳውያን እስከ 1597 ድረስ ሁሉም በአገሪቱ ውስጥ በሞት አለቁ ።[1] በ1540ዎቹ ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ የፖርቱጋል ነፍጠኞች በአገሪቱ የቀሩት ከኢትዮጵያውያን በጋብቻ ተባዝተው በ1600ዎቹ መጀመሪያ በጦር ሜዳ የሚሰለፉ ወንዶች ብዛት ወደ 1400 ደርሶ ነበር ።[2]

በሌላ በኩል ፣ በውጪ ዓለም ከ1580 እስከ 1640 ድረስ ፖርቱጋል ራሱ በእስፔን ዘውድ ሥር መሆኑ ይታወሳል ።[3] በዚህ ወቅት ከ1603 እስከ 1627 ድረስ በታዋቂው ከአገሪቱና ከአካባቢው ቋንቋዎች አረብኛ፣ ቱርክኛ ፣ አማርኛና ግዕዝኛ የሚናገር በሙያውም አስተማሪ ፣ ሰባኪ ፣ መሐንዲስ ግምበኛና አናጢ በነበረው ፔትሮ ፓየዝ ( 1564-1622)[4] መሪነት ብዙ የእስፔን ኢየሱሳውያን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በዘመናዊ ትምህርትና በሙያ ጥበብ አገልግሎት የአገሪቱን ነገሥታትና ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት እንዴት እንደሚለወጡ ከዚህ በታች ይታያል ።

---

1 Getahun Dllebo, “ Portuguese in Ethiopia, ” p. 120

2 *Ibid.*, p. 129; Job Ludolph, *A New History of Ethiopia* (London: St. paul's 1682), pp. 87-88.

3 *Ibid*; P. 126

4 *Ibid;* pp. 122, 130, 136

የዘመኑ የጦር አበጋዞችን ኃይልና ተግባር በሚመለከት ፤ አፄ ሠርፀ ድንግል ከሕግ ሚስቱ ከእቴጌ ማርያም ሲና አልጋ ወራሽ የሚሆን ወንድ ልጅ አልነበረውም ። በመሆኑም በ1590 አካባቢ ከአንዲት ገረዱ ያዕቆብን ከመውለዱ በፊት የወንድሙን ልጅ ዘድንግል ልሳነ ክርስቶስን የአልጋው ወራሽ እንዲሆን ሰይሞት ነበር ። ነገር ግን በአማካሪዎቹ ተጽዕኖ በ1596 አጼ ሠርፀ ድንግል የራሱን የዙፋን ውርስ ወሳኔ በመሻር በእቴጌ ማርያም ሲና ፤ በራስ አትናቴዎስ የጐጃም ገዥና በደጃዝማች ክፍለዋህድ የትግራይ ገዥ ሞግዚትነት ሥር የሰባት ዓመት ሕጻን ያዕቆብን አልጋ ወራሹ አድርጐ ሰየመው ። ራስ አትናቴዎስና ደጃዝማች ክፍለዋህድ የአጼው ኃይለኛ አማቾች ነበሩ ።

በ1597 አጼ ሠርፀ ድንግል በድንገት ሞተ ። በመሆኑም በ1597 የተጠቀሱ ሞግዚቶችና የጦር አበጋዞች በቁጥጥራቸው ሥር ያዕቆብን (1597-1603) አነገሡት ። የቀድሞ አልጋ ወራሽ ዘድንግልን ደግሞ በሰንሰለት ወደ ግዞት ላኩት ።

ሦስተኛው የዙፋን ተወዳዳሪ ሱስንዮስ ፋሲለደስ የአጼ ልብነ ድንግል የልጅ ልጅ ከተጠቀሱ የአልጋ ወራሹ ሞግዚቶች እጅ አምልጦ በኦሮሞዎች ዘንድ ወደ የቀድሞ የጉዲፈቻ ዘመዶቹ በመሸሽ ከ1597 እስከ 1604 ድረስ ለረጅም ጊዜ በደቡብና በምዕራብ ማለትም በጐጃም ፥ በዳሞት ፤ በጋፋት ፤ በወለቃ ፤ በሸዋ ፤ በዋጅ ፤ በጉራጌ ፤ በሀዲያ ፤ በመንዝ በይፋት ከኦሮሞ ተከታይ ወታደሮቹ ጋር ከቦታ ወደ ቦታ በመንቀሳቀስ አገሬውንና መንገደኛውን እየዘረፈ የሚኖር ሽፍታ ሆነ ።[5]

በሌላ በኩል በ1602 በደምብያ በቆጋ ከተማ በሞግዚቶቹ ቁጥጥር ሥር የነገሠው አጼ ያዕቆብ ራሱን ከሞግዚቶቹ ተጽዕኖ ነፃ በማድረግ የመንግሥትን ሥልጣን በቀጥታ ያዘ ።[6] መንግሥታዊ ሥልጣኑን ስለተቃወመ ወጣቱ አጼ ያዕቆብ ራስ ዘሥላሴ የቁርባን ጦር አበጋዙን በቅጣት እርምጃ ለግዞት ከደምብያ ወደ እናርያ ላከ ። በ1603 ቄስ ፓየዝ ከትግራይ በግዕዝና በአማርኛ ያስተማራቸውን ሁለት ኢትዮጵያዊ ተማሪዎች ይዞ በደምቢያ ክፍለ ሀገር በቆጋ ቤተ መንግሥት ወደ አጼ ያዕቆብ ፊት ቀረበ ።[7] አጼውም በሕዝቡ ቋንቋ ሃይማኖትና ትምህርት የሚያስተምር ፈረንጅ በማየቱ በጣም ተደስቶ ለሥራ ጉዳይ በቅርቡ ተመልሶ እንዲመጣ ነግሮት ቄሱን ከተማሪዎቹ ጋር አሰናበተ ።

---

[5] ተክለ ሥላሴ ፤ የአጼ ሱስንዮስ ታሪክ ምዕራፍ 1-22 ።

[6] Getahun Dilebo, " The portuguese in Ethiopia," p. 124.

[7] Ibid., p. 125



ነገር ግን ከዚያ በኋላ ብዙ ወራት ሳይቆይ በ1603 አፄ ያዕቆብን የቀድሞ ሞግዚቶቹና የጦር አበጋዞቹ በራስ አትናቴዎስ መሪነት ከዙፋኑ አውርደው በሰንሰለት ለግዞት ወደ እናርያ ላኩ ።[8] በምትኩም ደግሞ ዘድንግል ልሳነ ክርስቶስን ከግዞቱ አምጥተው በዙፋን ላይ አስቀመጡት (1603-1604)። ከቅርብ ጊዜ በፊት በአጼ ያዕቆብ ትእዛዝ ለግዞት ወደ እናርያ የተላከውን ራስ ዘሥላሴን የቁርባን ጦር አበጋዝ ደግሞ በነፃ ለቀው ወደ ሥራው መለሱት ።

በሰኔ 17 ቀን 1604 አጼ ዘድንግል ደግሞ ቄስ ፓየዝን በቆጋ ወደ ቤተ መንግሥቱ አስጠራ ። ሰባኪው ፓየዝ ለኢትዮጵያ የመንግሥት መሪዎችና ከፍተኛ ባለሥልጣኖች በግብጻዊው አቡን የሚመራው የአገራቸው ጥንታዊ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በመሠረታዊ የሥላሴ እምነቱ ስህተተኛ በዘመናዊ ትምህርትና ማህበራዊ አገልግሎት ደግሞ ኋላቀር ተቋም ነው በማለት አጼ ዘድንግልን ፤ እቴጌ ማርያም ሲናን ራስ አትናቴዎስን ጨምሮ የመንግሥት አመራር መሪዎችንና አባሎችን ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት በቀላሉ ለወጣቸው ።[9]

በሰኔ 26 ቀን 1604 አጼ ዘድንግል በፓየዝ አማካይነት ለእስፔኑ ንጉሥና ለሮማ ፓፓ በጻፈላቸው የወዳጅነት ደብዳቤዎች የቴክኒክ ሙያተኞችንና ነፍጠኞችን ከሚሲዮናውያን ጋር እንዲላኩለት ጠየቃቸው ።[10] አጼ ዘድንግል የካቶሊክ ሃይማኖቱን በይፋ ከማሳወቁም በላይ በቄስ ፓየዝ ትምህርት መሠረት በአገሪቱ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ እንደ ክርስቲያን በዓል የሚከበረውን የቅዳሚት ሰንበትንም በአዋጅ ሻረ ።

በተጨማሪም አጼ ዘድንግል ለረጅም ዘመን በእርሶ አደሩ ጉልበትና ምርት በድሎት የሚኖሩ የቁርባን ወታደሮችንና የጦር አበጋዞችን የኢኮኖሚ ጥቅም ከፖለቲካ ኃይል ጋር ለመቀነስ በክረምት 1604 በአጠቃላይ የጦር ድርጅቶችና ሹማምንቶች በጐጃም ፤ በደምቢያ ፤ በበጌምድር ፤ በአማራ ፤ በሰሜንና በወገራ በመሬትና በእርሶ አደሩ ላይ የነበራቸውን ጥቅምና ሥልጣን የሚያስቀሩ የፖሊሲ እርምጃዎችን ወሰደ ።[11]

እነዚህንና ሌሎቹንም የአጼ ዘድንግልን በሃይማኖትና በአስተዳደር መስኮች አዲስ የለውጥ እርምጃዎችን በመቃወም የአገሪቱ የጦርና የሃይ

---

[8] Ibid., p. 124,

[9] Ibid., p. 126,
እየለ ተክለ ሃይማኖት ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት (1951) ገጽ116

[10] Ibid., " The Portuguese in Ethiopia," pp. 126-127.

[11] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 21 ቁጥር 102 ።

ማኖት ድርጅቶችና ባለሥልጣኖች በራስ ዘሥላሴ የቁርባን ጦር ዋና አበጋዝ መሪነት በዘድንግልና በመኳንንቶቹ ላይ በትጥቅ አመፅ ተነሱ ።[12] በዚህ ሁኔታ በጥቅምት 13 ቀን 1604 በጐጃም በበርቻ ሜዳ በተካሄደው ጦርነት አጼ ዘድንግል ሲገደል [13] ድሉ የራስ ዘሥላሴ ሆነ ። በጦር ሜዳው ከአጼ ዘድንግል ጐን የተሰለፉ 200 የድሮ የፖርቱጋል ነፍጠኞች በራስ ዘሥላሴ ሠራዊት ላይ የድል ሚዛን አላስገኙበትም ። ቄስ ፓየዝ በግጭቱ ሰዓት ከጦር ሜዳው ተሰወረ ። ራስ አትናቴዎስ ደግሞ የድል ሚዛን አቅጣጫውን አይቶ ከአጼ ዘድንግል ወገን ወጥቶ ወደ ራስ ዘሥላሴ ወገን ተደባለቀ ።

አጼ ዘድንግል ከተገደለ በኋላ ፤ በአገሪቱ የጦር አበጋዞች ዘንድ ሦስት የፖሊሲና የተግባር አማራጮች ቀረቡ ። አንደኛ ፤ የጦር አበጋዞች " ዘድንግልን ከገደሉት በኋላ እንግዲህ ንጉሥ አናነግስም ብለው መከሩ ፤ በየሀገሮቻችንና በየሹመታችን እንቀመጥ ፤ እንኑር አሉ ። ንጉሥ በመሆን ማንም አይግዛን አሉ ። " [14]

ሁለተኛ ፤ ራስ ዘሥላሴ አጼ ዘድንግልን ከገደለው በኋላ ፤ ያዕቆብን እንደገና ሊያነግሰው ከእናርያ ግዞት በአስቸኳይ ወደ ደምቢያ እንዲያመጣለት አንድ የመልእክተኞች ቡድን ላከ ። ነገር ግን ቡድኑ ወደ እናርያ ሲደርስ ግዞተኛው የቀድሞ አጼ ወደ ከምባታ ተወስዶአል ተባለ።[15] በመሆኑም እስከ ሰኔ 1605 ድረስ ያዕቆብ ከከምባታ በደምቢያ ወደ ራስ ዘሥላሴ ሠፈር አልደረሰም ።

ሦስተኛ ፤ ሱስንዮስ በአጼ ያዕቆብ ሽረትና በአጼ ዘድንግል ሞት የአባቶቼ ዙፋን ባዶ ስለሆነ እኔን አንግሡኝ ብሎ በታህሳስ 1604 ወደ ራስ አትናቴዎስና በራስ ዘሥላሴ ወደሚመሩ የቁርባን ጦር መሪዎች መልእክተኞች ላከ ። የጦሩ መሪዎች በሟቹ በአጼ ዘድንግል ሀብትና መሣሪያ ድርሻ ላይ እርስ በርሳቸው ተጣልተው ነበር ። በተጨማሪም ራስ አትናቴዎስና ራስ ዘሥላሴ የቁርባን ሠራዊት አለቆች እርስ በርሳቸው ኃይለኛ የሥልጣን ተወዳዳሪዎችና ባላንጣዎች ነበሩ ።

የቁርባን ጦር አበጋዞች በራስ ዘሥላሴ መሪነት ያዕቆብን ከግዞቱ አስመጥተው እንደገና ለማንገስ በዝግጅት ላይ ስለ ነበሩ መጀመሪያ የሱስንዮስን የዘውድ ጥያቄ አንቀበልም አሉ ። ነገር ግን ራስ አትናቴዎስ

---

[12] Getahun Dilebo, " The Portuguese in Ethiopia," pp. 128-129.

[13] Ibid. p. 128; Budge, *History*, P. 379; ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ምዕራፍ 21 ቁጥር 102 ።

[14] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 21 ቁ. 103 ።

[15] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 21 ቁ. 103 ።



ከኃለይኛይቱ ምሽቱ ከወይዘሮ ወለተጊዮርጊስ የሠርጸ ድንግል ልጅ ጋር ሱስንዮስን ለማንገስ ተስማማ ። በዚሁ መሠረት ሽፍታው ሱስንዮስ 400 [16] የኦሮሞ ወታደሮችን አስከትሎ ከአማራ ክፍለ ሀገር በጐጃም ወደ ራስ አትናቴዎስ ሄደ ። ከዚያ በኋላ በታህሳስ 13 ቀን 1604 በጐጃም ጥቂት ባለሥልጣኖችና የሃይማኖት ምሁራን በተገኙበት ራስ አትናቴዎስ ሱስንዮስን ሥልጣን ሰገድ በሚል የዙፋን ስም አነገሠው ። [17]

ሽፍታው ሱስንዮስ ከራስ አትናቴዎስ እጅ የአጼ ሥልጣን ከተቀበለ በኋላ ፤ በአባቶቼ ዙፋን ላይ ስለ ወጣሁ የአጼ ሥልጣኔን በመቀበል ተከተሉኝ በማለት በራስ ዘሥላሴ ለሚመሩ ለቁርባን ጦር ሹማምንቶችና ጭፍሮች ንጉሣዊ ጥሪ አስተላለፈ ። [18]

በራስ ዘሥላሴ መሪነት የቁርባንና የአቄትዝር የጦር ድርጅቶችና ሹማምንቶች በበጌምድርና በደምቢያ ሆነው ከግዞት የያዕቆብን መምጣት ይጠብቁ ስለነበር የአጼ ሱስንዮስን ጥሪ አሁንም ውድቅ አደረጉት ።[19] ስለዚህ አጼ በጉልበቱ ሱስንዮስ ከጐጃም የኦሮሞ ወታደሮቹን ልኮ በበጌምድር የቁርባንና የአቄትዝር ይዞታዎችንና ተከታዮችን በብርቱ ደበደበ ።[20]

በመሆኑም ከታህሳስ እስከ ሚያዝያ ድረስ በራስ ዘሥላሴ መሪነት የጦር ክፍሎች በአባይ ወንዝ ክልል በደፈጣ ውጊያ ስልት ከቦታ ወደ ቦታ እየተንቀሳቀሰ አደጋ የሚጥለውን አጼ ሱስንዮስን በግምባር ለመግጠም ብዙ ያልተሳኩ ሙከራዎችን አደረጉ ። [21] በዚህ ወቅትና ሁኔታ አጼ ሱስንዮስ ራስ አትናቴዎስን ከነጦሩ በጐጃም ትቶ ራሱ ከአባይ ግዶ የአማራ አምባዎችን በጠላቶቹ ላይ የመከላከያ ምሽጐቹ አድርጐ ያዘ ። [22]

በራስ ዘሥላሴ አመራር የቁርባንና የአቄትዝር የጦር ድርጅቶችና አበጋዞች እስከ ግንቦት 1605 ድረስ ፤ በአንድ በኩል ግዞተኛው ያዕቆብ ከከምባታ ባለመድረሱ በሌላ በኩል ደግሞ አጼ ሱስንዮስ በደፈጣ ውጊያ ታክቲክ ከሥፍራ ወደ ሥፍራ እየተንቀሳቀሰ በግምባር ግጥሚያ በእጃቸው የማይገባ ጠላት ስለሆነ ፤ በፖሊሲ ጉባኤ ወስነው በጥያቄው መሠ

---

[16] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 22 ቁ. 111 ።

[17] ተክለ ሥላሴ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 22 ቁ. 112 ።

[18] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 22 ቁ. 115 ።

[19] ተክለ ሥላሴ ፤የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 22 ቁ. 116 ።

[20] ተክለ ሥላሴ ፤የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 22 ቁ. 117-119 ።

[21] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 22 ቁ. 123-125 ፤ 127 ።

[22] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 22 ቁ. 121፤ 128 ።

ረት ለሱስንዮስ ሊገብሩ ተስማሙ ። [23] ይህንኑ የስምምነት ውሳኔ ለአጼ ሱስንዮስ የሚያሳውቅ አንድ ከፍተኛ የመልእክተኞች ቡድን ላኩ ። [24]

ነገር ግን የራስ ዘሥላሴ የሰላም መልእክተኞች ቡድን ወደ አጼ ሱስንዮስ ሠፈር ከተላከ በኋላ ፤ በሰኔ 1605 ግዞተኛው ያዕቆብ ከከምባታ ወደ ደምብያ መድረሱ በራስ ዘሥላሴ ዘንድ ተሰማ ። በመሆኑም ራስ ዘሥላሴ የመልእክተኞቹ ቡድን የሰላም ተልዕኮውን በማቋረጥ ከአጼ ሱስንዮስ ሠፈር ተመልሶ እንዲመጣ አንድ አስቸኳይ መልእክት ላከ ። [25]

በሰኔ 1605 በደምቢያ ክፍለ ሀገር በቆጋ ከተማ ራስ ዘሥላሴ የቁርባንና የአቄትዝር ሠራዊት መሪ ያዕቆብን ለሁለተኛ ጊዜ አነገሠ (1605-1607) ። የአገሪቱ ማዕከላዊ የቁርባንና የአቄትዝር ጨዋዎች ወይም የጦር ኃይሎች ፤የፖርቱጋል ነፍጠኞችና በግብጻዊው አቡነ ጴጥሮስ የተመራው የአገሪቱ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከአጼ ያዕቆብ ጋር ተሰለፉ ።

አጼ ሱስንዮስ ከጥቂት ዘመዶቹና ተከታዮቹ ጋር የኦሮሞ ወታደሮቹን ሰብስቦ የአማራን አምባዎች የትግሉ መሠረት አድርጎ ያዘ ። በታህሳስ 1604 አጼ ሱስንዮስን በጐጃም ያነገሠው ራስ አትናቴዎስ የኃይል ሚዛን ሁኔታ ገምቶ አሁን ከእርሱ ሠፈር ወደ አጼ ያዕቆብ ሠፈር ሄደ ። [26]

የጦርነቱን የውጊያ ስልት በሚመለከት የአጼ ያዕቆብ ወገን ጥንታዊውንና ንጉሣዊውን ማለትም የጨዋዎችን የግምባር ውጊያ ታክቲክ ሲከተል የአጼ ሱስንዮስ ወገን ግን የሉባን ማለትም የኦሮሞ የደፈጣ ውጊያ ስልት ያዘ ። [27]

በአጼ ሱስንዮስና በአጼ ያዕቆብ መካከል የሥልጣን ጦርነት በ 1604-1605 ሲካሄድ ሳለ ቄስ ፓየዝን ተከትለው አራት ሌላ ኢየሱሳውያን ሰባኪዎች ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ። [28] ነገር ግን በሁለቱ ነገሥታት አንጃዎች መካከል በሰኔ 1605 የሀያ ሁለት ወራት ጦርነት ከተከፈተ በኋላ የድል ሚዛን አቅጣጫውን እስኪያሳውቅ ድረስ ቄስ ፓየዝ በጐጃም ወደ ራስ አትናቴዎስ ሠፈር ሸሸ ። [29] ራስ አትናቴዎስ ከአጼ ዘድንግል ጋር

---

[23] ተክለ ሥላሴ <u>የሱስንዮስ ታሪክ</u> ፤ም. 23 ቁ. 129-133 ።

[24] ተክለ ሥላሴ ፤<u>የሱስንዮስ ታሪክ</u> ፤ም.23 ቁ. 130-131 ።

[25] ተክለ ሥላሴ ፤ <u>የሱስንዮስ ታሪክ</u> ፤ ም. 24 ቁ. 134

[26] ተክለ ሥላሴ ፤<u>የሱስንዮስ ታሪክ</u> ፤ም. 29 ቁ. 154-156 ።

[27] ተክለ ሥላሴ ፤ <u>የሱስንዮስ ታሪክ</u> ፤ ም. 30 ቁ. 157 ።

[28] Getahun Dilebo, " The Portuguese in Ethiopia" p. 130; S. Gobat, *Journal Of Three Years' Residence in Abyssinia* (1850,) pp. 75-77.

[29] *Ibid.*, " The Portuguese in Ethiopia," p. 131; *Journal*, p. 76.



ቄሱ ፓየዝ ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት ከለወጣቸው ከኢትዮጵያ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አንዱ እንደነበር አይዘነጋም ።

በጦርነቱ መሀል ራስ አትናቴዎስ ከአጼ ሱስንዮስ ሠፈር ወጥቶ ወደ አጼ ያዕቆብ ወገን በሄደ ጊዜ ከዘመናዊ የጦር መሣሪያና ትምህርት አኳያ በጠላቶቹ ላይ ሊያስገኝለት የሚችለውን ጥቅም በማስገንዘብ ቄስ ፓየዝን ከሁለት ሌላ ኢየሱሳውያን ጋር በቆጋ ቤተ መንግሥት ወደ አጼ ያዕቆብ አቀረበ ።

በመሆኑም በጥር 1606 አጼ ያዕቆብ ፓየዝን ከአገሩ መንግሥት በአስቸኳይ ወታደራዊ እርዳታ እንዲያስመጣለት ጠየቀ ። [30] አጼ ያዕቆብ በበኩሉ የካቶሊክ ሃይማኖት ለመቀበል ፈቃደኛ መሆኑን ለቄሱ ፓየዝ ቃል ገባ ። [31] በዚህ ስምምነት መሠረት በአጼ ያዕቆብ ስም ፓየዝ ለተጠየቀው ወታደራዊ እርዳታ ወደ ሊዝቦንና ወደ ሮም ደብዳቤዎችን ላከ ። [32]

በጦርነቱ መጀመሪያ ከአራቱ አውራ ተዋንያን አጼ ሱስንዮስና ራስ አትናቴዎስ በጐጃምና በአማራ ክፍለ ሀገራት አጼ ያዕቆብና ራስ ዘሥላሴ በደምቢያና በበጌምድር ክፍለ ሀገራት እንደተሰለፉ ይታወሳል ። በሰኔ 1605 የቁርባንና የአቄትዝር ጨዋዎች በራስ ዘሥላሴ መሪነት በቆጋ ደምቢያ ያዕቆብን ማንገሳቸው እንደታወቀ አጼ ሱስንዮስ ከጐጃም በበጌምድርና በአማራ ክፍለ ሀገር በሚገኙ በአጼ ያዕቆብ ደጋፊዎች ላይ ታላቅ የቅጣትና የዘረፋ ጦርነት እንዳካሄደባቸው አይዘነጋም ። [33]

ነገር ግን በሰውና በመሣሪያ ሚዛን ሰላሳ ለአንድ የሚሆን ከፍተኛ ብልጫ የነበራቸው አጼ ያዕቆብና ራስ ዘሥላሴ በአማራ ታላላቅ አምባዎች ላይ በደፈጣ ውጊያ ስልት ከቦታ ወደ ቦታ እየተንቀሳቀሰ በድንገት ጥቃትና ጥፋት የሚያደርሰውን የአጼ ሱስንዮስን የጦርነት ታክቲክ በቁርባንና በአቄትዝር ጨዋዎች የግምባር ውጊያ ስልት እየተመሩ ግምባር ለግምባር ደርሰው መግጠም አቃታቸው ። [34]

በመስከረም 1605 አጼ ያዕቆብ ከበጌምድር ራስ ዘሥላሴ ደግሞ ከጐጃም በመሆን በሁለት ግምባሮች በአማራ አምባዎች ላይ በመሸገው በአጼ ሱስንዮስ ላይ ያልተሳኩ የጥቃት እርምጃዎችን ወሰዱ ። በዚህ ወቅት የአጼ ሱስንዮስ ፈጣን ጦር በደፈጣ ውጊያ የራስ ዘሥላሴን የቁር

---

[30] Getahun Dilebo, " The Portuguese in Ethiopia," p. 131.

[31] *Ibid.*

[32] *Ibid.*

[33] ተክለ ሥላሴ ፤ <u>የሱስንዮስ ታሪክ</u> ፤ ም. 25 ቁ. 137 ።

[34] ተክለ ሥላሴ ፤ <u>የሱስንዮስ ታሪክ</u> ም. 25 ቁ. 138 ም. 27 ቁ. 145 ።

ባን ሠራዊት ከጥቅም ውጭ አደረገ ።[35] ከዚህ ሽንፈት በኋላ ብዙ ጊዜ ሳይቆይ ራስ ዘሥላሴ በአጼ ያዕቆብ ላይ ከአጼ ሱስንዮስ ጋር በስውር የስምምነት ድርድር ጀመረ ።[36] በሌላ በኩል ደግሞ ራስ አትናቴዎስ በስም በአጼ ሱስንዮስ ሠፈር እንደሆነ ከአጼ ያዕቆብ ጋር ሕቡዕ የስምምነት ፖለቲካ ከፈተ ።[37]

በመጋቢት 1606 አጼ ሱስንዮስ በጨጨሆ በጌምድር በቀጥታ ከአጼ ያዕቆብ ሠራዊት ጋር በመጀመሪያ የግምባር ውጊያ ተጋጥሞ ሲያሸንፍ ፤ ከአጼ ያዕቆብ ጋር በጦር ሜዳው የተገኘው አቡነ ጴጥሮስ በጠላት ጥይት ቆስሎ ሄደ ።[38]

ከጨጨሆ ጦርነት በኋላ በህዳር 1606 አካባቢ አጼ ሱስንዮስ ከአማራ ፤ አጼ ያዕቆብ ደግሞ ከደምቢያ በየግምባራቸው የአባይ ወንዝ ተሻግረው ለመጨረሻ ፍልሚያቸው ወደ ጐጃም ገቡ ። በዚህ ወቅት በአጼ ያዕቆብ ሠፈር የዘመኑና የሥርዓቱ ኃይለኛ የቁርባንና የአቴትዝር ጦር አበጋዞች ለአጼ ሱስንዮስ በጻፉለት ደብዳቤ የዘመኑን የጦር ሥርዓት ኃይልና ተግባር እግረ መንገዳቸውን እንደሚከተለው ገለፁ ። በዘመኑ የነገሥታት ሹም ሽር የሚያደርጉ የቁርባንና የአቴትዝር የጦር አበጋዞች ለአጼ ሱስንዮስ በጻፉለት ደብዳቤ ፤

" እኔን ያነግሡኛል ብለህ አትጠራጠር ። በልብህም አታስብ ። ከንጉሡ ከመላክ ሰገድ ( ሠርፀ ድንግል ) ልጆች መካከል ወንድ ልጅ ብናጣ ከሴት ልጆቹ መርጠን እናነግሳለን ። ይህም ባይሆን በአምባ ግዞት ከሚኖሩ እስራኤላውያን ( ልዑላን ) አንዱን እስከናነግስ ድረስ አንተን አንፈልግም ። በፍቅርም አናነግስህም ። በግድም ቢሆን እናሸንፍሃለን ። ነገር ግን የምንዋጋበትን ቦታ አንተ ምረጥ ። በምትመርጠውም የውጊያ ቦታ ፀንተህ ቁም ። እንደ ልማድህ ፈርተህ አትሽሽ ። ደግሞም አትርሳ ። ፋሲልን ድል ያደረግነው ያዋረድነው እኛ ነን ። አዜን ድል ያደረግነው፤ መሐመድን ድል ያደረግነው የገደልነው ሠራዊቱንም ያጠፋንበት እኛ ነን ። የአበጢን ጋላ ድል ያደረግነው የገደልነው እኛ ነን ። የረድኤትን የካሌፍን የጐሽን አምባ ( በሰሜን አምባ የፈላሻ አመጸኛ መሪዎች የነበሩትን ማለታቸው ነው) የሰበርነው እኛ ነን ። ስለዚህ ያነግሡኛል ብለህ በፍጹም አታስብ "[39]

በማለት በአለፉት አራት አሥርታት ውስጥ ከአፄ ሠርፀ ድንግል እስከ አጼ ያዕቆብ ( 1563-1606) ድረስ በአገር አቀፍ ደረጃ በየወቅቱና በየአካባቢው ማለትም በማዕከል በቤተ መንግሥት አካባቢ ፤ በሀዲያ ፤ በአዳል በፈላሻ አገሮችና መሪዎች ላይ ያካሄዱ የጦርነት ሥራዎችን በጉራ እየዘረዘሩ አስፈራሩት ።

ነገር ግን በመጋቢት 10 ቀን 1607 በጐጃም ደብረ ዘይት በሚባል ሥፍራ ጐል በተባለው ተራራ ሥር በዜና መዋዕሉ ጸሐፊ በተክለ ሥላሴ ግምት በኃይል ሚዛን ሰላሳ ለአንድ ሰው የነበረው የአጼ ያዕቆብ ታላቅ ሠራዊት ከአጼ ሱስንዮስ በከፍተኛ ደረጃ ከተደራጀ ግን በቁጥር በጣም አነስተኛ ከነበረው ጦር ጋር ለመጨረሻ ጊዜ በግምባር ተጋጠመ ።

የአጼ ያዕቆብ በጦር ፤ በጐራዴ ፤ በጋሻና በጠመንጃ የታጠቁ የእግርና የፈረስ ወታደሮች እንዲሁም በዘመኑ " ቱርክ " እና " ናራ" ተብለው የሚጠሩ ነፍጠኞች (የፖርቱጋል ነባር ነፍጠኞች ጨምሮ) በቁርባንና በአቴትዝር የጦር አበጋዞች በእነራስ አትናቴዎስ ሥር የተሰለፉት በጨዋ ሠራዊት የውጊያ ደምብ መሠረት በሜዳ ላይ ሁሉም በአንድነት ለግምባር ጦርነት ነበር ።[40]

በሌላ በኩል የአጼ ሱስንዮስ በቁጥር ጥቂት ሆኖ በጦር ፤ በጐራዴና በጋሻ የታጠቀ የእግርና የፈረስ ሠራዊት የተደራጀው ደግሞ በኦሮሞ[41] የሉባ ጦርነት ስልት መሠረት ለደፈጣ ውጊያ በትንንሽ ቡድኖች በሥፍራ ተለያይቶና ተበታትኖ በራሱ በሱስንዮስና በታናሽ ወንድሙ በራስ ስዕለ ክርስቶስ ጥምር አዝማችነት ነበር ። በዘመኑ የእስፔኑ ኢየሱሳዊ የታሪክ ጸሐፊ አልሜይዳ በዓይኑ አይቶ እንደ ጻፈው " የጋላ ወታደሮች ለጦርነት የሚ ደራጁ በቁጥር ከ6000 እስከ 8000 የሚደርሱ ምርጥ ወጣቶችን በሚይዙ[42] ቡድኖች ነበር ። የእነዚህ ቡድኖች " የዘመቻ ዓላማ ጠላትን ለማሸነፍ ወይም ለመሞት ስለሆነ "[43] በጠላት ወገን በጣም ይፈሩ ነበር ።

---

[35] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 27.ቁ. 146 ።

[36] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 27 ቁ. 147 ፤ ም. 28 ቁ. 151

[37] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 29፤ ቁ. 154 - 155 ።

[38] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 27 ቁ. 147 ።

[39] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 29 ቁ. 152 ፤ ለማስታወስ ያህል በሰኔ 1605 ያዕቆብ ከግዞቱ ከመምጣቱ በፊት እነዚሁ የጦር አበጋዞች በራስ ዘሥላሴ መሪነት የአጼ ሱስንዮስን ንግሥ ለመደገፍ ተስማምተው አንድ የመልእክተኞች ቡድን ወደ በጌምድር እንደላኩለት አይረሳም ( ተክለ ሥላሴ የሱስንዮስ ታሪክ ም. 23)

[40] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 30 ቁ. 156-157 ።

[41] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 30 ቁ. 157 ።

[42] Beckingham and Huntingford, *Some Records*, pp. 137-38

[43] *Ibid.*, p. 137.

በዚህ ወጣት የጦር ኃይል ነበር አጼ ሱስንዮስ በመጋቢት 10 ቀን 1607 በዘመዱና በዙፋን ጠላቱ በአጼ ያዕቆብ ላይ የመጨረሻውን ድል የተቀዳጀው ። የጦርነቱ ውጊያ በአጼ ያዕቆብ ሠራዊት ተከፈተ ። በውጊያ ሂደት በቡድን በቡድን በሥፍራ ተለያይቶና ተበትኖ ከኋላ በድብቅ የተሰለፈው የአጼ ሱስንዮስ ጦር ከተራራማ ሥፍራ በቁልቁለት እየተከታተለ በሜዳው ላይ በተሰለፈው የጠላት ወገን ላይ በድንገት ሲወርድበት በጠላቱ ጐራ ታላቅ ሽብርና ትርምስምስ ተፈጠረ ። ጦርነቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአጼ ሱስንዮስ ድል ተፈፀመ ። አጼ ያዕቆብና አቡነ ጴጥሮስ ሁለቱም በጦርነቱ ሜዳ ሞቱ ። ራስ አትናቴዎስ ደግሞ በሽሽት አምልጦ በዲማ መነኩሳት ዘንድ ተማጸነ ። ነገር ግን ከገዳሙ መነኩሳት ዘንድ ራስ አትናቴዎስ በራስ ስዕለ ክርስቶስ እጅ በምርኮ ተወሰደ ።ድል አድራጊው አጼ ሱስንዮስ በደምቢያ ወደ ቀድሞ የያዕቆብ ቤተ መንግሥት አመራ ።[44] ከ1603 እስከ 1607 ድረስ በሁለት ነገሥታት ላይ የሽረትና የሞት ውሳኔ የፈጸመውና በደብረ ዘይት ጦርነት ዋዜማ ወደ አጼ ሱስንዮስ ወገን የሄደው ራስ ዘሥላሴ በ1608 በእሱም ላይ ያልተሳካ ሴራ ሲያካሂድ ተገደለ ። [45]

ሱስንዮስ ከ1597 እስከ 1607 ለአሥር ዓመታት ከኃይለኛ የጦር አበጋዞችና የሥልጣን ባላንጣዎች ጋር ረጅምና መራራ ግጭት አካሄዶ በመጨረሻ በሰሜኑ ደጋ በአካባቢ የተወሰነ የአጼ መንግሥት ሥልጣን በኃይል ሚዛን ያዘ ። ከ1607 እስከ 1632 ድል አድራጊው አጼ ሱስንዮስ ኢየሱሳውያን በተባሉ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ትምህርትና ምክር በኢትዮጵያ ጥንታዊና በሀወርታዊ ሕብረተሰብ ዘንድ ከላይ በንጉሣዊ ትዕዛዝና ውሳኔ ዘመናዊ የትምህርትና የባህል ለውጥ ለማምጣት በወሰዳቸው ብርቱ የፖሊሲና የተግባር እርምጃዎች በሰሜኑ ደጋ ከባድ የጸጥታ ፤ የአስተዳደር ፤ የኤኮኖሚ ፤ የአካባቢ ፤ የሃይማኖት ፤ የጐሳና የፖለቲካ ችግሮች ስለአጋጠሙት ፤ በመሀል ሥፍራ የሰፈረውን የኦሮሞ ሕዝብ አልፎ ደቡብ ኢትዮጵያን እንደ ጥንቱ ነገሥታት በማዕከላዊ የአጼ መንግሥት ሥር ለማስተዳደር አቅምና ጊዜ አጣ ። በመሆኑም በአገሪቱ ረጅም ታሪክ እስከ አስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ድረስ በአገር አቀፍ ደረጃ የአካባቢ የፖለቲካ ሥርዓትና ሥልጣን ተስፋፋ ። በዚህ ሁኔታና ወቅት ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ አንድ ታላቅ አካባቢ ሆኖ በአጼ ሱስንዮስ ተቆረቆረ ። በዚህ ረገድ

[44] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፣ ም. 30 ።

[45] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ም. 34 ።



አንደኛ ፤ አጼ ሱስንዮስ የዘውድ ሥልጣኑን የያዘው የማዕከላዊ መንግሥት ሥርዓትንና ሥልጣንን በሚቃወሙ የአካባቢ የጦር ፤ የመሳፍንትና የቤተክርስቲያን ኃይሎች ላይ ገና በፍለሳ እንቅስቃሴ ላይ የነበረውን የኦሮሞ ሕዝብ በውትድርና አገልግሎት በመጠቀም እንደሆነ ይታወሳል።

በተጠቀሰው የሰሜኑ ደጋ አካባቢ የአጼ ሥልጣኑን ይዞ ኢየሱሳውያን በተባሉ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ትምህርትና ምክር ፤ አጼ ሱስንዮስ ከላይ ከዙፋን በንጉሣዊ ትዕዛዝ በሕብረተሰቡ ዘንድ አዲስ ትምህርትና ባህላዊ ለውጥ ለማስገባት ብርቱ የፖሊሲ እርምጃዎችን በወሰደ ጊዜ የተጠቀሱ ተቃዋሚ የጦርና የሃይማኖት ኃይሎች[46] በአንድ በኩል ፤ በአካባቢው በትግራይ ፤ በአንጎት ፤ በላስታ ፤ በአማራ ፤ በበጌምድር በደምቢያና በጐጃም ክፍለ ሀገራት ላይ በፍለሳ ስምሪት ገና መስፋፋት የሚፈልጉ የተለያዩ የኦሮሞ ጐሳዎች[47] በሌላ በኩል ሁሉም በአንድነትና በየፊናቸው የጋራ ጠላቶቹ ሆኑበት ።

ሁለተኛ ፤ ከ1607 በኋላ በሰሜኑ ደጋ አካባቢ በአጼ ሱስንዮስና በአካባቢው ነባር የፈላሻ ፤ የአገውና የጉሙዝ ሕዝቦች መካከል በሥፍራና በጊዜ የማያቋርጥ የግዛትና የግብር ጦርነት ተጀመረ ። በዚህ ረገድ በሰሜን ምዕራብ በጣና - አባይ ክልል በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ የኢማም አህመድ ግራኝ መንግሥት ( 1535- 1543) ቀጥሎም በአስራ ሰባተኛው ምዕተ ዓመት የአጼ ሱስንዮስ መንግሥት ብሎም የጐንደር ሥልጣኔ የተመሠረተው በእነዚህ በተጠቀሱት ሦስት ጥንታዊ ሕዝቦች መሬት ጉልበትና ሀብት ላይ ነው ።

ከ1607 እስከ 1632 ድረስ በዚህ ክልል አጼ ሱስንዮስ ከፈላሻ ፤ ከአገውና ከጉሙዝ ነባር ሕዝቦች ጋር ረጅም የቅጣት የዘረፋና የግብር ጦርነቶች እንደ አካሄደ በዜና መዋዕሉ ተመዝግቦአል ። በተለይም በተከዜ ወንዝና በጣና ሐይቅ መካከል በሚገኘው አገሩ በአስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት ከአጼ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት (1413-1344) ጀምሮ ለረጅም ዘመን ለአካባቢ ሥልጣን ከአገሪቱ ማዕከላዊ አጼ ነገሥታት ጋር የማያቋርጥ የፖለቲካና የትጥቅ አመጽ ያካሄድ የነበረውን ጥንታዊ የፈላሻ ሕዝብ በ1610ዎቹና በ1620ዎቹ አሥርታት አጼ ሱስንዮስ ከረጅምና መራራ ጦርነት በኋላ በንጉሣዊ የቅጣት ውሳኔ የሃይማኖት በአሉን ሻረ ። ከመሬ

[46] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ.ታሪክ ፤ ም. 33 ፤ 35 ፤ 36 ፤ 38 ፤ 41 ፤ 43 ፤ 44 ፤ 45 46 ፤ 49 ፤ 51 -55 ፤ 57 ።

[47] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ም. 33 ፤ 36 ፤ 37 ፤ 41-42 ፤ 44-45 ፤ 50 ፤ 56-

ቱም ነቅሎ በሌላ የአካባቢ ሕዝቦች መካከል በተነው ። [48] ከዚያን ጊዜ ወዲህ ከአገሩ የተነቀለው የፈላሻ ሕዝብ በአካባቢው የአማራ ፣ የአገውና የትግሬ ሕዝቦች መካከል ተበትኖ በተወሰነው ክልል በአመዛኙ በእደ ጥበብ ሥራ የሚኖር ማኅበረሰብ ሆነ ።

ሦስተኛ ፣ ከ1616 እስከ 1632 ድረስ ኢየሱሳውያን በተባሉ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ትምህርትና ምክር መሠረት በአጼ ሱስንዮስ ፣ በወንድሙ በራስ ቢትወደድ ስዕለ ክርስቶስና በአልጋ ወራሽ ፋሲለደስ መሪነት ወደ አዲሱ የካቶሊክ ሃይማኖት በተለወጠው በአገሪቱ የመሳፍንት ወገንና በግብጹ አቡን በሚመራው የኦርቶዶክስ ምዕመናን አንጃ መካከል ረጅምና መራራ የሆነ የሃይማኖት ጦርነት ተካሄደ ። [49] በሮምና በግብጽ ማለትም በካቶሊክና በኦርቶዶክስ አንጃዎች ተከፍለው የአገሪቱ ብዙ ክርስቲያኖች በእርስ በርስ ጦርነት አለቁ ። በግብጹ አቡን ስምኦን መሪነት የኦርቶዶክስ ክርስትና የሚከተሉ የሕብረተሰቡ የጦር ፣ የክህነትና የእርሶ አደሩ ወገኖች በአገሪቱ ረጅም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአጼው ርዕሰ ብሔሩና በመሳፍንቱ ወገን ላይ በትጥቅ አመጽ ተነሱ ።[50] በአገሪቱ የኦርቶዶክስ ክህነትና ገዳማት መካከል ደግሞ ለሦስት ምዕተ ዓመታት የማያቋርጥ የሃይማኖት ክርክር ፣ ሁከት ፣ ስደትና መከራ ተጀመረ ። [51]

አራተኛ ፣ በሌላ አኳያ ፣ በ1610ዎቹ የሁለተኛው አጋማሽ አጼ ሱስንዮስ ከደምቢያ የፖለቲካ ማዕከል የአገሪቱን ብሔራዊ የግዛት ክልል በሰሜን ምዕራብ በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ አካባቢ በዘመኑ ዜና መዋዕል ጸሐፊ ተክለ ሥላሴ ቃል ፣ "በቀይ ባህር ከሱዋኪን ዳርቻ ወርቅ እስከሚወጣበት ፋዝቁሎ"[52] ማለትም እስከ የዛሬው አሶሳ ወለጋ አካባቢ ድረስ ለማስፋፋት ብርቱ ፖለቲካዊና ወታደራዊ እርምጃዎችን ወሰደ ።

[48] ተክለ ሥላሴ ፣ የሱስንዮስ ታሪክ ፣ ም.41-44 ። በዜና መዋዕሉ ፣ ቃል ፣ በ1616 አጼ ሱስንዮስ አገረገዥዎቹን " ከየግዛታቸው ያሉትን ፈላሾች ማንንም ሳያስተርፉ እንዲገድሏቸው አዘዘ ። ከፈንሐስ ጋር ከሸሹት ፈላሾች በቀር ሁሉም እንዲገደሉ አዘዘ ። የፈላሻ ሚስቶችና ልጆችን ለራሱ ባሮች አደረገ ። ለወደደውም በተናቸው ። በነገሡበት በደንቢያ የነበሩ ፈላሾችን ወደ ክርስትና ይገቡ ዘንድ በክርስቶስ ያምኑ ዘንድ ስማቸውም ከነገሡበት አገር ይጠፋ ዘንድ አዘዘ ። " ፣ ም. 44 ቁ 209 ።

[49] Getahun Dielbo, " The Portuguese in Ethiopia," pp. 135-142.

[50] ተክለ ሥላሴ ፣ የሱስንዮስ ታሪክ ም. 62-63 ።

[51] ተክለ ሥላሴ ፣ የሱስንዮስ ታሪክ ፣ ም. 57 ። አየለ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ፣ ገጽ 137- 59 ።

[52] ተክለ ሥላሴ ፣ የሱስንዮስ ታሪክ ም. 53 ቁ. 245፣347 ።



በዚህ ረገድ በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ማለትም ከአጼ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት በኋላ በአንድ በኩል በሰሜን የምፅዋ ጠረፍ በቱርኮች ቁጥጥር ስር በመሆኑ ፣ በሌላ በኩል በታላቁ የሕዝቦች ፍለሳ ምክንያት ከአባይ ወንዝ የሸዋ እምባ በመለስ መላው ደቡብ ኢትዮጵያ ከማዕከላዊ የአጼ መንግሥት ጥንታዊ ይዞታና ቁጥጥር ውጭ በመሆኑ ፣ በአስራ ሰባተኛው ምዕተ ዓመት መባቻ በሰሜን ምዕራብ በአባይ - ጣና ክልል ደምቢያ የአገሪቱ የአጼ መንግሥት አዲስ መሠረትና ማዕከል ለመሆን እንዴት እንደበቃ ከዚህ በላይ አይተናል ።

በአስራ ሰባተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በተለይም በአጼ ሱስንዮስ ዘመን (1604-1632) ለኢትዮጵያ መንግሥት ከደምቢያ የፖለቲካ ማዕከል በምዕራብ የላይኛው አባይ ሸለቆ በምስራቅ የአትበራ - ቀይ ባህር ክልል እንደ ጥንቱ የአክሱማውያን ዘመን አዲስ የግዛትና የንግድ ማስፋፊያ ክፍትና ቅርብ አካባቢ ሆኖ ተገኘ ።

በተጠቀሰው ዘመን በዚህ ክልል በሁለቱ የአባይ ወንዞች መካከል እስከ አትባራ ወንዝ ድረስ ከአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ጀምሮ ሰናር ወይም ፋንጅ የተባለው ንዑስ ናይሎቲካዊ አዲስ መንግሥት እንደተነሳ ይታወሳል ።[53] በተጨማሪም በአስራ ሰባተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በነጭ አባይና በአትባራ ወንዞች መገናኛ ጥንት የአክሱማውያን ንጉሥ አጼ ኢዛና ከኑባ ጦርነት በኋላ የድል መታሰቢያ ሐውልት ባቆመበት አካባቢ ሐኬት በተባለው በአገሩ የቤጃ ባላባት የሚገዛ የአትበራ አገር ነበር ። እንዲሁም ከዛሬው ከሰላ በስተሰሜን በአርባ ስድስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ፋጥማ በተባለች የቤጃ ባላባት የሚገዛ ዱሮ ለኢትዮጵያ አጼዎች የሚገብር አሮም የተባለ አገር ነበር ። በአጼ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል መሠረት እነዚህ አጐራባች የሰናር ፣ የአትበራና የአሮም አገሮችና መሪዎች ጥንት ለኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ገባሮች ነበሩ።[54]

ይሁን እንጂ ከአስራ ሰባተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ጀምሮ በኢትዮጵያና በሰናር ነገሥታት መካከል በተለይ ለረጅም ዘመን የሚቆይ የንግድና የጠረፍ ግጭት ተፈጠረ ። በሁለቱ አጐራባች አገሮች መካከል የአትበራ - ቀይ ባህር ስትራቴጂያዊ ክልል የግጭቱ መነሻ ሆነ ። ግጭቱም እየተባባሰ በመሄድ በ1616-1618 ወደ ግልጽ ጦርነት ደረሰ።

[53] O.G.S. Crawford., *The Fung Kingdom of Sennar* (1951).

[54] ተክለ ሥላሴ ፣ የሱስንዮስ ታሪክ ፣ ም. 32 ቁ. 167 ፣ ም. 33 ቁ. 171 ፣ ም 46 ቁ. 213 - 215 ፣ ም. 55 ቁ. 249-50 ።

በጸሐፊ ትዕዛዝ ተክለ ሥላሴ ዘገባ መሠረት ፤ የጦርነቱም ምክንያቶች የሚከተሉ ነበሩ ። [55]

1. የሰናር ንጉሥ አለጼ ሱስንዮስ ግብር አልከፈለም ።
2. የሰናር ሰዎች የኢትዮጵያን ብሔራዊ የግዛት ክልል ተሻግረው በደምብያ የዘረፋ ድርጊት ፈጽሞአል ።
3. በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ አምጾ ወደ ሰናር ለሄደው ለመዘጋ ባላባት የሰናር ንጉሥ ጥገኝነት ሰጥቷል ።
4. ወደ ኢትዮጵያ ተሹሞ ይመጣ የነበረው ግብጻዊ አቡነ ይስሐቅ በሰናር አገር ለብዙ ጊዜ ታስሮ ከቆየ በኋላ በእስር ቤት ሞቷል ።
5. በሰናር አገር በኢትዮጵያ ዜጐች ላይ የበደል ሥራ ተፈጽሞአል ።
6. ከኢትዮጵያ የሚሄዱና ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ነጋዴዎች በሰናር አገር ይዘረፋሉ ።

በእነዚህና በሌላም ብዙ ተመሳሳይ የንግድና የጠረፍ ጉዳዮችና ምክንያቶች በ1617-1619 አጼ ሱስንዮስ በሰናር በአትበራና በአርም በተከታታይ ብዙ የፀጥታ ፤ የግዛት ፤ የንግድና የገበያ ማስፋፊያ ዘመቻዎችን ከደምብያ በልዩ ልዩ ወራትና አቅጣጫዎች አካሄደ ።

(1) በሚያዝያ - ግንቦት 1617 በራሱ መሪነትና አዝማችነት አጼ ሱስንዮስ በሰናር ላይ የመጀመሪያውን የቅጣት ዘመቻ አካሄዶ በድል ተመለሰ ። [56] (2) በ1618፤ በደጃዝማች ዮናኤልና በከንቲባ ዘጊዮርጊስ ጥምር አዝማችነት ሌላ የቅጣት ዘመቻ በሰናር ላይ ተካሄደ ። [57] (3) በደጃዝማች ወልደ ሐዋርያት መሪነት አንድ የጦር ሠራዊት ወደ አትበራ ዘምቶ ከአርባ ስድስት ቀናት በኋላ በድል ወደ ደምብያ ተመለሰ ።[58]

(4) በደጃዝማች ተክለ ጊዮርጊስ የትግራይ ገዥ የተመራ ሠራዊት በከሰላ አካባቢ በቤጃ ምድር ዘምቶ በድል ተመለሰ ። [59] (5) በአቤቶሁን መልክአ ክርስቶስና በደጃዝማች ዮናኤል ጥምር አዝማችነት ሦስተኛው የቅጣት ዘመቻ በሰናር አገር ላይ ተካሄደ ። [60] (6) በሐምሌ 1619 ከዛሬ

[55] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 46 ፤ 53 ።
[56] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 46 ቁ. 213 - 214 ።
[57] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 51 ቁ. 242 ።
[58] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 53 ቁ. 245 ።
[59] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 53 ቁ. 245 ።
[60] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 53 ቁ. 245 ።



ኢርትራ በባህረ ነጋሽ ንብረ ግርያም መሪነት ከአሉላ በስተሰሜን በ46 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደሚገኘው የአርም ቤጃ አገር የዘመተው ሠራዊት የአገሩን ባላባት ፋጥማን በምርኮኝነት ይዞታ በደምብያ ወደ ደንቀዝ መጺና ተመለሰ ። [61]

እነዚህን የአገር ግምቢታ ዘመቻዎችን ሂደትና ውጤት መሠረት በማድረግ ፤ ፀሐፊ ትዕዛዝ ተክለ ሥላሴ በስፋት እንደአስቀመጠው ፤ በ1619 አጼ ሱስንዮስ ፤ [62]

« ከእሱ አስቀድሞ የነገሡ ነገሥታት ያላደረጉትን አደረገ ። ከሱዋኪን ከባህር ዳርቻ ወርቅ እስከሚወጣበት ፋዝቁሉ ድረስ እስጉብር የበጋውን ወራት በደስታ አሳለፈ ። [63]

በዚህ ፀሐፊ ትዕዛዝ ተክለ ሥላሴ የጌታውን የአጼ ሱስንዮስን የአገር ግምባታ ሥራ ሰፋ አድርጐ ማቅረቡ ግልጽ ነው ። ነገር ግን በዘመኑ በሰሜን ምዕራብ በቀይ ባህርና በላይኛው አባይ ሸለቆ መካከል የሚገኘው ጥንታዊ የቤጃ ምድር እንደ ጥንቱ የአክሱማውያን ዘመን ለኢትዮጵያ መንግሥት ለንግድና ለግዛት ማስፋፊያ ክፍትና ቅርብ አካባቢ ሆኖ እንደ ቀረበ ብሎም ለኢትዮጵያ የጐንደር መንግሥትና ሥልጣኔ ዕድገት ታላቅ አስተዋጽኦ እንዳደረገ የማያጠያይቅ ጉዳይ ነው ። ምክንያቱም በቀይ ባህር ዳርቻ በምጽዋና በሱዋኪን ደሴቶች መሽገው የተቀመጡ ቱርኮች በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት የሁለተኛው አጋማሽ ከሰሜን ኢትዮጵያ በሽንፈት ከተባረሩ ወዲህ በመሀል አገር ለመስፋፋት እንደገና አልሞከሩም ። በተጨማሪም ነውሱ አጐራባች ናይሎቲካዊው የሰናር መንግሥት በምስራቅ ወደ አትበራ - ቀይ ባህር ክልል ለመስፋፋት ምኞት ቢኖረውም ከኢትዮጵያ ጋር ለመወዳደር ድርጅትም ኃይልም አልነበረውም ። በዚህ ሁኔታና ወቅት በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የጐንደር ነገሥታት በውስጣዊ የእርስ በርስና የሃይማኖት ጦርነት ተይዘው ይህን ክፍትና ቅርብ የሆነ አካባቢ በአጼ ሱስንዮስ በተቀየሰው ፖሊሲ መሠ

[61] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 55 ቁ. 249-250 ።
[62] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 53 ቁ. 247 ።
[63] ተክለ ሥላሴ ፤ የሱስንዮስ ታሪክ ፤ ም. 53 ቁ. 247 ፤ የአጼ ሱስንዮስ ባለሥልጣን የነበረው የኢትዮጵያ በደተኛ አባ ጐርጐርዮስ ለጀርመኑ ምሁር ሉዶልፍ በ1650 ዎቹ በአውሮፓ እንደነገረው ፤ በላይኛው የአባይ ሸለቆ ሰናር ፤ በደቡብ ምዕራብ በጊቤና በዴዴሳ መካከል እናርያ ፤ በመሀል ደቡብ ጉራጌ በሰሜን ምስራቅ ደግሞ የደንከል ሱልጣኑት በዘመኑ ለኢትዮጵያ ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት ራስ ገዝ ገባር አገሮች ነበሩ ። ( *Ludolph, History,pp. 87,235* ).